**DSpace Institution**

**DSpace Repository** | **http://dspace.org**

Ethiopian Languages and Literature - Amharic | Thesis and Dissertations

2020-09-22

# þÿ sÊ •ce `¤v î 5 ( f ô Í5%

þÿ e - q « • , Í

http://hdl.handle.net/123456789/11225

*Downloaded from DSpace Repository, DSpace Institution's institutional repository*

**ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ**

**ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ**

**የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል**


# ሚታዊ ንባብ በኤቶዮጵ ረጅም ልቦለድ ውስጥ

**በ**


**ብርቱካን ሙላው**



**ነሐሴ፣ 2012 ዓ.ም**

**ባሕር ዳር**

**ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ**

**ሂዩማኒቲስ ፋኩሊቲ**

**የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል**

# ሚታዊ ንባብ በኤቶፖጵ ረጅም ልቦለድ ውስጥ

**በ**

**ብርቱካን ሙላው**

**ለአማርኛ ሥነጽሑፍ ሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ መመረቂያ**

**ጥናታዊ ጽሑፍ**

**አማካሪ፡- ተስፋማርያም ገ/መስቀል (ዶ/ር)**

**ነሐሴ፣ 2012 ዓ.ም**

**ባሕር ዳር**

**© 2012 [ብርቱካን ሙላው]**

## ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሂዩማኒቲስ ፋኩሊቲ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል

### የቴሲስ ማረጋገጫ

ይህን "ሚታዊ ንባብ በሌቶ፦ጵ ረጅም ልቦለድ ውስጥ" የተሰኘ የማስተርስ ዲግሪ መመረቂያ ጽሑፍ በደንቡ መሠረት እያነበብኩ ማማከሬን በማረጋገጥ ለቃል ፈተና እንዲቀርብ ስምምነቴን እገልጻለሁ፡፡

ተስፋማርያም ገ/መስቀል (ዶ/ር)

**ፊርማ**

**ቀን**

______________________ ______________________ ______________________

**የትምህርት ክፍሉ ኃላፊ ስም** **ፊርማ** **ቀን**

# ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ

# ሂዩማኒቲስ ፋኩሊቲ

# የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ- አማርኛ ትምህርት ክፍል

## የቴሲስ ፈተና ውጤት ማረጋገጫ

እኛ ስማችን ከታች የተዘረዘሩት የፈተና ቦርድ አባላት “ሚታዊ ንባብ በኤቶፆጵ ረጅም ልቦለድ ውስጥ” የሚለውን መመረቂያ ጽሑፍ ፈትነን፣ የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ መመረቂያ ጽሑፍ እንዲያሟላ የሚፈለገውን ያሟላ መሆኑን እናረጋግጣለን፡፡

### የፈተና ቦርድ አባላት

| | | |
|---|---|---|
| ________________________ | ________________ | ______________ |
| የውጭ ፈታኝ ስም | ፊርማ | ቀን |
| ________________________ | ________________ | ______________ |
| የውስጥ ፈታኝ ስም | ፊርማ | ቀን |
| ------------------------- | --------------------- | ------------------- |
| የፈተናው ሰብሳቢ ስም | ፊርማ | ቀን |

# ምስጋና

ይህ ጥናት  በጀመርኩበ ወቅት ያልተጠበቀ የሕይወት አጋጣሚዎች ገጥሞኝ ዝየ ነበር፤ ይሁን እንጅ ከሁሉ በፊት የሚያስፈልገኝን ሁሉ አሞልቶ፣ የጠየኩትን ሁሉ ሰጥቶ፣ ይህ ሥራዬም ከዚህ ይደርስ ዘንድ ፈቅዶ፣ እየወደድኩት እንድኖር ላደረገኝ **ልዑል አምላካችን እግዚአብሔር** ክብር ምስጋና ይግባው።

ዶ/ር ተስፋ ማሪያም ገ/መስቀል ጽሑፌን አንቀጽ በአንቀጽ እያረምክ በምሁራዊ አንደበትህ በርካታ ገንቢ የሆኑ አስተያየቶች ሰጥተህኛል። ይህ ጽሑፍ አሁን ያለበት ደረጃ እንዲደርስም ያንተ በወቅቱ አርሞ መመለስ ወሳኝ ድርሻ ነበረውና፤ ከልብ አመሰግናለሁ።

የድህረ ምረቃ ትምህረቴን እንድማር ሙሉ ወጪየን ድጋፍ አደረጋለው በማለት፣ በሀሳብ፣ የምታበረታታኝና የመኖሬ ሚስጥር የስኬቴ ሁሉ ምክንያት የምኞትህን ፍፃሜ ሳታይ ለተለየህኝ አባቴ አቶ ሙላው ሽፈራው **እግዚአብሔር** ነፍስህን በአጸደ በገነት ያኑርልኝ፤ እናቴ፣ አባቴ ቢለየንም አይዞሽ ከጎንሽ ነኝ ብለሽ የሰጠሽኝ ሞራል እዚህ አድርሶኛልና ምስጋና ይገባሻል።

ትምህርት በተከታተልኩባቸዉ ዓመታት ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ፍቅራችሁን በመቸር ትምህርቴ ከግብ ይደርስ ዘንድ የሀሳብ ድጋፍ በማድረግ፣ ማቴሪያል በማባዛት፣ ያልተለየኝ ባለቤቴ እንዳለው አቻሜ እና የምጨርስበትን ጊዜ ትናፍቁ ለነበራችሁት ልጆቼ ሀና ጥላሁን፣ አቤል እንዳለው እና ኖቤል እንዳለው እንዲሁም የት ደረሰ አይዞሽ እያላችሁ ማንቂያ ደወላችሁ ላልተለየኝ ሁሌም የምሳሳላችሁ እህቶቼ፣ ወንድሞቼ እና ጓደኞቼ እዚህ ደርሻለሁና ምስጋና ይግባችሁ።

ጓደኛየ አገርነሽ አየለ ከእኔ እኩል ለነበረው ቁጭትሽ መልሱ ይኸውልሽ ላደረግሽው ብቻ ሳይሆን ልታደርጊ ለነበረው ምኞትሽ ሁሉ አመሰግናለሁ።

ለጥናቴ መሳካት ረቂቆቼን በማረም፣ የመጻሕፍት እና የተለያዩ ወዳጃዊ ድጋፎችን በመስጠት አብራችሁኝ ለነበራችሁ ምርጦቼ ጌታቸው ተስፋ፣ መንበሩ ክበር፣ አብይ፣ ይታይሽ ተስፋ፣ መቅደስ ጥላሁን እንዲሁም ስማችሁን ላልጠቀስኳችሁ ጓደኞቼና ወዳጆቼ ሁሉ ከፍ ያለ ምስጋናየን አቀርባለሁ።

# ማውጫ

**ይዘት** **ገጽ**

ምስጋና ..... i
ማውጫ ..... ii
አጠቃሎ ..... iv
ምዕራፍ አንድ ..... 1
መግቢያ ..... 1
1.1. የጥናቱ ዳራ ..... 1
1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ..... 3
1.3. የጥናቱ ዓላማዎች ..... 5
1.4. ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች ..... 6
1.5. የጥናቱ ፋይዳ ..... 6
1.6. የጥናቱ ወሰን ..... 6
1.7. የጥናቱ ዘዴ ..... 7
1.7.1. ልቦለዱ የተመረጠበት መስፈርት ..... 8
1.7.2. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ..... 8
1.7.3. የመረጃ መተንተኛ ስልት ..... 8
1.8. የጥናቱ አደረጃጀት ..... 9
ምዕራፍ ሁለት ..... 10
ክለሳ ድርሳናት ..... 10
2.1. የንድፈሃሳባዊ ጽሑፍ ቅኝት ..... 10
2.1.1. ሚት ..... 10
2.1.2. ሚት እና ሥነጽሑፍ ..... 17
2.1.3. ሚታዊ ተጋዳሊ (Mythical Hero) ..... 18
2.1.4. የሚታዊ ተጋዳሊያን ጉዞ ወይም ተጋድሎ (The Adventure of the Hero) ..... 22
2.1.4.1. መለየት ..... 25
2.1.4.1.1. ወደ ተጋድሎ መጠራት ..... 25
2.1.4.1.2. ጥሪን አለመቀበል ወይም “እምቢኝታ” ..... 27
2.1.4.1.3. የልዕለ ተፈጥሮ ዕርዳታ ..... 28
2.1.4.1.4. የመጀመሪያውን መግቢያ በር ማለፍ ..... 29

2.1.4.1.5. የአሳነባሪ ሆድ ........ 31
2.1.4.2. መነሳሳት ........ 32
2.1.4.2.1. የምርመራ ወይም የሙከራ መንገድ ........ 33
2.1.4.2.2. ከእንስት ጣዖት ጋር መገናኘት ........ 33
2.1.4.2.3. ሴትነት እንደ መሳሳቻ ፈተና ........ 34
2.1.4.3. መመለስ ........ 34
2.1.4.3.1. መመለስ አለመፈለግ ........ 36
2.1.4.3.2. ተዓምራዊ በረራ ........ 37
2.1.4.3.3. የመመለሻውን በር ማለፍ ........ 37
2.2. የቀደምት ጥናቶ ቅኝት ........ 38
ምዕራፍ ሦስት ........ 42
የሚታዊ ተጋዳሊያን የተጋድሎ ጉዞ ደረጃዎች ትንተና በኤቶፆጵ ረጅም ልቦለድ ውስጥ ........ 42
3.1. የልቦለዱ አጽመ ታሪክ ........ 42
3.2. መለየት ........ 45
3.2.1. ወደ ተጋድሎ መጠራት ........ 46
3.2.2. ጥሪን አለመቀበል ........ 51
3.2.3. የልዕለተፈጥሮ ዕርዳታ ........ 52
3.2.4. የመጀመሪያውን መግቢያ በር ማለፍ ........ 57
3.2.5. የዓሳ ነባሪ ሆድ ........ 61
3.3. መነሳሳት ........ 64
3.3.1. የምርመራ ወይም የሙከራ መንገድ ........ 64
3.3.2. ሴትነት እንደ ማሳሳቻ ፈተና ........ 65
3.4. መመለስ ........ 67
3.4.1. መመለስ አለመፈለግ ........ 67
3.4.2. ተዓምራዊ በረራ ........ 69
3.4.3. የመመለሻውን በር ማለፍ ........ 71
ምዕራፍ አራት ........ 74
ማጠቃለያ ........ 74
ዋቢ ጽሑፎች ........ 76
መግለጫ ........ 80

# አጠቃሎ

*ይህ ጥናት "ሚታዊ ንባብ በኢቶዮጵ ረጅም ልቦለድ ውስጥ" በሚል ርዕስ የተደረገ ሲሆን፣ ይኸውም፣ በኤቶዮጵ ልቦለድ ውስጥ የቀረቡትን የሚታዊ ተጋዳሊያን የተጋድሎ ጉዞ ደረጃዎችን ለይቶ ማውጣት እና ተንትኖ ማሳየት የሚል ዓብይ ዓላማን አንግቦ፣ ይህንኑ ልቦለድ ከሚታዊ ሂስ አጻር በመመርመር የሚያስተላልፈውን ሚታዊ ይዘት ገልጧል፡፡ በዚህ ሂደትም፣ ይዞት የተነሳውን ዓብይ ዓላማ ለማሳካት ሰነድ ፍተሻን በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴነት የተጠቀመ ሲሆን፣ የጭብጥ ትንተናን ደግሞ በመተንተኛ ስልትነት ጥቅም ላይ አውሏል፡፡ እነዚህን የመረጃ መሰብሰቢያ እና መተንተኛ ዘዴዎች በመጠቀም እና በልቦለዱ ውስጥ የሚገኙ ተጋዳሊ ገፀባርያት የሚያልፉባቸውን ሦስት ዋነኛ የተጋድሎ ጉዞ ደረጃዎችን መሠረት በማድረግ፣ በእያንዳንዱ ዓበይት የተጋድሎ ጉዞ ደረጃዎች ውስጥም እንዲሁ፣ ተጋዳሊያኑ የሚያልፉባቸውን ዝርዝር ሂደቶች በነቂስ ትንተና ተደርጎባቸዋል፡፡ በዚህ መሠረት በመጀመሪያ፣ "መለየት" በሚለው ዓብይ ጉዳይ ስር፡- ወደ ተጋድሊ መጠራት፣ ጥሪን አለመቀበል፣ የልዕለ ተፈጥሮ እርዳታ፣ የመጀመሪያውን መግቢያ በር ማለፍ እና የዓሳ ነባሪ ሆድ የሚሉትን ዝርዝር የተጋድሎ ሂደቶች ተንትኖ አቅርቧል፡፡ በተከታይነት ደግሞ፣ "መነሳሳት" በሚለው ጽንሰሃሳብ ስር የምርመራ ወይም የሙከራ መንገድ እና ሴትነት እንደ ማሳሳቻ ፈተና የሚሉ ሁለት ጉዳዮች ተዳስሰዋል፡፡ በሦስተኛ ደረጃነትም እንዲሁ "መመለስ" በተሰኘው ዋነኛ የጉዞ ደረጃ ስር መመለስ አለመፈለግ፣ ተዓምራዊ በረራ እና የመመለሻውን በር ማለፍ የሚሉ ዝርዝር ሂደቶች ተቃኝተዋል፡፡ ከዚህ አንጻር፣ ለጥናት በተመረጠው ልቦለድ ውስጥ የሚገኙ ተጋዳሊ ገፀባህርያትን በመለየት የፈጸሟቸውን ተጋድሎዎች ተንትኖ ለማሳየት አቅርቧል፡፡ በአጠቃላይ እነዚህ ተጋዳሊያን ያለፉባቸውን የተጋድሎ ውጣውረዶች፣ ያጋጠሟቸውን ዋነኛ ፈተናዎች እና ከተጋድሎው ያገኟቸውን በረከቶች እንደዚሁም ለተጋድሏቸው መነሻ የሆኗቸውን ዋና ዋና ምክንያቶች በመመርመር በግልጽ ለማሳየት ሞክሯል፡፡ ከዚህ አንጻር ለምርምር በተመረጠው ልቦለድ ውስጥ የቀረቡ ሚታዊ ጉዳዮች ተተንትነው ቀርበዋል ማለት ነው፡፡*

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

ሥነጽሑፍ በቋንቋ አማካኝነት አካላዊ ቅርጽ ይዞ የሚከተብ እና የሰው ልጆች ሁለንተናዊ ህላዌ የሚንጸባረቅበት ጥበብ ስለመሆኑ ለአብዛኛዎቻችን የማያሻማ ሐቅ ነው፡፡ ይኸውም ለረቀቁ ነገሮች ግዝፈትን፣ ለተወሳሰቡ ጉዳዮች ግልፅነትን፣ እንዲሁም ለሁለንተናዊ የህላዌ ገጠመኞች አጽንኦትን በመስጠት የሚከየን እና የሰዎች ልዩ ልዩ የሕይወት መልኮች የሚወከሉበት ፈርጀብዙ የኪነጥበብ ዘርፍ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ከእነዚህ በርካታ የሥነጽሑፍ ዘውጎች መካከል ደግሞ ልቦለድ አንዱ እና (ምናልባትም ዋናው) ነው፡፡

ልቦለድ የሰዎችን ሁለንተናዊ ሕይወት በተመሳስሎ በመቅረጽ በስፋት የሚያቀርብ ምናባዊ ጥበብ ነው፡፡ ስለሆነም ከያንያን በሥራዎቻቸው ውስጥ ኪነጥበባዊ ምናባቸውን ተጠቅመው ለረቀቁ፣ ለጸነኑ እና ለተወሳሰቡ ገጠመኞቻቸው አንዳች አካላዊ ቅርጽ አበጅተው እና አግዝፈው ለተደራሲያኑ ሕውስታ ሥርዓት ያስገዛሉ (ቴዎድሮስ ገብሬ፤ 2001፣xv)፡፡

በሥነጽሑፍ ብሎም በልቦለድ ውስጥ የሚከሰቱ ልዩ ልዩ የሕይወት መልኮች ደግሞ ዘርፉን ለትጓርሜ ብዝሃነት እና ለተለያዩ የጥናት እና ምርምር ማሂጃነት ይሆን ዘንድ በር ከፋቾች ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ የአንድ ሥነጽሑፋዊ ሥራ ቅርጽም ሆነ ይዘት በተለያዩ ወቅቶች ከተለያዩ ንድፈሃሳቦች አንጻር ይጠናል፡፡ አንድን የሥነጽሑፍ ዘውግ ለማጥናት ከሚያገለግሉ በርካታ ሥነጽሑፋዊ ንድፈሃሳቦች መካከል ደግሞ ሚታዊ ሂስ አንዱ ነው፡፡

ሚታዊ ሂስ በተለይም፣ በአንድ የሥነጽሑፍ ሥራ ውስጥ የሚነሱ ልዩ ልዩ ተምሳሌታዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ታሪካዊ፣ ባህላዊ እና መሰል ሐተታዎችን ለመተንተን ያገለግላል፡፡ ምክንያቱም "ሚት" የሚለው ቃል በራሱ "ታሪክ"ን ወይም ደግሞ "ልማዳዊ (ከባህል ጋር የተገናኘ) ታሪክ"ን የሚገልጽ ግሪካዊ ቃል ስለመሆኑ Matey (2016; 337) እንዲህ ያትታሉ፤ "Myth is derived from the Greek word mythos, which can mean tale, or story, and that is essentially what the myth is: a story, or a traditional story"፡፡

ሚት ምንም እንኳን ቀደምትነት ያለው እና ጥንታዊ የሆነ እሳቤ ቢሆንም፣ ከ19ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ጀምሮግን ዘመናዊ ወይም ደግሞ ሳይንሳዊ (Scientific) መልክ እየያዘ እንደመጣ Segal (2004) ያስረዳሉ፡፡ በእርግጥም ሚት በ4ኛው እና በ3ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ቅድመ ልደተ ክርስቶስ አካባቢ እንደተጀመረ የዘርፉ ምሁራን ምስክር ናቸው (Segal, 2004፣ Ubaldo Lugli, 2014፣ Matey, 2016 እና ሌሎችም)፡፡ በኋላም ከ19ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ በኋላ ከሥነጽሑፍ በተጨማሪ በማህበራዊ ሳይንስ፣ በሥነ ሰብዕ (anthropology)፣ በሥነ ልቦና፣ በሥነ ማኅበረሰብ (sociology) እና መሰል የሙያ መስኮች እየተጠና እና እየተመረመረ የመጣ ብሎም ለየዘርፎቹ የራሱ የሆነ አበርክቶ ያለው እሳቤ እየሆነ የመጣ ፅንሰሃሳብ ነው (Segal፣ 2004 እና Lugli፣ 2014)፡፡

ቴዎድሮስ ገብሬ (2001፣72) በበኩላቸው፣ "ሚት በፍጥረት እና በፈጣሪ፣ በሰው እና በፍጥረት፣ በግለሰብ እና በማህበረሰብ፣ በሰው እና በህሊናው፣ መካከል ሊኖሩ የሚገቡ ግንኙነቶች ምን መምሰል እንዳለባቸው የተደነገጉበት፤ እንደ ጥሩ እና መጥፎ፣ ትክክል እና ስህተት፣ ጽድቅ እና ኃጢአት፣ ንፅህናና ወንጀል፣ ያሉ እጅጉን የልቦና ጣጣ የሆኑ ተቃራኒ ጥንዶች የተበየኑበት ዶግማ ነው" በማለት ያትቱታል፡፡ Sedigheh Sherkat Moghaddam (2016, 210)ም Djavadi (2004)ን ዋቢ በማድረግ የቴዎድሮስን ገለፃ እንዲህ ይጋሩታል፤ "A myth has a distinguishing feature that […] represents a set of contradictions such as ups and downs, insides and outsides etc"፡፡

እንደ ቴዎድሮስ (2001) እና Moghaddam (2016) ማብራሪያ፣ ሚት ከጥቅሉ ከሰው ልጅ ህልውና ጋር በእጅጉ የተቆራኘ በመሆኑ፤ እራሱ የሰው ልጅ የነገረ ፍጥረት እና የነገረ ህላዌ እንቆቅልሾችን ለመፍታት የሚሞክርበት እንዲሁም ምስቅልቅል የሆነውን የዓለም ህልው ሥርዓት ለማደራጀት የሚጣጣርበት ሃይማኖታዊ፣ ፍልስፍናዊ፣ ማህበራዊ፣ ኪናዊ ወዘተ ሠነድ ነው፡፡

ይህ ጥናት በዶ/ር ኤልያስ ገብሩ አዕምሮ ተደርሶ በ2010 ዓ.ም ለንባብ በበቃው ኤቶፎቭ ረጅም ልቦለድ ላይ ያተኮረ ሲሆን፤ ይህ ልቦለድ ልዩ ልዩ ማኅበራዊ፣ ባህላዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ተፈጥሯዊ እና መሰል ሚት ነክ ጉዳዮችን የሚያትት በመሆኑ የዚህ ጥናት ልዩ ትኩረት ሆኗል፡፡ ስለዚህ በዚሁ ልቦለድ ላይ በመወ'ሰን እና የቀረበውን ሐተታ ከሚታዊ ሂስ አንፃር

በመተንትን የልቦለዱን ይዘት ገልጧል፡፡ ይህንን ለማድረግ ያነሳሳው ዋነኛ ምክንያት ደግሞ በልቦለዱ ውስጥ በዕምነት እና በእውነተኛ ታሪክ ተሸፍነው የቀረቡ የሚታዊ ተጋድሎ (ጉዞ) ደረጃዎችን ለይቶ በማውጣት አጉልቶ ለማሳየት ካለ ልባዊ መሻት የመነጨ ነው፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

*ኤቶዖጵ* ረጅም ልቦለድ የሰዎችን የጋራ ምነት ወይም ሃማኖት፣ ታሪክ እና ልዩ ልዩ ባህላዊ ሁነቶች በጉልህ የሚዳስስ ብሎም የእያንዳንዳችንን አስተሳሰብ እና ዓለማዊ ምስል በድምቀት የሚያሳይ የሥነጽሑፍ ሥራ ነው፡፡ እነዚህ እና መሰል ማህበራዊ እና ባህላዊ ሁነቶች በሥነጽሑፍ ውስጥ የሚስተዋሉ ሚታዊ ጉዳዮች መሆናቸውን በመግለጥ ረገድ ደግሞ ከሚታዊ ሂስ አንፃር ቢጠኑ ተመራጭ ሊሆን እንደሚችል የዚህ ጥናት አጥኚ በጽኑ ታምናለች፡፡ በመሆኑም ይህ ልቦለድ የዕውኑን ዓለም ማኅበረሰብ እምነት እና ፍላጎት እንዲሁም ባህል እና አመለካከት በተለያዩ ሚታዊ ታሪኮች እያዋዛ በማቅረቡ ከሚታዊ ንድፈሃሳብ አንፃር ይጠና ዘንድ የበለጠ ምቹ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

ከዚህ አንጻር፣ አጥኚዋ በሚታዊ ሂስ ማናበቢያነት በመመርመር የሚታዊ ተጋሊያን የተጋድሎ ጉዞ ደረጃዎችን ለመለየት እና አጉልቶ ለማሳየት ካለው የበለጠ ምቹነት አንጻር *ኤቶዖጵ* ረጅም ልቦለድን ለማጥናት ተነሳስታለች፡፡ በተመሳሳይ መልኩ፣ ይህ ጥናት እስከተካሄደበት ጊዜ ድረስ አጥኚዋ ባደረገችው ዳሰሳ መሠረት በዚህ ልቦለድ ላይ ከሚት ጽንሰሃሳብ ጋር የተያያዘ ምንም አይነት ሥነጽሑፋዊ ጥናት ያልተሠራበት መሆኑን ስላረጋገጠች፤ ይህን ልቦለድ ለማጥናት ሌላው አነሳሽ ምክንያት ሆኗታል፡፡

በሌላ በኩል ግን ከዚህ ጥናት አስቀድሞ ሚትን ርዕሰ ጉዳያቸው አድርገው በሌሎች የአማርኛ ልቦለዶች ላይ የተሠሩ ሌሎች በርካታ ጥናቶች ስለመኖራቸው አጥኚዋ ባካሄደችው ቅኝት ለመታዘብ ችላለች፡፡ ከእነዚህ መካከል ደግሞ የታደሰ ሽበሽ (2005 ዓ.ም) "*ሚቶሎጂያዊ ጥናት በእቴሜቴ የሎሚሽታ እና ይወስዳል መንገድ ያመጣል መንገድ*"፣ የቴዎድሮስ ገብሬ (2001) "*የመባዎ ጉዳዮች በገድለ ተክለሃይማኖት ውስጥ*" እና የአለማቀፍ ተናገር (2011 ዓ.ም) "ሚታዊ ንባብ በይስማዕከ ወርቁ *ዴርቶጋዳ* እና *ራማቶሓራ* ረጅም ልቦለዶች" የሚሉት ይገኙበታል፡፡ እነዚህ ሚትን ዋነኛ ጉዳያቸው

ያደረጉ ቀደምት ጥናቶች ደግሞ ከዚህ ከእኔ ጥናት ጋር ያላቸው ተዛምዶ የት ድረስ እንደሆነ እንደሚከተለው በጥቂቱ ተቀምጧል፡፡

በመጀመሪያ የቴዎድሮስ ገብሬ (2001) *"የመባያ ጉዳዮች በገድለ ተክለሃይማኖት ውስጥ"* የተሰኘውን ጥናታዊ ጽሑፍ ያየን እንደሆነ፣ ለትንተና በተመረጠው የገድል መጽሐፍ ውስጥ ተመላልሰው የመጡ እና በተደጋጋሚ የተነሱ ጽንሰሃሳቦች ተዳሰውበታል፡፡ በዚህ መሠረት፣ "የልዕለ ተፈጥሮ እርዳታ" እና በጥቂቱም ቢሆን "መስበክ/መመለስ" የተሰኙት ጉዳዮች (በቴዎደወሮስ አባባል፣ "መባያዎች") ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳሳይነት (በተለይም የስያሜ) ያላቸው ናቸው፡፡ ይሁን እንጅ በሁለቱም ጥናቶች ውስጥ ሙሉ በሙሉ በአንድ አይነት መልኩ ቀርበዋል ማለት ግን በፍጹም አይደለም፤ በሌላ አገላለጽ የቀረቡበት መንገድም ሆነ ዓላማ የተለያየ ነው፡፡

በቴዎድሮስ ጥናታዊ ጽሑፍ ውስጥ ቀደም ሲል ያነሳኋቸውን ጨምሮ ሌሎች "መባያዎች" በተመረጠው ገድል ውስጥ የተከሰቱበትን ድግግሞሽ እና ያላቸውን ትዕምርታዊ ፋይዳ መሠረት ባደረገ መልኩ የተብራሩ ሲሆን፤ በዚህ (በእኔ) ጥናት ውስጥ ግን በተመረጠው ልቦለድ ውስጥ የተሳሉ ተጋዳሊ ገፀባህሪያት የሚጓዙባቸውን ሚታዊ የተጋድሎ ደረጃዎች እና በዚህ ሂደት ውስጥ የሚያጋጥሙ ጉዳዮች እንደዚሁም ከጉዞው በኋላ የሚገኙ ቱርፋቶችን በመግለጥ ላይ በማተኮር የልቦለዱን ይዘት አጉልቶ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ ስለሆነም እነዚህ ሁለቱ ጥናቶች በአንጻር ምርጫ ተመሳሳይ ይሁን እንጅ በእጅጉ የተራራቀም ባይሆን በሚያነሷቸው ሃሳቦችም ሆነ በተነሱባቸው ዓላማዎች ልዩነት አላቸው ማለት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የቴዎድሮስ ጥናት በሃየማኖታዊ ገድላት ላይ መሠረት ያደረገ ሲሆን፤ ይህ የእኔ ጥናት ደግሞ ዋነኛ ትኩረቱ የአማርኛ ልቦለድ ነው፡፡ ይኸውም ሌላው የእነዚህ የሁለቱ ጥናቶች ልዩነት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

ሁለተኛው ደግሞ የታደሰ ሽበሽ (2005 ዓ.ም) "*ሚቶሎጂያዊ ጥናት በእቴሜቴ የሎሚሽታ እና ይወስዳል መንገድ ያመጣል መንገድ*" የተሰኘው ጥናት ሲሆን፣ ይህ ጥናት በተለይም ሚታዊ የሆኑ ጉዳዮችን ከስነልቦና ጋር አያይዞ እና አዛምዶ ያቀረበ ጥናት ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ከታደሰ ጥናት ጋር በአንጻር ምርጫ ይመሳሰል እንጅ ፈጽሞም ባይሆን በሚተነተኑት ጉዳዮችም ሆነ በናሙና ምርጫ የተለያዩ ናቸው፡፡

ሌላው እና የመጨረሻው የአለማቀፍ ጥናት ሲሆን፣ ይኸውም ለጥናቱ በተመረጡት ሁለት ልቦለዶች ውስጥ የተስተዋሉትን እና "ሁነታዊ ሚት፣ ምልክታዊ ሚት እና ሚታዊ ገፀባህርያት" የተሰኙ ጉዳዮችን በእርሷ ስያሜ ደግሞ "የሚት አይነቶች"ን ከሚታዊ ሂስ አንጻር ለመተንተን የሞከረ ንጽጽራዊ ጥናት ነው፡፡ ይሁን እንጅ በዚህ ጥናት ውስጥ የተነሱት፣ በውስጣቸው ሌሎች ንዑሳን ሂደቶችን ያካተቱ ሦስት ዋና ዋና የተጋዳሊያን የጉዞ ደረጃዎች በመሆናቸው፣ በይዘት ትኩረትም ሆነ በአቀራረብ ስልት ከአለማቀፍ ጥናት ጋር የተለየ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

እንግዲህ ከዚህ በላይ እንዳነሳሁት፣ የዚህ ጥናት ዋነኛ ትኩረት ለምርምር በተመረጠው ልቦለድ ውስጥ የቀረቡ የሚታዊ ተጋሊ የተጋድሎ ጉዞ ደረጃዎችን ለይቶ በማውጣት አጉልቶ ማሳየት በመሆኑ እና ሌሎቹ ጥናቶች በዚህ መልኩ ያላነሱት በመሆኑ አጥኚዋ ይህን ጥናት ለማካሄድ ተነሳስታለች፡፡ በሌላ አባባል ልቦለዱ ይህን መሰል ጥናት ለማካሄድ ምቹ እና ከዚህ አስቀድሞ መሰል ጥናት ያልተካሄደበት ከመሆኑ በተጨማሪ፣ ይህን ጥናት ለማካሄድ ያነሳሳው ዋነኛ ምክንያት፣ በታሪኩ ውስጥ የታተቱ የሚታዊ ተጋዳሊ የተጋድሎ ጉዞ ደረጃዎችን ለይቶ በማውጣት የልቦለዱን ይዘት አጉልቶ ለማሳየት መሻት ነው ማለት ነው፡፡

## 1.3. የጥናቱ ዓላማዎች

የዚህ ጥናት ዋነኛ ዓላማ፣ ለጥናት በተመረጠው *ኤቶዖጵ* ልቦለድ ውስጥ የቀረቡትን የሚታዊ ተጋዳሊያን የተጋድሎ ጉዞ ደረጃዎች ከሚታዊ ሒስ አንጻር በመመርመር ማሳየት ሲሆን፣ ይህን ዓብይ ዓላማ ለማሳካት የሚረዱ ዝርዝር ዓላማዎች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. በልቦለዱ ውስጥ ያሉትን ሚታዊ ተጋዳሊ ገፀባህሪያት መለየት፣
2. በልቦለዱ ውስጥ የተሳሉ ተጋዳሊ ገፀባህሪያት ለተጋድሏቸው መነሻ የሆኑ ጉዳዮችን መተንተን፣
3. በልቦለዱ ውስጥ የተሳሉ ተጋዳሊ ገፀባህሪያት በተጋድሏቸው ወቅት ያጋጠሟቸውን መሰናክሎች መፈከር፣
4. በልቦለዱ ውስጥ የተሳሉ ተጋዳሊ ገፀባህሪያት በተጋድሏቸው ያገኟቸውን በረከቶች መመርመር፣

## 1.4. ጥናቱ  የሚመልሳቸው ጥያቄዎች

ይህ ጥናት፣ ለምርምር በተመረጠው ልቦለድ ውስጥ የቀረቡት የሚታዊ ተጋዳሊያን የተጋድሎ ጉዞ ደረጃዎች ምን ምን ናቸው? የሚል ሲሆን፣ ይህንን ጥያቄ በተገቢው መንገድ ለመመለስ የሚያስችሉ ዝርዝር ጥያቄዎች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. በልቦለዱ ውስጥ ውስጥ ያሉት ሚታዊ ተጋዳሊ ገፀባህርያት የትኞቹ ናቸው?
2. በልቦለዱ ውስጥ የተሳሉት ተጋዳሊ ገፀባህሪያት ለተጋድሏቸው መነሻ የሆኗቸው ጉዳዮች ምን ምን ናቸው?
3. በልቦለዱ ውስጥ የተሳሉ ተጋዳሊ ገፀባህሪያት በተጋድሏቸው ወቅት ያጋጠሟቸው መሰናክሎች ምን ምን ናቸው?
4. በልቦለዱ ውስጥ የተሳሉት ተጋዳሊ ገፀባህሪያት ከተጋድሏቸው ምን ምን በረከቶችን አተረፉ?

## 1.5. የጥናቱ ፋይዳ

ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ተጠቃሚዎች ይኖሩታል፡፡

1. ይህን ጥናት ለሚያነቡ አካላት ሚት በአማርኛ ሥነጽሑፍ ሥራዎች ውስጥ ያለውን ስፍራ በማመላከት ቀድሞ በነበራቸው ግንዛቤ  ላይ አንዳች ዕውቀት ያክላል፡፡
2. በተመሳሳይ መልኩ ጥናት ለሚያካሂዱ ሌሎች ተመራማሪዎች እንደማነቃቂያ በመሆን ያገለግላል፡፡
3. ይህ የምርምር ሥራ ሥነጽሑፋዊ ጥናት እንደመሆኑ፣ እራሱ ዘርፉ (ሥነጽሑፋዊ ጥናት) አንድ እርምጃ ከፍ ይል ዘንድ የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በዶ/ር ኤልያስ ገብሩ አእምሮ ኤቶ፦ጵ ረጅም ልቦለድ ላይ ብቻ የተወሰነ ሲሆን፣ በዚህ ልቦለድ ውስጥ በእምነት እና በእውነተኛ ታሪክ ተሸፍነው የቀረቡ የሚታዊ ተጋድሎ ደረጃዎችን በመመርመር እና አጉልቶ በማሳየት ላይ ያኩራል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥም በልቦለዱ ውስጥ የተሳሉትን ተጋዳሊ ገፀባህያት፣ ተጋዳሊያኑ ለተጋድሏቸው መነሻ የሆኗቸውን ጉዳዮች፣ ያለፉባቸውን ሚታዊ ተጋድሎዎች እና ከተጋድሏቸው ያገኟቸውን

በረከቶች ይፈትሻል፡፡ እነዚህን ጉዳዮች ለመተንተን ደግሞ ሚታዊ ሂስን ይጠቀማል፡፡ ምክንያቱም በዚህ ጥናት የሚነሱት እነዚህ ሁሉ ጉዳዮች ከዚህ የትችት አንፃር ጋር ቀጥተኛ ዝምድና ያላቸው እና ሚታዊ ጽንሰሃሳቦች በመሆናቸው ነው፡፡

ለምርምር በተመረጠው *ሔቶዖጵ* ልቦለድ ውስጥ ካሉት በርካታ ዓበይት እና ንዑሳን ገፀባርያት መካከል ተጋዳሊ የሆኑ ገፀባህርያት ብቻ ተለይተው የትንተናው ትኩረት ሆነዋል፡፡ ተጋዳሊያኑ፣ እያንዳንዳቸው ያለፉባቸውን የተጋድሎ መንገዶች ለመሳየት ደግሞ በየራሳቸው ወደተለያዩ ዝርዝር ሂደቶች በሚከፋፈሉ ሦስት ዋና ዋና የተጋድሎ ጉዞ ደረጃዎች (መለየት፣ መነሳሳት እና መመለስ) ላይ ተወስኗል፡፡

"መለየት" በሚለው ስር ወደ ተጋድሎ መጠራት፣ ጥሪን አለመቀበል፣ የልዕለተፈጥሮ እርዳታ፣ የመጀመሪያውን መግቢያ በር ማለፍ እና የዓሳ ነባሪ ሆድ የተሰኙ አምስት ዝርዝር የተጋድሎ ጉዞ ሂደቶች የቀረቡ ሲሆን፤ "መነሳሳት" በሚለው ዋና የተጋድሎ ጉዞ ደረጃ ስር ደግሞ የምርመራ ወይም የሙከራ መንገድ እና ሴትነት እንደ ማሳሳቻ ፈተና በተሰኙ ሁለት ጽንሰሃሳቦች ላይ ብቻ የተገደበ ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ፣ "መመለስ" በተሰኘው ዓብይ የተጋድሎ ጉዞ ደረጃ ስር መመለስ አለመፈለግ፣ ተዓምራዊ በረራ እና የመመለሻውን በር ማለፍ በሚሉት ሦስት ጽንሰሃሳቦች ላይ ብቻ ተወስኗል፡፡

## 1.7. የጥናቱ ዘዴ

በዚህ ንዑስ ርዕሰጉዳይ ውስጥ ልቦለዱ የተመረጠበት መስፈርት፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ እና የመረጃ መተንተኛ ዘዴ የተሰኙ ርዕሰጉዳዮች ይቀርቡበታል፡፡ ከሁሉ በፊት ግን ይህ ጥናት አይነታዊ ምርምር እንደመሆኑ፣ ለምርምር በተመረጠው ልቦለድ ውስጥ ጠቀረቡ ሚታዊ ጉዳዮችን መሠረት ያደረገ የይዘት ትንተና አድርጓል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ ደግሞ ለዚሁ ጥናት ውጤት የሚበጁ ልዩ ልዩ ሐተታዊ ወይም ገላጭ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ በእነዚህ ገላጭ መረጃዎች ማጠናከሪነትም የምርምሩ ታላሚ ጉዳይ ተተንትኖ እና ተብራርቶ ቀርቧል ማለት ነው፡፡

### 1.7.1. ልቦለዱ የተመረጠበት መስፈርት

የዚህ ጥናት ዋነኛ እና ብቸኛ ተጠኚ ወይም ተተኳሪ የዶ/ር ኤልያስ ገብሩ አእምሮ *ኤቶᵨጵ* ረጅም ልቦለድ ስለመሆኑ ከፍ ሲል በተደጋጋሚ ተገልጧል፡፡ በዚህ ክፍል ደግሞ ይኸው ልቦለድ ብቸኛ ተጠኚ ሆኖ ስለተመረጠበት መመዘኛ ይቀርባል፡፡

*ኤቶᵨጵ* ልቦለድ ብቸኛ የምርምር ትኩረት የሆነበት ዋነኛ ምክንያት በልቦለዱ ሐተታ ውስጥ እዚህም እዚያም የቀረቡ ሚታዊ ጉዳዮች በአጥኚዋ አስተውሎት ውስጥ መግባታቸው ነው፡፡ በሌላ አባባል፣ አጥኚዋ ከሌሎች የደራሲው ሥራዎችም ሆነ ከዚህ ቀድሞ ካነበበቻቸው ሌሎች የአማርኛ ልቦለዶች ይልቅ ይህንን ልቦለድ ስትመርጥ፣ ለምርምር ይዛው ከተነሳችው ዋነኛ ጉዳይ ጋር ተዛማጅ ሆኖ ስላገኘችው እና ይህን ጉዳይ ለማሳየትም በቂ እና የተሻለ መረጃ አለው በሚል ጽኑ እምነት ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ይህ ልቦለድ በዓላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴ ተመርጧል ማለት ነው፡፡

### 1.7.2.የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

ቀደም ሲል እንደተጠቀመው፣ ይህ ጥናት አይነታዊ ምርምር እንደመሆኑ ይዞት ለተነሳው ዓላማ መሳካት የሚበጁ ሐተታዊ መረጃዎችን ከልዩ ልዩ ጽሑፋዊ መረጃዎች መቃረምን ይጠይቃል፡፡ ስለሆነም ለዚሁ ጥናት ሁነኛ የተባሉ መረጃዎች ከቀዳማይ እና ካልዓይ የመረጃ ምንጮች የተሰበሰቡ ሲሆን፣ ለዚሁ ጥናት ማሂጃነት የተመረጠው *ኤቶᵨጵ* ረጅም ልቦለድ በቀዳማይ የመረጃ ምንጭነት ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ፣ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከዚህ ጥናት ጋር ዝምድና ያላቸው ሌሎች ጥናቶች እና ስለሚታዊ ጉዳዮች የሚያወሱ መዛግብቶች በካልዓይ የመረጃ ምንጭነት አገልግለዋል፡፡

### 1.7.3.የመረጃ መተንተኛ ስልት

ይህ ጥናት በዋነኛነት ለምርምር በተመረጠው ልቦለድ ውስጥ የቀረቡ የሚታዊ ተጋድሎ ደረጃዎችን ለይቶ በማውጣት አጉልቶ ማሳየት ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ ጥናት ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለው የጭብጥ ትንተና (የይዘት ፍካሬ) የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ነው ማለት ነው፡፡ በዚህ መሠረት ለጥናት በተመረጠው ልቦለድ ውስጥ የተስተዋሉ ሚታዊ ጉዳዮች የሚታዊ ተጋዳሊያን መነሻ ምክንያቶች፣ የተጋዳሊያን ያለፉባቸው የተጋድሎ ጉዞዎች እና በተጋድሏቸው የገኟቸው በረከቶች ከሚታዊ ሂስ አንፃር ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

## 1.8. የጥናቱ አደረጃጀት

ይህ ጥናት በአራት ዋና ዋና ምዕራፎች የተከፋፈለ ሲሆን፣ ምዕራፍ አንድ የጥናቱን ዳራ፣ የጥናቱን አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱን ዓላማዎች፣ የጥናቱን የምርምር ጥያቄዎች፣ የጥናቱን ጠቀሜታ (ፋይዳ)፣ የጥናቱን  ወሰን (ገደብ) እና ውስንነቶች እንዲሁም የጥናቱን ሥነ ዘዴ አካቶ ይዟል፡፡

ምዕራፍ ሁለት ደግሞ በዋናነት  የጥናቱ ማዕከላዊ ጉዳይ የሚተነተንበትን የንድፈ ሃሳባዊ ጽሑፍ ክለሳ እና የቀደምት ጥናቶች ክለሳን ያካተተ ሲሆን፣ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የሚታዊ ሂስ ምንነት፣ የሚታዊ ንድፈሃሳብ እና የሥነጽሑፍ ዝምድና፣ የሚታዊ ተጋድሎ ምንነት፣ የሚታዊ ተጋዳሊያን ጉዞ ወይም ተጋድሎ ደረጃዎች የሚሉት ፅንሰ ሃሳባዊ ጉዳዮች ትንተና እንደዚሁም የቀደምት ጥናቶች ክለሳ የተካሄደባቸው ንዑሳን ርዕሶች ቀርበውበታል፡፡

ምዕራፍ ሦስት “የሚታዊ ተጋዳሊያን የተጋድሎ ጉዞ ደረጃዎች” በሚል ርዕሰ ጉዳይ ስር በየራሳቸው ወደተለያዩ ንዑሳን ርዕሰጉዳዮች የሚከፋፈሉ ሦስት ንዑሳን ርዕሶች የተነሱ ሲሆን፣ እነዚህም፡ መለየት፣ መነሳሳት እና መመለስ የሚሉት ናቸው፡፡ ይኸውም ለትንተና በተመረጠው ኢቶዮጵ ረጅም ልቦለድ ውስጥ በተገለጹት የሚታዊ ተጋዳሊያን የተጋድሎ ጉዞ ሦስት ደረጃዎች ውስጥ በሚገኙት ዝርዝር የጉዞ ሂደቶች ላይ የተደረገውን ትንታኔ የያዘ ምዕራፍ ነው፡፡

አራተኛው እና የመጨረሻው ምዕራፍ ደግሞ ከዚህ ምዕራፍ አስቀድሞ በነበሩት ሦስት ምዕራፎች ውስጥ የተነሱት ጉዳዮች በማጠቃለያ መልክ የቀረበበት ክፍል ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ዓብይ ምዕራፍ ስር የንድፈሃሳባዊ ጽሑፍ ቅኝት እና የቀደምት ጥናቶች ቅኝት የሚሉት ሁለት ንዑሳን ርዕሰጉዳዮች የቀረቡ ሲሆን፤ የንድፈሃሳባዊ ጽሑፍ ቅኝት በሚለው ንዑስ ርዕስ ስር ሚት፣ ሚት እና ሥነጽሑፍ፣ ሚታዊ ተጋዳሊ እና የሚታዊ ተጋዳሊያን ጉዞ ወይም ተጋድሎ የተሰኙ አራት የንዑስ ንዑሳን ርዕሰጉዳዮች ጽንሰሃሳባዊ ዳሰሳ ተደርጎባቸዋል፡፡ የሚታዊ ተጋሊያን ጉዞ ወይም ተጋድሎ በሚለው ርዕሰነገር ስር ደግሞ መለየት፣ መነሳሳት እና መመለስ የተሰኙ ሦስት ዋና ዋና ማዕቀፎች የተነሱ ሲሆን፤ በእያንዳንዳቸው ስርም እንደዚሁ ሌሎች ዝርዝር ጽንሰሃሳባዊ ማዕቀፎች ቀርበዋል፡፡ ከዚህ ባሻገር ደግሞ በሁለተኛው እና የቀደምት ጥናቶች ቅኝት በተሰኘው ንዑስ ርዕስ ስር ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የሚዛመዱ አራት ያህል ተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ተደርጎባቸዋል፡፡

## 2.1. የንድፈሃሳባዊ ጽሑፍ ቅኝት

### 2.1.1. ሚት

ሚትን በጥንታዊውም ይሁን በዘመናዊው ባህላዊ ሥርዓት እና ልማዳዊ ሁነት እንዲሁም በተለያዩ የፈጠራ ጥበባት እና ስለተፈጣሯዊ ዓለም ባለን አመለካከት ውስጥ ሁሉ አማካይ ላይ የምናገኘው እሳቤ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ይህ እሳቤ በተለያዩ ማኅበራዊ ልማዶች፣ ስለተፈጥሮ በሚኖረን አመለካከት፣ በሃይማኖታዊ እንቅስቃሴዎች፣ በፈጠራ ሥራዎች እና መሰል ሁነቶች ሁሉ የተዘረጋ የጋራ መስመር ነው ማለት ይቻላል፡፡ ይህ ድንበር የለሽ እና ሁለንተናዊ የሆነ ፅንሰሃሳብ (ሚት) ከጥንታዊ ግሪክ እና ሮማውያን ጀምሮ መተለያዩ የሙያ መስኮች ውስጥ እያደገ የመጣ ወይም በልዩልዩ ዲሲፕሊኖች ሲንጸባረቅ የቆየ እና አሁንም ድረስ የዘለቀ ጥንታዊ ጥበብ ስለመሆኑ የዘርፉ ልሂቃን ያትታሉ፡፡

ሚት ለልቦለድ ደራሲያን፣ ለታሪክ ጸሀፊያን (ተናጋሪዎች)፣ ለጸሐፈተውኔቶች (Dramatists) ወዘተ እንደማነቃቂ እና እናደ ፅንሰሃሳብ መነሻ በመሆን ከማገልገልም ባለፈ በሥነጽሑፍ

ሃያሲያን ዘንድም ጭምር አንድን ሥነጽሑፋዊ ሥራ ለመተንተን ትልቅ አስተዋጽኦ ያለው የሀላዌ መግለጫ ተምሳሌት (Pattern) ነው (Frey፣ 2000)፡፡

Leeming (2002)፣ በአንድ ከባቢያዊ ሃይማኖት እና ባህል ውስጥ የሚኖሩ የማኅበረሰብ ክፍሎች በጋራ የሚስማሙባቸው ባህላዊ፣ ሃይማኖታዊ ወይም እምነታዊ ልማዶች በሌሎች ማኅበረሰቦች ዘንድ ደግሞ እንደሚት ይቆጠራሉ፡፡ በዚህ መሠረት፣ ሁላችንም የእያንዳንዳችንን እና የየባህላችንን ያለፈ ታሪክ እና የዓለምን (Univers) አፈጣጠር እንዲሁም አሁን ላይ ያሉንን ሚታዊ ተግባራት (Mythical consciousness)፣ ስለማንነታችን፣ ስለራሳችን ያለንን ዕውቀት ወይም የራሳችን የሆኑ እና ልዩ የሚያደርጉንን (በልዩነት የምንታወቅባቸውን) ረቂቅ ተግባራት፣ ስለ ቅድመ ዝርያችን፣ እንደዚሁም ስለምንገኝበት መልክዓምድር ወዘተ ሁሉ ለመግለጽ ወይም ለማሳየት ሚት ያስፈልገናል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ሚቶሎጅን ማጥናት እውነተኛ ሁነትን እና ህላዌያችንን ሁሉ በአጠቃላይ (myth_ logic in general) ማጥናት ነው ማለት ይቻላል፡፡ ይህ ሂደትም ባህላችንን፣ ውስጣዊ ማንነታችንን፣ የማወቅ ፍላጎታችንን ወይም ደግሞ ልዩ ባህርያችንን፣ የጋራ እሴቶቻችንን፣ እና አፈጣጠራችንን ወይም ጥንተአመጣጣችንን ለማወቅ ይረዳናል፡፡ ይህ ብቻም ሳይሆን፣ በጋራ እምነት ወይም አመለካከት የሚፈጠር እና በሕይወት ውስጥ ለሚፈጠሩ ሌሎች ምስቅልቅል ገጠመኞች እንደ ማሳለጫነት የሚያገለግል ተምሳሌትም ነው፤ "Myths are created by the collective imagination as metaphorical projections of the way things are in life". (Leeming, 2002; 18)፡፡

እንደ Campbell (2004) ትንታኔ፤ ሃይማኖቶች፣ ፍልስፍናዎች፣ ጥበባት፣ በጥንታዊ እና ታሪካዊ ሰዎች ስብስብ የተመሰረቱ ማህበራዊ ሥርዓቶች፣ በሳይንስ እና ቴክኖሎጅ ውስጥ ያሉ ሁሉም ግኝቶች፣ በእንቅልፍ ውስጥ ያሉ ህልሞች ሁሉ ከመሰረታዊ የሚት ተዓምራዊ ክብ ውስጥ የሚፈሱ ሁነቶች ናቸው፡፡ "ሚት፣ ከዓለም ወደ ሰው ልጆች ባህላዊ ተግባራት በሚፈስሰው እልቆቢስ ኃይል ውስጥ ያለውን ሚስጢራዊ ጉዳይ የመግለጥ ሂደት ነው፤ […] myth is the secret opening through which the inexhaustible energies of the cosmos pour into human cultural Manifestation". (Campbell, 2004; 3)፡፡

Mircea Eliade (1963) ደግሞ፣ ሚት በአማኞች ዘንድ ትልቅ ስፍራ የሚሰጠው እና እንደ እውነተኛ ታሪክ የሚታመን ተረክ ነው፡፡ ይኸውም አስፈላጊ፣ ውድ (precious)፣ ጥሩ አርዓያ የሆነ (exemplary) እና የልዕለተፈጥሮ መሠረት (origin) ያለውን ዓለም እና የሰው ልጅን የህላዌ ታሪክ ይገልጻል በማለት ያትቱታል፡፡ ከዚህ አንፃር ሚት በሰዎች ዘንድ እውነታ ናቸው ተብለው የሚታመኑ እሴቶች መግለጫ እንጅ ሳይንሳዊ ማረጋገጫ የተቀመጠላቸው እና በሙከራ የተረጋገጡ አሊያም ነባራዊ ሐቆችን የሚያወሳ ታሪክ ነው ማለት እንዳልሆነ መገንዘብ ያሻል፡፡ በእርግጥ Sedigheh Sherkat Moghaddam (2016)፣ ሚት ፍጹም ፈጠራ ወይም ደግሞ ሃሰተኛ የሆነ ታሪክ እና ወደፊት ሊሆን የማይችል ምትኃት ሳይሆን ከፍልስፍና ጋር ተያያዥ የሆነ ፅንሰሃሳብ ያላቸውን እና ምክንያታዊ መፍትሔ የማይገኝላቸውን ወይም ሳይንሳዊ ምላሽ የማይሰጣቸውን ጥያቄዎች ለመመለስ የሚያስችል ፅንሰሃሳብ ነው፤ በማለት ይህን ሃሳብ ያጠናክሩታል፡፡ ስለሆነም እንደ ሞት እና ሕይወት፣ ማህበራዊ እና ዓለማዊ ሁነቶች እንዲሁም የሰዎች የሥነፍጥረት ሁሉ አፈጣጠር እና ዕጣፋንታ ወይም የህላዌ ሂደት የመሳሰሉ ጥያቄዎች በሚት ምላሽ እንደሚሰጣቸውም ጨምረው ያብራራሉ፡፡

እንደ Eliade (1963) ሐተታ፣ ሚት ከዓለም ሥርዓት ወይም ከሰዎች እና ከሥነፍጥረት የትመጣነት እንዲሁም ዕጣፋንታ ውጭ የሆነ ጉዳይ አይደለም፤ ይልቁንም በቀላሉ ለመረዳት እና በግለለጽ ለመጠናት (ለመመርመር) አስቸጋሪ የሆኑ እንደ ባህላዊ ሥርዓት፣ እምነታዊ ጉዳዮች፣ ልማዳዊ እሴቶች፣ ሃይማኖታዊ ቀኖናዎች ወዘተ ያሉ ሁነቶችን ፍካሬያዊ የመባያ ጉዳዮችን (internal motives) ወይም አመክንዮዎችን ግልጽ ለማድረግ እና ለመገንዘብ የሚረዳን ፅንሰሃሳብ ነው፡፡

Jaja (2012)፣ Alagoa (1978)ን ዋቢ አድርገው እንደሚያብራሩት፣ ሚት ከሰው ልጅ ያለፈ ወይም የረጅም ጊዜ ድርጊት የተቀዳ እና በሰዎች ዘንድም እውነት እንደሆነ የሚታመን ታሪክ ነው፡፡ ከዚህም ባለፈ፣ ለእያንዳንዱ ማኅበረሰብ እንግዳ (peculiar) የሆነ እና በቃል የሚተላለፍ ታሪካዊ መረጃም ነው፡፡ በአጠቃላይ ግን ሚት፣ በእያንዳንዳቸው አንድን የተወሰነ ክስተት የሚገልጹ ሦስት አይነት ታሪኮችን አካቶ የያዘ ሲሆን፤ እነርሱም፡- የአፈጣጠር ታሪኮች (Stories of origion)፣ ገላጭ ታሪኮች (explanatory stories) እና የግኝት ታሪኮች (didactic stories) ናቸው፡፡ ከዚህ አንፃር ሚት አንድን ማኅበራዊ ወይም

ተፈጥሯዊ ክስተት የመግለጽ ተለምዷዊ ወይም ባህላዊ ታሪክ (traditional story) ነው ማለት እንችላለን፡፡ ሚት ዓለምን እና የሰዎችን ታሪክ የሚገልጽ ታሪክበመሆኑ፤ ሚታዊ ታሪኮች ወይም ሚታዊ ገፀባህርያት የቀደምት ባህሎችን፣ ልማዶችን፣ በጣም ጠቃሚ ናቸው የሚባሉ ክስተቶችን እና እምነቶችን ታሪክ እንደዚሁም የሰው ዘር አመጣጥ መላምትን ይገልጻሉ፤ ያንጸባርቃሉ፡፡ ስለዚህ ሚት የሰዎች የአስተሳሰብ ውጤት ሳይሆን የእውነተኛ ታሪክ ቀጥተኛ ጥርጓሜ ወይም የእውነታ ነፀብራቅ ነው ሊባል ይችላል፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን፣ በመሠረታዊ ምክንያት የማይገለጽ ነገር ግን የእያንዳንዱ የሰው ልጅ ድርጊት ተቀዳሚ ተምሳሌት እና የህላዌው አካልም ጭምር ነው፡፡

በተጨማሪም Moghaddam (2016) ልክ እንደነ Matey (2016) ሁሉ፣ ሚት የተሰኘው ቃል "Muthos" ከተሰኘ የግሪክ ቃል የተወረሰ ሲሆን ፍቺው ደግሞ ንግግር (speech) ወይም ደግሞ ክስተት (event) ማለት እንደሆነ ገልጸው፣ ሚት በመጀመሪያ ደረጃ አንድን እውነት የሚገልጽ ቅዱስ ታሪክ (sacred story) ነው፡፡ ከዚህ አንፃር፣ ሚት የሰዎችን አፈጣጠር (origin) እና አካባቢ  የሚገልጽ ተረክ ነው ማለት ነው፤ በማለት ያትታሉ፡፡ በተለይ ደግሞ Djavadi (2004)ን ጠቅሰው እንደሚያስረዱት፣ በነገረመለኮት ውስጥ የሚትን መነሻ ለመገንዘብ ከሞከርን ስለፈጣሪ ውልደት (አፈጣጠር) ወይም ደግሞ ስለ ዓለም ታሪካዊ ሁነቶች የሚያጠና ሳይንስ ሆኖ እናገኘዋለን፤ በማለት ያክላሉ፡፡

Moghaddam (2016)፣ ሚትን ካለው ባህርይ አንፃር ከእውናዊነት እና ከፈጠራ ታሪክ ጋር በማነፃጸር እንዲህ ይበይኑታል፤ ሚት፣ የታሪክነት ባህርይ ያለው መሠረታዊ እና የተደራጀ ፈጠራ ሲሆን፣ ቀደም ካለው ጊዜ አንስቶ በጋራ እምነት እና ፍላጎት ላይ ተመስርቶ የሚቀርብ ታሪክ ነው፡፡ ሚት ሥነምግባራዊ፣ ሞራላዊ እና ማህበራዊ ጭብጥ ያለው በመሆኑ ሰዎችን ስለማህበራዊ እና ሃይማኖታዊ መርሆዎች የሚያስተምር ተረክ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ሚቶሎጅስቶች ማኅበረሰባቸውን ለማሳየት ከሚፈልጉት አተያይ አንፃር ይለያይ እንጅ ሚት በየትኛውም ጊዜ እና ሁኔታ በማኅበረሰቡ ዘንድ ያለው ተቀባይነት ልክ እንደ እውነተኛ ታሪክ ነው፡፡ እንደ ታሪክ እና ልማዳዊ ድርጊትነቱም መለኮታዊ ኃይልን እና መሠረታዊ እውነታነቱን የሚያስገነዝቡ ተጋዳሊያንን (ጀግኖችን) ያሳትፋል፡፡

በሌላ መልኩ ደግሞ፣ Jung እና Campbell ሚትን ከስነልቦናዊ ጉዳዮች ጋር አያይዘው እንደሚፈቱት Leeming (2002) ከጠቆሙ በኋላ፣ ይኸውም 'ከህልም ጋር የሚነፃጸር እና ልክ እንደ ህልም ሁሉ በአእምሯችን ትልቅ ቦታ የምንሰጠው እውነታ ነው፤ ህልም ደግሞ አስፈላጊ እና ትክክለኛ የሆነ መረጃ በንቁው የአእምሯችን ክፍል አማካኝነት የሚቀርብበት ዘዴ ነው፡፡ ስለዚህ ሚትም እንደዚሁ (እንደ ህልም ሁሉ) በአንድ ማኅበረሰብ ባህል ውስጥ ያለው ምናባዊ ወይም መንፈሳዊ እውነታ የሚቀርብበት ዘዴ ነው'፤ በማለት እንደሚያብራሩም ጨምረው ይገልጻሉ፡፡ ከራሳችን ትክክለኛ ገጠመኝ እንዲሁም በውስጣችን ካለ እምነት ወይም ውስጣዊ ፍላጎት የሚመነጭ እሳቤ በመሆኑ፤ ልክ እንደ ገጠመኞቻችን፣ እንደ ባህላችን እና እንደሚለዋወጠው ዝርያችን ሁሉ አብሮ የሚለዋወጥ እውነታ ነው ማለት እንችላለን፡፡

በመልክዓምድራዊ አቀማመጥም ይሁን በሥነልሳን (በቋንቋ) የሚጎራበቱ ማኅበረሰቦች የሚጋሯቸው መሠረታዊ ታሪኮች እና ሚቶች መኖራቸው የሚያስደንቅ ጉዳይ አይደለም፡፡ ከዚህም በላቀ ሁኔታ፣ በመልክዓምድር ተራርቀው እና በቋንቋ ተለያይተው በሚኖሩ ባህሎች መካከል ሳይቀር የጋራ የሆኑ ባህላዊ ጭብጦች ሊኖሩ የሚችሉበት አጋጣሚም ጥቂት አይደለም፡፡ በአብዛኛው ባህል ውስጥ ስለዓለም ህልውነት እና ስለፈጣሪ የሚያወሱ የጋራ ታሪኮችን እናገኛለን፡፡ በዚህ መሠረት፣ መለኮታዊ ኃይል ያለው እና ዓለምን እንዲሁም በዓለም ላይ ያሉ በርካታ ነገሮችን ሁሉ የፈጠረ፣ የፈጠረውን ፍጡር የሚመራበት እና በተለይም ደግሞ ሰይጣናዊ ስልጣንን የሚቋቋምበት ልዩ አቅም ያለው ወንድ አምላክ የአብዛኛዎቻችን ባህል የሚጋራው ሚት እንደሆነ Dr. Neelam Matey (2016) ያስረዳሉ፡፡ እንደ Matey (2016) ማብራሪያ፣ በእርግጥም ስለዓለም አፈጣጠርም ሆነ ስለፈጣሪው የሚያትቱ ተረኮች ስፍር ቁጥር የላቸውም፡፡

Raymond Pierotti (2017)፣ Bringhurst (2008)ን ጠቅሰው፣ ሚት ሳይንሳዊ ማረጋገጫ የሌላቸው እና በተረክ ብቻ የሚቀርቡ ምልክቶችን ወይም ረቂቅ እና ግዑዛን ነገሮችን (inanimate abstractions) ለመግለጽ የሚያገለግል የትክክለኛ ተፈጥሮ መተንተኛ ቀመር ነው፡፡ በመሆኑም እንደ ሳይንስ ሁሉ ትክክለኛውን እና የመጨረሻውን እውነት የመረዳት እና የመግለጽ ዓላማ ያለው ሆኖ፣ ነገር ግን በጥናት ሊደረስበት የሚችል እና ቴክኒካዊ ትንተናን የሚጠይቅ ሳይሆን ታሪክን ማዕቀፍ ያደረገ መላምት ያለው የሳይንስ እና

የምርምር አማራጭ ሥርዓት ነው፡፡ በየትኛውም ጊዜ እና ባህላዊ ሁኔታ ውስጥ የሚስተዋሉ እንደተፈጥሮ ህግ ያሉ ጉዳዮችን እና ሊጠኑ የሚገባቸው እውነታዎችን ፈጥኖ የመረዳት ሂደት ነው፡፡ Manuel Alejandro Crespo Rodriguez (2019)ም እንዲሁ፣ Campbellን ጠቅሰው፣ ሚት በምርምር ሊረጋገጥ የማይል ወይም ሳይንሳዊ ማረጋገጫ የሌለው በመሆኑ ጥልቅ ትርጓሜ እና ሰፊ ግንዛቤን የሚጠይቅ ታሪክ ነው፤ በማለት ይህን የPierotti (2017)ን ሃሳብ ይጋራሉ፡፡

ሚት በተለይም በጊዜ ቀደምትነት ያላቸውን የዓለም ትክክለኛ እና ሊታወቁ የሚገባቸውን ልዩ ልዩ ተግባራት፣ ቦታዎች፣ ወቅቶች እና አጠቃላይ ሁለንተናዊ ጉዳዮችን ትርጉም ለመፈለግ፣ ለመረዳት እና ለማንፀባረቅ የሚያስችል ሁሉንአቀፍ ፅንሰሃሳብ ነው፡፡ ይሁን እንጅ በዘመናዊያን እሳቤ ደግሞ ትንቢትን፣ ተረትን፣ ሃይማኖታዊ ጽሑፍን (መጽሐፍን)፣ አስማተኛ ተረትን፣ አፈታሪክን፣ የጀግንነት ታሪክን አለፍ ሲልም ማኅበረሰባዊ አሉባልታን (community hearsay) የሚመለከት ጥቅል መጠሪያ እየሆነ የመጣ ይመስላል፡፡ ነገር ግን ዛሬም ድረስ ስለዓለም፣ ስለተጋዳሊያን፣ ስለ ፈጣሪ፣ ስለልዕለተፈጥሮ አካላት እንዲሁም ስለተፈጥሮ እና አፈጣጠር (origion) በሚት ይገለጻል (Jose Manuel Losada፣ 2018)፡፡

በአጠቃላይ፣ ሚት በመንፈሳዊነት እና በእውናዊነት (እውነተኛ ታሪክነት) መካከል የተዘረጋ የጋራ መጓጓዣ መስመር ሲሆን፣ በየትኛውም ስፍራ በሰዎች የየእለት የሕይወት እንቅስቃሴ ውስጥ በእምነቶች (rituals)፣ በህልሞች (dreams)፣ በልማዶች (customs)፣ በሃይማኖታዊ አመለካከቶች ወዘተ አካል ነስቶ የሚገለፅ፤ ነገር ግን ሊዳሰስ ወይም ሊጨበጥ የማይችል (intangible) ሁነት ነው፡፡ ስለሆነም የእያንዳንዱን ግለሰብ ሕይወት የሚመለከት ብቻም ሳይሆን የማኅበረሰቡን የጋራ የሆነ ህላዌ ማንጸባረቂያ ነው ማለት ይቻላል፡፡

የትኛውም የማኅበረሰብ ክፍል የረጅም ጊዜ ታሪክ ያለው ወይም ከጥንት የሚነሳ ባህላዊ ታሪክ የዓለምን አፈጣጠር የሚረዳበት እና የሚገልጽበት የራሱ የሆነ ተረክ ስለመኖሩ አያጠራጥርም፡፡ ይህ አይነቱ የሰዎች አእምሯዊ ምስል ወይም ስለዓለም የትመጣነት ያለው ግንዛቤ በሚታዊ ሂስ ይዳኛል፤ ይመረመራል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ የዘርፉ ልሂቃን "ሚት" ብለው የሚጠሩት ይህንኑ የጋራ የሆነ እምነትን፣ ባህልን፣ ሃይማኖትን፣ ታሪክን፣ ማንነትን ወዘተ የሚገልጽበትን ተረክ ነውና፡፡

ሚት በሳይንሳዊ ምርምር ወይም በሙከራ የማይረጋገጡ ነገር ግን ከሰው ልጅ ህላዌ ጋር በእጅጉ የተቆራኙ እና ከሕይወቱ ጋር የተሰናሰሉ ሁነቶች መግለጫ ነው፡፡ ሳይንሳዊ ትንታኔ የማይሰጣቸው ነገር ግን የማኅበረሰቡ ክፍል አሜን ብሎ የተቀበላቸው እና እውናዊነታቸውን የማይጠራጠርባቸው እንደ ባህል፣ እምነት፣ ሃይማኖት እና መሰል ሥርዓቶች ወይም ልማዶች በሚት ይተላለፋሉ፡፡ ሌላው ትውልድም እንደዚሁ ተቀብሎ በራሱ አረዳድ እና ከራሱ ዘመን ጋር አጣጥሞ ይጠቀምባቸዋል እንጅ ምንም ያህል ቴክኖሎጂካል (የበለፀገ) ቢሆን እራሱን ከሚት ውጭ ሊያኖር ከቶውንም አይችልም፤ በእያንዳንዱ እስትንፋሱ ይህ እውነታ አለና ነው፡፡ የሰው ልጅ ከሚት ውጭ የሆነ ሕይወት የለውም፤ የእያንዳንዱ የሰው ልጅ ህላዌ በሚት የተቃኘ ነው (Matey፣ 2016 እና Jaja (2012)፡፡

የሰው ልጅ ሁልጊዜም በበርካታ ጥያቄዎች ይመሰጣል፡፡ ሥለተፈጥሮ ተዓምራት እና በውል ስለማይታወቁ እና የዓለምን አፈጣጠር ስለሚመለከቱ ነገሮች ይጠይቃል፡፡ ምክንያቱም ለተደበቁ እና በውል ላልታወቁ ነገሮች መፍትሔ መፈለግ ወይም ደግሞ ያላወቁትን የማወቅ ጉጉት የሰው ልጆች ተፈጥሯዊ ባህርይ ነው፡፡ በሌላ አባባል፣ የሰው ልጆች በባህርያቸው በቂ ምላሽ ያላገኙላቸውን ጥያቄዎች ተቋቁመው ለመኖር የሚችገሩ ፍጡራን በመሆናቸው እነዚህን ሳይንሳዊ ምላሽ የሌላቸውን ጥያቄዎች የሚመልሱባቸው ሚቶችን ይፈጥራሉ፤ ለእነዚሁ እራሳቸው ለሚጠይቋቸው ተፈጥሮን የተመለከቱ ረቂቅ ሁነቶች ሁሉ በራሳቸው ሚታዊ ፈጠራ (creation myth) ማብራሪያ ይሰጧቸዋል፤ ምላሽ ያስቀምጡላቸዋል፡፡ ከዚህ አንጻር፣ የሰው ልጅ ሚት ፈጣሪ (myth-making) እንስሳ ነው ማለት ይቻላል (Matey፣ 2016 እና Jaja (2012)፡፡

ሚት ያልተለመደ ፍጥረትን (anonymous origin)፣ ወደ ቀደምት ሰዎች ሳይቀር የተስፋፋ እንደ እውነታ አምነው የሚቀበሉት፣ ልዕለተፈጥሯዊ አካላትን እና ተግባራትን ያካተተ፣ ተፈጥሯዊ አካላት እና ተግባራቶቻቸው ደግሞ በልዕለተፈጥሮ ተወካዮቻቸው ተጽእኖ ሥር ሲወድቁ፣ አሊያም ከልዕለ ተፈጥሯዊ ወኪሎቻቸው ቱርፋቶችን ሲቸሩ የሚያሳይ ታሪክ ነው ማለት ይቻላል፡፡

በመጨረሻም፣ Hartman (2008) ሚት ካለው ባህርይ አንጻር እርስ በእርሳቸው ግንኙነት ወይም ዝምድና ያላቸው በርካታ ትርጓሜዎች እንደሚሰጡት ጠቅሰው፣ በአጠቃላይ ግን

ሰባት ያህል ዋና ዋና ጭብጦችን አስቀምጠዋል፡፡ በዚህ መሠረት፣ እነዚህን ጥቂት ጭብጦች ላስቀምጥ እና ይህንን ንዑስ ክፍል ላጠናቅ፡፡

(1) ሚት እንደ አፈ-ታሪክ (narrative)፣ ሥነጽሑፋዊ ቅርጽ ወይም ደግሞ ኪነጥበባዊ ይዘት በመሆን ያገለግላል፡፡ (2) ስለ ፈጣሪ እና ስለዓለም የሚያወሳ ርዕሰጉዳይ ነው፡፡ (3) ስለ ተፈጥሮ እና አፈጣጠር የሚያብራራ ጽንሰሃሳብ ነው፡፡ (4) ጥንታዊ ሳይንስ ነው፡፡ (5) በመንፈሳነዊነት ላይ መሠረት ያደረገ ጥበብ ነው፡፡ (6) ስለ ዓለም ተጨባጭ እና ጉልህ ማብራሪያ የሚሰጥ፣ ስለ ዕምነት የሚገልጽ እንዲሁም የጋራ ልምድ እና እሴቶችን የሚያትት ጽንሰሃሳብ ነው፡፡ (7) ከተፈጥሮ የላቁ እና የረቀቁ (psychic) ወይም መንፈሳዊ የሆኑ ኃይሎችን የመግለጽ ሂደት ነው፡፡

## 2.1.2. ሚት እና ሥነጽሑፍ

ከላይ በዳራው ክፍል ላይ እንደተጠቆመው፣ ሚት ቀደም ሲል በቃል አማካኝነት የሚተላለፍ ቃላዊ ተረክ የነበረ ቢሆንም፣ በሂደት ግን በመጻሕፍት መልክ በመታተም እና በተለያዩ ጊዜያት ተለዋዋጭ የሆኑ ታሪካዊ ሁነቶች ሳይለወጡ ተጠብቀው እንዲቆዩ በማድረግ የራሱን አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ ይህ በጽሑፍ የሰፈረ ነባር ታሪክ ደግሞ የደራሲ እና የተደራሲ (የተናጋሪ እና የአድማጭ) የሁሉም የጋራ ታሪክ ሲሆን፣ በሃይማት ተቋማት ሳይቀር የምናምነውን እምነት ሁሉ ያካትታል (Moghaddam፣ 2016)፡፡ ከዚህ አንጻር፣ ሚት ለሥነጽሑፍ መጀመር ያበረከተውን አስተዋጽኦ መገንዘብ ይቻላል፡፡

የሚት እና የሥነጽሑፍ ዝምድና በተለያየ መልኩ የሚገለጽ ሲሆን፣ ሚት ለሥነጽሑፍ ሥራ ያለውን ጠቀሜታ የሚመለከተው ጉዳይ ደግሞ ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛል፡፡ ሚት በሥነጽሑፍ ሥራ ውስጥ ለበርካታ ጥንታዊ ወይም ነባር ክስተቶችን በጭብጥነት በስፋት ለማንሳት እንደ ዋና ማዕቀፍ ሆኖ ሲያገለግል የቆየ እና አሁንም ድረስ እያገለገለ ያለ ፅንሰሃሳብ ነው (Segal, 2004)፡፡ ከዚህ ባለፈ ደግሞ፣ ሚት ለራሱ ለሥነጽሑፍ መነሻ ወይም መሠረት በመሆን ያገለገለ እሳቤ ነው፡፡ በእርግጥም ቀደም ባሉት ጊዜያት በቃል አማካኝነት ሲተላለፍ የነበረ እና ቀስ በቀስም ወደ ጽሑፋዊ ጥበብነት እየተለወጠ የመጣ እና ለሥነጽሑፍ ዘርፍ መወለድ ምክንያትም ጭምር እንደሆነ በበርካቶች ዘንድ ይታመናል (Lugli፣ 2014)፡፡

ሚት እና ሥነጽሑፍ እርስ በእርስ ትይዩ የሆነ ግንኙነት ያለቸው ጥበባት ብቻም ሳይሆኑ አንደኛው በሌላኛው ውስጥ የሚገለጽ፣ አንደኛው ይዞት ለተነሳው ሃሳብ ሌላኛው እንደ ማብላያ እርሾ በመሆን የሚያገለግል ከመሆኑም በላይ አብረው የሚቦኩ እና በመጨረሻም አንድ ግዙፍ አካል ይዘው የሚከሰቱ ጥበባት መሆናቸውን እንረዳለን፡፡ በሌላ በኩል፣ በታሪክ ወደኋላ ስንመለስ ደግሞ አንዱ ለሌላው (ሚት ለሥነጽሑፍ) እንደ መነሻ ምንጭ ሆኖ ያገለገለ እና ተዋረዳዊ ዝምድናም ያላቸው ስለመሆኑ ከSegal (2004) እና ከLugli (2014) የጋራ ሐተታ መረዳት እንችላለን፡፡

Hartman (2008) ደግሞ፣ ሚትን ካለው ጠቀሜታ አንጻር እንዲህ ይበይኑታል፡፡ ሚት በሰው ልጆች የእለት ከዕለት ድረጊት እና እንቅስቃሴ፣ እምነት እና አስተሳሰብ ውስጥ ዘልቆ በመግባት ስለ እነዚህ እና ሌሎች ከዓለም በስተጀርባ ስላሉ ሰብዓዊ ስሜቶች እና እንቅስቃሴዎች ሃሳብ የምናቀርብበት ሰፊ ጽንሰሃሳብ ነው፡፡ ስለሆነም የሕይወትን ዝብርቅርቅ ጉዞ ለማስተካከል እና መልክ መልክ ለማስያዝ ያለው ጠቀሜታ ላቅ ያለ ነው፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ሚት ዓለምን አስውቦ እና ኪነጥበባዊ መልክ አላብሶ በሥነጽሑፍ ውስጥ ማደራጀትም ነውና፤ በማለት Hartman በስፋት ያትታሉ፡፡ በዚህ መሠረት የሚት ጠቀሜታ ሲነሳ አንዱ እና ፈጥጦ የሚወጣው እውነት ሥነጽሑፋዊነቱ መሆኑን በቀላሉ እንረዳለን፡፡ ይኸውም የሁለቱን ጉዳዮች ጥበባዊ ግንኙነት ያጎላዋል፡፡

## 2.1.3. ሚታዊ ተጋዳሊ (Mythical Hero)

የሰው ለልጅ ህልው ከሆነበት ዘመን አንስቶ የተጋዳሊያን ገጽታ በቃላዊ ባህሎች (oral traditions)፣ በሥነጽሑፍ እና በሌሎችም የትምህርት ማዕከላት ወይም መገናኛዎች ቀጣይነት ያለው እና ከጊዜ ወደ ጊዜም እየተለወጠ፣ የተለያየ ትርጓሜ እና ባህርይ እየተሰጠው የመጣ ጉዳይ ሲሆን፣ የተጋዳሊው አይነትም እንዲሁ ህልው እንደሚሆንበት ማኅበራዊ ሁናቴ የተለያየ እና ተለዋዋጭ ነው (Simona Klaus፣ 2010)፡፡

ቀደም ባሉት ሚቶች ውስጥ ተጋዳሊያን ይሰጣቸው የነበረው ትርጉም፣ ማንነታቸውም ሆነ ተግባሮቻቸው ከፈጣሪ ወይም ከትልቅ አምላካዊ ኃይል ባህላዊ እሴቶች (cultural goods) የተቀዱ እንደሆኑ እና በወቅቱም ሞራላዊ ፍጹምነት የጎደላቸው፣ የሚፈጽሙት ጀብዱ እና ተጋድሎ ያልተገባ (ነውር)፣ ድርጊቶቻቸው ሰዎች ተመሳሳይ ተግባር እንዳይፈጽሙ እና

መልካም ሥራ እንዴት መስራት እንዳለባቸው እንደማሳያ፣ እንደ ማስፈራሪያ ወይም ማስጠንቀቂያ ተምሳሌትነት የሚያገለግሉ ነበሩ፤ በማለት ያስረዳሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩ L-Jay Fine (1997)፣ ቀደም ባለው አስተሳሰብ መሠረት ተጋዳሊያን እንደ ጦረኛ፣ ጠባቂ፣ ሳይንቲስት፣ የሰለጠኑ (thechnologist)፣ የአንጸባራቂነት መልክ ያላቸው እና የሕይወትን እንቅፋት ሁሉ ብቻቸውን የሚጋፈጡ ተደርገው ይቆጠሩ ነበር፤ በማለት ይገልጻሉ፡፡

እንደ Klaus (2010)፣ ለእነዚህ ተጋዳሊያን አንዱ እና ዋናው መገለጫቸው ዳግም ውልደት ነው፡፡ እንደሚታወቀው የማነኛውም ሰው ዓለማዊ ህላዌ በሞት ይቋጫል፡፡ ይሁን እንጅ እንደእነዚህ አይነት ባህላዊ ተጋዳሊያን (cultural Heroes) የመለኮታዊነት ባህርይ ያላቸው በመሆኑ ህላዌያቸው እንዲሁ እንደማነኛውም ሰው በሞት የሚደመደም ሳይሆን፣ ከሞት በኋላ በሌላ ሕይወት የሚመጡ ናቸው፡፡ ይኸውም ሌሎች ዓለማዊ ሰዎች ያከብሯቸው እና አምነው ይቀበሏቸው ዘንድ እንደ አንድ ዋነኛ ምክንያት ሊሆን የሚችል ተምሳሌታዊ መገለጫ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ፣ ባህላዊ ተጋዳያን በሚት ውስጥ የሚመጡት ሁልጊዜም ከወንድማቸው ጋር በመሆን (ጥንድ መልክ ይዘው) እንደሆነ Davidson (1982)ን ጠቅሰው፣ Klaus (2010) ያስረዳሉ፡፡ እንደ Davidson (1982) ሃሳብ ከሆነ ደግሞ ባህላዊ ተጋዳሊያን በሚት ውስጥ ጥሩ እና መጥፎ የሆኑ ሁለት መልኮች ያሏቸው ሲሆን፣ በአንደኛው ወገን ሰዎችን የሚያግዙ እና የሚረዱ፣ በሌላኛው ወገን ደግሞ በተቃራኒው ሰዎችን የሚጎዱ እና የሚያሳዝኑ ይሆናሉ፡፡ ይህ አይነቱ የተጋዳሊያኑ የጥሩ እና መጥፎ ባህርያት ተቃርኖዎች ወይም ሁለት አይነት መልኮች በየትኛውም ዓለም ሚቶሎጅዎች ውሰጥ ባሉ አማልክት መካከል የሚስተዋል እና ልክ እንደ ወንድ እና ሴት ገፀባህርያት ሆኖ ብቅ የሚል ጉልህ ጉዳይ ነው፡፡

በ20ኛው ክፍለዘመንም ቢሆን ቀደምት ሚታዊ ተጋዳሊያን ፈጽሞ አልሞቱም፤ በዘመናዊ ተጋዳሊያን ቅርጽ ይዘው ቀጠሉ፤ ተሸጋገሩ እንጂ (Klaus፣ 2010፤ Segal፣ 2005ን ጠቅሰው)፡፡ እነዚህ ዘመናዊ የሚባሉት ተጋዳሊያን የመለኮታዊነት ዝርያ ያላቸው ቢሆኑም፤ ቅዱስነታቸው እየቀነሰ እና እየተናቀ መጥቶ ልክ እንደማንኛውም ተራ ሰው (normal

person) ሁሉ ደካማ እና ብዙ ጊዜ ደግሞ የሞራል እሴት ውሱንነት የሚስተዋልባቸው ሆነው በሥነጽሑፍ ውስጥ የሚገኙበት አጋጣሚ ቀላል እንዳልሆነም Klaus ያትታሉ፡፡

ወደ 21ኛው ክፍለ ዘመን ስንመጣ ግን የቴክኖሎጂ መሻሻል ምዕራፍ ሚታዊ ተጋዳሊያንንም ወደ አዲስ ዓለማዊ ሕይወት እንደመራቸው እና እዚህም-እዚያም ብቅ-ብቅ ማለት እንደጀመሩ ወይም በቀጥታ መከሰት እንዳበዙ Klaus (2010) ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ አንጻር በዚህ ወቅት ባሉት ሚቶች ውስጥ የምናገኛቸው ተጋዳሊያን በሰዎች እና በቅዱሳን መካከል ያለውን ክፍተት የሚቀንሱ እና የሚያጠቡ ከመሆን አልፈው፣ የመለኮት ትክክለኛ መገለጫ ተደርገው ይታዩ የነበሩ አምላካዊ ባህርያት እንደተቀየሩ እና በምስለ አምላክነት (virtual Gods) ባህርያት እንደተተኩ ይገልጻሉ፡፡

ቴዎድሮስ (2001) በበኩላቸው፣ በነባሩ ወይም በባህላዊው የሚት ሥርዓት (ልማድ) ውስጥ ተጋዳሊነት የአማልክት ስጦታ ነበር፡፡ በአዲሱ ወይም በዘመናዊው ልማድ ውስጥ ደግሞ እያንዳንዱ ሰው በገዛ ጥረቱ እራሱን ለተጋዳሊነት የሚያበቃ እጩ ተጋዳሊ ነው፤ በማለት ያስረዳሉ፡፡

ሚታዊ ተጋዳሊ በዘወትር ከሚኖርበት አካባቢ፣ ጎጆ ወይም መጠለያ በአንዳች ነገር ተማርኮ፣ ለአንዳች ዓላማ ተነሳስቶ፣ አሊያም በፈቃደኛነት (በገዛ ፈቃዱ) ተመርቶ አንዳች የጀግንነት ሥራ (ጀብዱ) ለመፈጸም ሲል ወደ ሌላ አዲስ ቅጽር እና ያልለመደው ስፍራ እንዲሁም ወደ አስቸጋሪ ትግል የሚገባ ነው፡፡ በዚህ ሂደት ደግሞ የመሸጋገሪያ መንገዱን ለመዝጋት የሚታትሩ በርካታ አይነት ያላቸውን ተጻራሪ ኃይላት ተቃውሞ ይፋለማል፤ ከፊቱ ላይ የሚደቀነውን ድቅድቅ ጨለማ ይጋፈጣል፤ የሚሉት ደግሞ፣ Campbell (2004) ናቸው፡፡

እንደ Campbell (2004) ማብራሪያ፣ ሚታዊ ተጋዳሊ ከዘወትራዊው ዓለም እና ከእያንዳንዱ መደበኛ ቀን ተነስቶ ወደማይታወቅ እና የልዕለተፈጥሮ አካላት ወደሚገኙበት ግዛት በአደጋ ውስጥ የሚገሰግስ፣ በሂደቱ ውስጥም ይህ ነው የማይባል ኃይል ሊያጋጥመው የሚችል፤ ነገር ግን በዚህ ኃይል ሳይበገር ድልን የሚቀዳጅ እና በስተመጨረሻም ከዚህ ምስጢራዊ ዓለም ውስጥ ታላቅ ጀብዱ በመፈጸም ታላቅ ድልን እና ደስታን ይዞ ወደ ማኅበረሰቡ (ወደ ቀደመው ነባር ግዛቱ) የሚመለስ አካል ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ሚታዊ

ተጋዳሊ፣ የማይሞከሩ በሚመስሉ ነገሮች ውስጥ በመግባት አስቸጋሪ ተግባራትን ለመፈጸም እና አብዛኛውን ጊዜ ደግሞ ሰዎች ደህንነት መስዋዕት ለመሆን ቁርጠኛ እና መልካም ፈቃደኛ የሚሆኑ፣ ጀግና እና ከተራው ሰው ላቅ ያሉ ሰዎች ናቸው፡፡ በአብዛኛው ተጋዳሊያን የራስ ነጸብራቅ፣ ለእኔ ብለን ተስፋ የምንጥልባቸው ሁነኛ ሰዎች እና ዝነኛ ተምሳሌት እንደሆኑ ይታመናል፡፡

ተጋዳሊ ሁልጊዜም በዘወትራዊው ዓለም ውስጥ በቤቱ፣ በቤተሰቡ፣ በባህሉ ወዘተ ደስተኛ ያልሆነ እና ከተለመደው ሕይወት የተሻለ ነገር የመፈለግ ልማድ ያለው ነው፡፡ በዚህ የአዲስ ህላዌ ፍለጋ ሂደት ውስጥም ወደሚታዊ ተጋድሎ የሚጠራ፣ ከማኅበረሰቡ በመነጠል ወደሌላ የማይታወቅ ምድር እና ወደ አዲስ ቦታ በመጓዝ የሚታወቅ ነው (Hartman & Zimberoff, 2009)፡፡

"ተጋዳሊ የሚባለው ለራሱ ዝና፣ ክብር እና ደህንነት ሲል ለተጋድሎ ጉዞ የሚነሳ ሳይሆን፣ ከራሱ ይልቅ ሌሎችን መጠበቅን ብቸኛ ዓላማው ያደረገ አካል ነው፤ The hero is someone who embarks on the journey without regard for personal safety, but embarks the journey only to save others" (Hunter, 2007; 31)፡፡ ተጋዳሊ ዋነኛ ግቡ እውነትን እና መልካምነትን ማግኘት የሆነ እና ለዚህም ብዙ መስዋዕትነትን የሚከፍል አካል ነው (Binford, 2011)፡፡ በዚህ መሠረት የአንድ ተጋዳሊ የመጨረሻ ግብ እራሱን ማዝናናት አሊያም አንድን አካል ማስፈንደቅ ሳይሆን፣ መድኃኒት መሆን፤ አንዳች ጥበብን፣ እውቀትን፣ መለካም ነገሮችን ወዘተ ለሌሎች ማቅረብ ወይም ማሳየት ነው ማለት ይቻላል፡፡

Klaus (2010)፣ Campbell (2004)ን ጠቅሰው ተጋዳሊያን ከፈጣሪ እና ከፈጣሪ ጋር ከሚጋጩ ሌሎች መናፍስት (anti-gods) ቀጥሎ በሚቶሎጅካል ተረክ ውስጥ እንደዋነኛ ገፀባህሪ ሆነው የምናገኛቸው አካላት ናቸው፡፡ እነዚህ ተጋዳልያን ደግሞ ሁልጊዜም ማለት ይቻላል፤ በጾታ ወንድ የሆኑ እና የተሻለ ብልሀት (cunning) ያላቸው፣ የሰውነት ጥንካሬ ያላቸው እና ኃይለኛ የሆኑ እነደሆኑ ይታመናል፡፡ እንደ Campbell (2004) ሃሳብ ደግሞ፣ እነዚህ ሚታዊ ተጋዳሊያን በአብዛኛው በከፊል የሰውነት እና የአምላካዊነት (Demigods)

ባህርይ ያላቸው ሲሆኑ፤ ተጋዳሊነታቸውም ቢሆን የሚረጋገጠው ወይም የሚታወቀው ገና በወጣትነት ዕድሜያቸው ላይ ነው፡፡

## 2.1.4. የሚታዊ ተጋዳሊያን ጉዞ ወይም ተጋድሎ (The Adventure of the Hero)

አንድ ተጋዳሊ ጉዞ የሚያደርገው ከአንድ የተወሰነ ግዛት ወደሌላ ሰፊ እና ያልተገደበ ወይም ደግሞ በርካታ አማራጮች ወደሚገኙበት ዓለም ነው፡፡ ዋነኛ ዓላማው ደግሞ ወደተጋድሎው መዝለቅ እና ከፍተኛ ክብርን (ማዕረግን) ማግኘት፣ ለልዑልነት (ለልዕልትነት) መብቃት፣ ለመድኃኔ ሕይወት መታጨት፣ ለራስ ያለን ስሜት ማሳደግ፣ ለመልካም ዕሴቶች ነጸብራቅ ለመሆን መታደል ነው (Hartman & Zimberoff፣ 2009)፡፡

በእርግጥ፣ በዚህ መካከል ተጋዳሊያኑ ኪሳራ ሊገጥማቸው፣ ህልማቸው ከንቱ ሊቀር፣ ያልተጠበቁ ምርጫዎችን ሊመርጡ እና በተቃዋሚዎቻቸው ሊሸነፉ ይችላሉ፡፡ ይሁን እንጅ አብዛኞዎቹ ተጋዳሊያን መልካም ጸጋዎችን ይዘው ወደ ቀድሞ ማኅበረሰቦቻቸው በመመለስ ለቤተሰቦቻቸው፣ ለአካባቢያቸው እና ለማህበረባህላቸው ሊያጋሩ የሚታደሉ ሲሆን፣ ሌሎቹ ደግሞ ከዚህ በተቃራኒው ለዳግም ፈተና ይሆን ዘንድ ተጨማሪ ተጋድሎ ሊታከልላቸው ይችላል፡፡ ይህ የተጋዳሊያን የጉዞ ታሪክ ደግሞ ሰዎች በሕይወት ዘመናቸው ውስጥ የሚያጋጥሟቸውን እንቅፋቶች በውጤታማነት እና በስኬት እንዴት ማለፍ እንዳለባቸው ብሎም ትልቅ እና የተሸለ ድልን እንዴት መቀዳጀት እንደሚችሉ የማስተማር ጠቀሜታም አለው፡፡

አብዛኛውን ጊዜ አንድ ተጋዳሊ በሕይወት ዘመኑ ቢያንስ አንድ ጊዜ አሊያ ደግሞ ለበርካታ ጊዜ ለተለያየ ዓላማ ጥሪ ይደረግለታል፡፡ ከሚደግፈው ሃይል ጎን ለመቆም፣ ለትልቅ እና ለተሸለ አብርሆት፣ የነገሮችን እውናዊነት ለማረጋገጥ ወይም እውናዊ ነገሮችን ለማግኘት፣ ተወዳጅነትን ይዞ ለመመለስ እና ለመሰል ዓላማዎች ሚታዊ ጉዞ ያደርጋል (Campbell፣ 2004)፡፡

እምነት ወይም መንፈሳዊነት ደግሞ የተጋዳሊ ጉዞ አንዱ አካል እና ዋነኛ መገለጫው ነው፡፡ በየትኛውም ማኅበረሰብ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ ወደአዲስ የሕይወት ደረጃ ሲገቡ እራሳቸውን ለማስቀጠል እና ለማሸጋገር የሚያስችላቸውን ዕምነት

ይጀምራሉ፡፡ የእነዚህ እምነቶች ዓላማ እና ትክክለኛ ውጤት ደግሞ በሕይወት ውስጥ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ የሚያጋጥምን አስቸጋሪ ጉዳይ ለማለፍ እና አስቸጋሪ በሚመስሉ አጋጣሚዎች ውስጥ ሁሉ ሕይወትን ማሸጋገር ነው (Fine፣ 1997)፡፡

ሚታዊ ጉዞ ሁልጊዜም አልጋባልጋ አይሆንም፤ ይልቁንም በብዙ ፈተናዎች የተሞላ፣ በበርካታ ተቃዋሚዎች የታጀበ፣ መልከ ብዙ መከራዎችን ያዘለ ወዘተ በመሆኑ የአካልም ሆነ የመንፈስ ጥንካሬን በእጅጉ የሚጠይቅ ተግባር ነው፡፡ ተጋዳሊ ጉዞውን ለመግታት ከፊቱ ላይ የሚገተሩትን ደንቃራዎች በኃይል በመደርመስ አሊያም ደግሞ በማታለል፣ በመደራደር ወይም በመስማማት እና በመግባባት ወደተነሳበት ዓላማ ዘልቆ ለመግባት ቅጽሩን ያልፋል፤ ወደውስጠኛው እና ይበልት ጨለማ ወደሆነው ግዛት ይገሰግሳል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ገና ከቅጽሩ መግቢያ ጀምሮ በተቃራኒ እና ተቃዋሚ ወገኖች ወይም በተጋድሎው አጨናጋፊዎች አማካኝነት ስቃይን፣ የድብደባ ውርጅብኝን፣ አሰቃቂ መወገርን ከፍ ሲልም ሞት እና ስቅለትን የሚያስተናግድ ይሆናል (Campbell፣ 2004)፡፡

እንደ Campbell (2004) ሐተታ፣ ከተጋድሎው ቅጽር መግቢያ ቀጥሎ፣ ተጋዳሊው ምንም በማያውቀው እና ፍጹም እንግዳ በሆነ ዓለም ውስጥ እና በሚስጥራዊ ኃይላት መካከል ጉዞውን ሲከውን፣ አንዳንዶቹ ኃይላት ፈተና ያቀርቡለታል፤ ይመዝኑታል፤ በሚገባ ይለኩታል፤ በውል ይመረምሩታል፡፡ ከዚህ በተቃራኒው ደግሞ ሌሎቹ አካላት ተዓምራዊ እርዳታቸውን፣ ያላሰለሰ ድጋፋቸውን እና ጽኑ ምርኩዝነታቸውን ይቸሩታል፤ ከክፉ ነገር ነቅተው ይጠብቁታል፤ ውጣውረዱን ያሳልጡለታል፤ ለጉዞው ስንቅ ይሆኑት ዘንድ ለድል የሚያበቁትን ዘዴ እና ብርታትን ያለመሰልቸት ይለግሱታል፡፡

ወደ ዋናው እና ተስፋ አስቀራጭ፣ እልህ አስጨራሽ ወደሆነው የተጋድሎ ዙር ላይ ሲደርስ መራር የሆነ ስቃይን እና በኋላም የስቃዩ መካሻ ሽልማትን በአንድ ላይ ያገኛል (Campbell፣ 2004)፡፡ ከዚህ አንጻር ይህ ክፍል ሃዘን እና ደስታ፣ ክፉ እና ደግ፣ ስቃይ እና ተድላ፣ መራራ እና ጣፋጭ፣ ውድቀት እና ስኬት ወዘተ የመሳሰሉ ፍጹም ተቃራኒ ገጠመኞች በአንድ ላይ ተቃይጠው የሚገኙበት ሆደሰፊ ክፍል ነው ማለት ይቻላል፡፡ ከዚህ ክፍል ውስጥ የሚገኘው ድል ደግሞ ተጋዳሊው፣ የምድር እናት (*the Mother of earth*) ተብላ ከምትታወቀው እንስት ጣኦት (አምላክ?) ባለው ጾታዊ ውህደት (*sexual unity*)

ወይም ሃይማኖታዊ ጋብቻ፣ ስለምህረት አድራጊነቱ ወይም ስለፍጡራን አባትነቱ (*The father-creature*)፣ ስለመለኮትነቱ ወይም ስለአዳኝነቱ ባለው እውቅና ይገለጻል፡፡

ከዚህ ሁሉ በኋላ የተጋዳሊያኑ የመጨረሻው ተግባር የሚሆነው መመለስ ነው፡፡ ተጋዳሊው በልዕለ ተፈጥሮ ኃይላቱ ከተባረከ ሁልጊዜም ቢሆን በእነርሱ ጥበቃ እና ከለላ ስር ይኖራል፤ ይህ ካልሆነ ደግሞ ጉዞው ሁሉ በመሰናክል የተሞላ እና አሁንም ቢሆን በኃይላቱ ክትትል ስር የወደቀ ይሆናል፡፡ ከመመለሻው ቅጽር ላይ ደግሞ ከሚያስፈራው ግዛት ለመውጣት እና ለመመለስ አሁንም ቢሆን የልዕለተፈጥሮ ኃይል ከጎን ሊኖር ይገባል፡፡ ይህ የተጋዳሊያን ጉዞ (ተጋድሎ) በድል መመለስ እንደ ዳግም ትንሳኤ፣ ከሞት በኋላ የተገኘ ሕይወት እና ታላቅ ቅድስና ነው፡፡ ይህ ቅድስና እና ምርቃት ደግሞ ከተጋዳሊያኑም አልፎ ለተመለሱለት ዓለም ሁሉ የሚተርፍ ትሩፋት ነው (Campbell፣ 2004)፡፡ ምክንያቱ ደግሞ እንደ Campbell ሃሳብ፣ ተጋዳሊው ከተጋድሎው ሲመለስ መድኃኒትን ወይም አዳኚነትን (elixir) ይዞ ይመለሳልና ነው፡፡ በተሰጠው ቅድስና እና ባርኮት፣ በተገለጠለት ምስጢር፣ የቀድሞውን እና አሁን በድጋሜ ተመልሶ የመጣበትን ዓለም ከክፉ ነገር ይጠብቃል፤ ከስቃይ ያድናል፤ ከህመም ይፈውሳል፤ ከኃጢዓት ያነጻል፡፡

Hartman & Zimberof (2009)፣ በሥነተረክ ውስጥ የምናገኛቸው ተጋዳሊያን ጉዞ በአምስት ዋና ዋና ደረጃዎች (stages) ዙሪያ እንሚሽከረከር ያብራራሉ፡፡ እነዚህ ደረጃች ደግሞ ጥሪ፣ ለጉዞ መዘጋጀት፣ ጉዞ፣ አንዳች ጸጋ ማግኘት እና መመለስ እንደሆኑም ሃሳባቸውን አስቀምጠዋል፡፡

Campbell (2004) በበኩላቸው፣ ከዚህ በላይ በጥቂቱ የቀረበውን የሚታዊ ታጋዳሊያን የተጋድሎ ጉዞ ጠቅለል ባለ መልኩ መለየት (Departure)፣ መነሳሳት (Initiation) እና መመለስ (Return) በሚል በሦስት ዋና ዋና ደረጃዎች መድበዋቸው እናገኛለን፡፡ እነዚህን ዋና ዋና ክፍሎችም ቢሆን ወደተለያዩ ንዑሳን ርዕሰጉዳዮች ከፋፍለው ያስቀምጧቸዋል፡፡ ቴዎድሮስ (2001)ም እንደዚሁ፣ ይህንኑ የCampbellን ሃሳብ ዋቢ በማድረግ፣ በሚት ሥርዓት ውስጥ የተጋዳሊው ዕጣ የሚጓዝባቸው መለየት፣ መዝለቅ እና መመለስ የሚሉት ሦስት ፈለጎች እንደሆኑ ጠቅሰው፣ ሁሉንም ምዕራፎች የሚያማክለው እና ሁሉንም ጉዳዮች

ጠቅሎ የያዘው ደግሞ "መለየት" የተሰኘው ክፍል እንደሆነ በመግለጽ የጽሑፋቸው ዋነኛ ትኩረት እንዳደረጉት ያትታሉ፡፡

በዚህ ጥናት ውስጥ ደግሞ እነዚህ የCampbell (2004) ዋነኛ የሚታዊ ተጋዳሊያን የተጋድሎ መንገዶች እና ንዑሳን ክፍሎች ደግሞ እንዳስፈላጊነታቸው (ለዚህ ጥናት ካላቸው አስፈላጊነት አንጻር) ተለይተው ከዚህ ቀጥሎ ቀርበዋል፡፡

## 2.1.4.1. መለየት

በሚት ሥርዓት ውስጥ መለየት ቀዳሚው የተጋድሎ ጉዞ ደረጃ ሲሆን፣ ሚታዊ ተጋዳሊያን ለወትሮው የሚኖሩበትን ቤት፣ ቤተሰብ፣ ማኅበረሰብ፣ አካባቢ ወዘተ ለቅቀው ወደሌላ ያልተለመደ እና እንግዳ የሆነ ስፍራ የሚሄዱበትን ሁኔታ ይመለከታል፡፡ እንደ Hartman & Zimberoff (2009)፣ መለየት ለፍተኛ ማዕረግ ለመታጨት፣ ለልዑልነት (ለልዕልትነት) ለመብቃት፣ ለሌሎች ዓለማዊ ማኅበረሰቦች መድኃኔ ሕይወት የሆኑ ለመሆን፣ ለራስ ያለን ስሜት ለማሳደግ፣ ለነባሩ ማኅበረባህሎቻቸው የመልካም ዕሴቶች ነጸብራቅ ለመሆን ወዘተ ከአንድ የተወሰነ ዘወትራዊ ዓለም ወደሌላ ሰፊ እና ያልተገደበ ወይም ደግሞ በርካታ አማራጮች ወደሚገኙበት ግዛት መሄድ ነው፡፡ ይኸውም ወደተጋሎ መጠራት (The call to Adventure)፣ ጥሪን አለመቀበል (Refusal of the call)፣ የልዕለተፈጥሮ ዕርዳታ (Supernatural aid) ፣ የመጀመሪያውን መግቢያ በር ማለፍ (The crossing of the first Threshold) እና የዓሳ ነባሪ ሆድ (The Belly of the whale) የሚሉ አምስት ዝርዝር የጉዞ ሂደቶችን አካቶ ይይዛል (Campbell፣ 2004)፡፡ በዚህ መሠረት እነዚህ አምስት ዝርዝር ጽንሰሃሳባዊ ጉዳዮች እንደሚከተለው ሰፋ ባለ መልኩ ተብራርተው ቀርበዋል፡፡

### 2.1.4.1.1. ወደ ተጋድሎ መጠራት

አንድ ተጋዳሊ ለአንድ ለሆነ ዓላማ በአንዳች ኃይል ታጭቶ ከሚኖርበት ቤት፣ አካባቢ እና ማኅበረሰብ እንደሚለይ ከፍ ሲል ጠቁሜያለሁ፡፡ ተጋዳሊያኑ ለገድል ከታጩ በኋላ ደግሞ ጥሪው በተለያየ መንገድ ይቀርብላቸዋል፡፡ ይህን አይነቱን ለተጋድሎ መጠራት ደግሞ የዘርፉ ምሁራን "የገድል ጥሪ" በማለት ይጠሩታል፡፡

የትኛውም ተጋዳሊ ጉዞውን (ተጋድሎውን) የሚጀምረው በራሱ ውሳኔ አሊያም ደግሞ በሌሎች ተምሳሌቶች በሚደረግለት ጥሪ ነው፤ በተለይም ደግሞ "ለተጋድሎ መጠራት" ከጉዞ መጀመር ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት አለው (Fine፣ 1997)፡፡ ሁሉም ለተጋድሎ የሚጠሩ (ጥሪ የሚደረግላቸው) ተጋዳሊያንም ቢሆኑ ፍጹም የሆነ ማንነት የላቸውም፡፡ በተጋዷቸው ሊያገኙት እና ሊያሻሽሉት ወይም ደግሞ ወደ ተጋድሎ የመጡበት አንዳች እንከን ይኖርባቸዋል፡፡ ነገር ግን በሁሉም ልብ ውስጥ ማለት ይቻላል፤ መሠረታዊ የሆኑ መልካም እና የሚቀርብላቸውን ጥሪ ለመቀበል የሚያስችሉ ውስጣዊ ስሜቶች ይኖሯቸዋል (Hunter፣ 2007)፡፡

የገድል ጥሪው ለተጋዳሊያኑ ከሚደርስባቸው መንገዶች መካከል ደግሞ ዕድል ወይም ዕጣ (destiny) አንዱ እንደሆነ Campbell (2004፣ 53) በግልጽ አስፍረውት እናገኛለን፡፡ ከዚህ አንጻር፣ አንድ ተጋዳሊ ከሚኖርበት ማኅበረሰብ እና ከለመደው አካባቢ በአጋጣሚ ተነስቶ ወደ ሌላ ያልታወቀ እና እንግዳ ወደሆነ ስፍራ ሊሄድ ይችላል፡፡ ስለዚህ ነባር መኖሪያውን ትቶ በአጋጣሚ ወደ ሌላ ስፍራ የሄደ ሁሉ ድንገት ስለሆነ ለተጋድሎ አልተጠራም ማለት አይቻልም ማለት ነው፡፡

በሌላ መልኩ ደግሞ፣ የተጋሎ ጥሪ የሚደረገው አንድም በራሱ በተጋዳሊው ፍላጎት እና ውሳኔ፤ አንድም ደግሞ በሌሎች እረቂቅ ተምሳሌቶች አማካኝነት እንደሆነ ከፍ ሲል ከተቀመጡት የFine (1997) እና የCampbell (2004) ማብራሪያዎች በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከእነዚህ መካከል የመጀመሪያውን ያየን እንደሆነ፣ አንድ ተጋዳሊ በሚኖርበት ዓለም ውስጥ ፈልጎ ያጣው ወይም ተመኝቶ ያላገኘው ነገር ካለ፣ ይህ የሚፈልገው ነገር ይገኛል ብሎ ወደሚያምንበት ስፍራ በገዛ ፈቃዱ እና ፍላጎቱ ነባሩን ዓለም ትቶ ይሰደዳል፡፡ በዚህ ወቅት የራሱ እምነት እና ፍላጎት እንደ አንድ የጉዞ ማንቂያ ደወል፣ የ "ተነሳ ሂድ!" ጥሪ ሆኖ ቀስቅሶታል ማለት ነው፡፡

ጠቅለል ባለ አገላለጽ፣ ሚታዊ ተጋዳሊያን ተጋድሏቸውን የሚጀምሩት በአንዳች የተጋድሎ ጥሪ ሲሆን፤ ይኸውም ከዕድል፣ ከአጋጣሚ፣ ከራሱ ከተጋዳሊው የገዛ ፍላጎት ወዘተ ጥሪው ሊመነጭ ይችላል፡፡ ተጋዳሊያን በአንዳች እርግማን ወይም ቁጣ (curse) ምክንያት ወደሌላ እንግዳ (የማይታወቅ) ስፍራ ለጥገኝነት ሲሸሹ፣ የተሻለ ነገር ፍለጋ ሲሰደዱ፣ ከዓለም ምቾት እና እረፍት ሲነጠሉ፤ አሊያም ባላቸው የአካል ብቃት እና የመንፈስ

ብርታት በአንድ ሃይል አማካኝነት ሆነ ተብሎ ለተጋድሎ በመመረጥ የሕይወት ተጋድሏቸውን ይጀምራሉ፡፡ ታዲያ እነዚህ ሁሉ ነገሮች የተጋድሎ ጥሪ ተምሳሌቶች ናቸው ማለት ነው፡፡ ሲመረጡም ቢሆን የማይሞቱ፣ በዓለም ላይ በርካታ ሰዎችን የማግኘት ዕድል የተቆረጠላቸው እና ከሚያገኟቸው ዓለማውያን ወይም ተጻራሪ ኃይላት ጋር ፍልሚያን በብቃት መከወን የሚችሉ እንደሆኑ ሲታመንባቸው ነው፤ (Niels Schollaert፣ 2015)፡፡

> ሕልም እና ራዕይ ተዘውታሪ የጥሪ ማድረሻ፣ ለገድል የመቀስቀሻ መንገዶች ናቸው፡፡ በሕልም እና በራዕይ ጥሪው በዝርው እንዳለ ሊቀርብ፣ አሊያም በሌሎች ነገሮች ተወክሎ በተዕምርትነት ሊመጣ ይችላል፡፡ ጥሪው በየትኛው መንገድ ይገለጥ፣ በየትኛውም ሁኔታ ይምጣ፣ ከጥሪው ጀርባ ግን ብዙውን ጊዜ የልዕለ ተፈጥሮ ኃይል እጅ አለ፡፡ የተጋዳሊው ዕጣ ከመነሻው የተቆረጠ ነውና፣ ይህ ኃይል አስቀድሞ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ (ቴዎድሮስ፣ 2001፤ 6)፡፡

## 2.1.4.1.2. ጥሪን አለመቀበል ወይም "እምቢኝታ"

እንደሚታወቀው፣ "እመቢኝታ" አንድን ድርጊት ወይም ተግባር ለመፈጸም አሊያም በአንድ አካል የሚቀርብን ትዕዛዝ ለማክበር፣ ካለመፈለግ የሚመነጭ አሉታዊ የሆነ ግብረመልስ ነው፡፡ ይህ አሊታዊ ግብረመልስ ደግሞ እራስን ቀድሞ ካለማዘጋጀት፣ በራስ ካለመተማመን፣ የራስን ዕውቀት እና ብቃት ከድርጊቱ በላይ ወይም በታች አድርጎ ከማሰብ፣ ከክፋት፣ ካለማወቅ ወዘተ ሊመነጭ ይችላል፡፡ እንግዲህ ያም ይሁን ይህ፣ እምቢኝታ በሚታዊ ታሪኮች ውስጥ ሁለት መልኮች ይኖሩታል፡፡

እንደ Campbell (2004) ሃሳብ፣ በሚት ሥርዓት ውስጥ በአብዛኛው ጥሪን አለመቀበል የተጋዳሊውን ጉዞ እና አጠቃላይ ህላዌ ማለት ይቻላል፤ ወደ አሉታዊ አኳኋን ይለውጣል፡፡ ምክንያቱም ጥሪው በራሱ መመረጥ ወይም ቅድስና ነውና፡፡ ስለዚህ ተጋዳሊው በቸልተኛነት፣ በብርቱ ሥራ በፍርሃት ወይም ደግሞ በባህላዊ እሴቶች በመታጠር እና በሌሎችም መሰል ምክንያቶች ሳቢያ የሚቀርብለትን ጥሪ ከገፋ ታላቅ የሆነውን አዎንታዊ ተግባር ያጣ እና ወደ ጥቃት አለፍ ሲልም ወደሞት ይመጣል፡፡ አሊያም ደግሞ፣ እያንዳንዱ የሚሰራው ሥራ በራሱ ላይ አዲስ እንቅፋት እና ችግርን ይወልድ እና የራሱን ውድቀት እየተጠባበቀ እንዲኖር ያደርገዋል፡፡

በሌላ በኩል ግን ጥሪን አለመቀበል አስፈላጊ የሚሆንበት ጊዜ እንደሚኖርም አያጠራጥርም፡፡ አንድ አካል ወደራሱ ጥቅም እና ፍላጎት ለመውሰድ የሚያደርገው ጥሪ

ይኖራል፡፡ ይህ የሌላ ወገን ጉትጎታ እና ግፊት ደግሞ ተጋዳሊውን አለመጥቀም ብቻም ሳይሆን ጥቅሙን የሚያሳጣ እና በቅድስና ፋንታ ወደ እርኩሰት የሚመራ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ ይህን አይነቱን ወደ አንድ ወገን ጥቅም ወይም ፍላጎት የሚያመራ መስመር መበጠስ እና መውጣት አሊያም ለአንድ አካል ፍላጎት የሚመጣን ጥሪ እምቢ ብሎ ማቋረጥ ከጉዳቱ ይልቅ ጠቀሜታው፣ ከዕርግመቱ ይልቅ ቅድስናው ይጎላል (Campbell፣ 2004)፡፡

“በተለምዶ፣ የልዕለተፈጥሮ ኃይል እረዳታ ያላቸው ተጋዳሊያን የተጋድሎ ጥሪን በመቀበል ይታወቃሉ፡፡ በእርግጥም ጥሪው በራሱ አንዱ ለቅድስና መቀስቀሻ ደወል ነው፤ The hero to whom such a helper appears is typically one who has responded the call.The call, in fact, was the first announcement of the approach of this initiatory priest”. (Campbell፣ 2004፤ 67)፡፡

## 2.1.4.1.3. የልዕለ ተፈጥሮ ዕርዳታ

ከዚህ ከፍ ሲል የገድል ጥሪን እና ጥሪ አለመቀበል የሚሉትን ጉዳዮች አንስተናል፡፡ ጥሪው በዕድል ወይም በአጋጣሚ ሊደርስ እንደሚችል ሁሉ የልዕለተፈጥሮ እርዳታም እንዲሁ በውል በማይታወቅ መልኩ (unconsciously) አብሮ ሊበረከት እንደሚችል Campbell ያስረዳሉ፡፡

ልዕለተፈጥሮ አካላት ደግሞ በግብርም ሆነ በሁለንተናዊ ማንነት ከተራው ሰው የተለዩ እና ላቅ ያሉ ናቸው፡፡ ለተጋዳሊያን ሲከፋቸው አጽናኝ፣ ሲደክሙ አበርች፣ የገነትን በር የሚጠቁሙ፣ በአጠቃላይ ከእናት ማህጸን አንስተው የሚያውቋቸው በመሆናቸው፤ ተጋዳሊያኑ የተነሱበትን ዓላማ፣ ያለፈ ህላዌያቸውን እና አሁን ላይ ያሉበትን ሁኔታ ሁሉ ያለማቋረጥ እና ያለመታከት ይደግፋሉ፡፡ ድጋፋቸው ደግሞ ተጋዳሊው አደጋ እንዳይደርስበት ቀድመው በማስጠንቀቅ፣ ከአደጋ የሚያመልጥበትን መፍትሔ በማስታጠቅ እንዲሁም በአካል ከተጋዳሊው ጋር ሆኖ ከጠላቶቹ ጋር ፊት ለፊት በጋፈጥ የሚገለጽ ይሆናል፤ (ቴዎደወሮስ፣ 2001)፡፡

በተመሳሳይ መልኩ፣ ተጋዳሊያን ለተጋድሎ ጉዟቸውን ሲጀምሩ ገና ከመጀመሪያው ቅጽር ጀምሮ አደጋ ሊያጋጥማቸው፣ ሕይወታቸው ላይ ስጋት ሊደቀንባቸው እና አጠቃላይ

ማንነታቸው ሊበጠበጥ ይችላል፡፡ ነገር ግን አንዳች ጠባቂ ኃይል በልባቸው እንኳን ሳይቀር አብሯቸው ይኖራል፤ አሊያም ደግሞ ከማያውቁት እና አዲስ ከሆነው የዓለም ባህርይ ውስጥ እነዚሁ ምንም የማይሳናቸው ደጋፊ ልዕለተፈጥሮዎች በግልጽም ሆነ በህቡዕ ከጎናቸው ሆነው ሁኔታውን ሁሉ ያላምዷቸዋል፤ ክፉን ያለዝቡላቸዋል፤ ተቃዋሚያቸውን ይማርኩላቸዋል፤ ሲጠሯቸው ይደርሱላቸዋል፤ ሲያምኗቸው ከክፉ ነገሮች ሁሉ በታማኝነት ይከላከሉላቸዋል፤ ሲጨነቁ ያጽናኗቸዋል፡፡ በዚህ ሁሉ ሂደት ተጋዳሊያኑ እስካመኗቸው ድረስ የዕርዳታ እጃቸውን ያለመሰሰት ይዘረጉላቸዋል፤ በድካማቸው ጊዜ ብርቱ ምርኩዝ ይሆኗቸዋል፤ በጨለማው ውስጥም ብርሃን ይፈነጥቁላቸዋል (Campbell፣ 2004)፡፡

የቀረበላቸውን ጥሪ የሚቀበሉ ተጋዳሊያን በአብዛኛው በጉዟቸው ጅማሬ ላይ በተጋድሏቸው ወቅት የሚያጋጥሟቸውን አስፈሪ እና አደገኛ ኃይላትን ለማለፍ የሚያስችሉ ረዳት ወይም ጠባቂ አካላት ይቸሯቸዋል፡፡ እነዚህ ጠባቂ አካላት ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ በጥቂቱም ቢሆን በዕድሜ ገፋ ባለች አረጋዊት (a little old crone) እና በወንድ አረጋዊ (old man) ይመሰላሉ (Campbell፣ 2004)፡፡ እነዚህ ኃይላት ደግ (ገር) ባህርይ ያለቸው የተጋዳሊውን ዕድል ጠባቂዎች ናቸው፡፡

ተጋዳልያን በአንዳች ተዓምራዊ ኃይል እርዳታ አስፈሪውን እና ትልቅ የሚባለውን ኃይል ሁሉ የማሸነፍ አቅም ይኖራቸዋል፡፡ ይኸው ምትሃታዊ ኃይል ደግሞ በጣም አስፈላጊውን ሚና የሚጫወት ከመሆኑ የተነሳ የሚያጋጥማቸውን እንቆቅልሽ ለመፍታት እና የሚገዳደራቸውን ኃይል ሁሉ ለማሸነፍ ያግዛቸዋል (Klaus፣ 2010)፡፡

## 2.1.4.1.4. የመጀመሪያውን መግቢያ በር ማለፍ

ተጋዳሊው ገና ከተለመደው ዓለም ተለይቶ ወደ መጀመሪያው የተጋድሎ ቅጽር መግቢያ በር እንደደረሰ በጣም ኃይኛ፣ አስፈሪ እና አደገኛ የቅጽሩ ጠባቂዎች (Guardians) ይጠብቁታል፡፡ እነዚህ ጠባቂዎች በአብዛኛው በአደገኛ አውሬ (Dragons) የሚመሰሉ ሲሆን፣ አስፈሪ እና አስደንጋጭ ቅርጽም ይኖራቸዋል፡፡ ገና ከመግቢያው የተጋዳሊውን ቁርጠኛነት፣ ውሳኔ እና ጥንካሬ በመፈተን እና በመመዘን ለጉዞው ያዘጋጁታል፡፡ እነዚህን ዘቦች አልፎ እንደገባ ግን በራሱ (በቀድሞ) ግዛቱ እና ተጋድሎውን በሚፈጽምበት ዓለም

መካከል የተዘረጉ እምነቶች፣ ክብረበዓላት እና ልዩ ልዩ ሥርዓተባህሎችን የማግኘት ዕድል ይኖረዋል (Hartman & Zimberoff፣ 2009)፡፡

በሚት ውስጥ ተጋዳሊያኑ በጉዟቸው ወቅት ከጅማሮው አንስቶ መንገዳቸው ሁሉ አልጋባልጋ (ምቹ) እንደማይሆን ከፍ ሲል ተጠቁሟል፡፡ ዋናው ፈተና ደግሞ የሚጀምረው ከዚሁ ከቅጽሩ መግቢያ በር ጀመሮ ነው ማለት ይቻላል፡፡ በመሆኑም የሚታደሉት የልዕለተፈጥሮ እርዳታ እና ምክር ወደ መጀመሪያው ቅጽር በሚገቡበት ወቅት ከሚያጋጥሟቸው ጠባቂዎች አንስቶ በጉዟቸው ወይም በተጋድሏቸው ውስጥ ወደፊት እስከሚያጋጥሟቸው ጉልህ እና አደገኛ ኃይላት ድረስ ሊዘልቅ ይገባል፡፡ በሌላ አገላለጽ፣ ተጋዳሊያኑ ከዘወትራዊው ዓለም ተለይተው ወደማያውቁት ዓለም ለመሸጋገር ጉዟቸውን በሚጀምሩበት ወቅት ነባሩን እና አዲሱን ግዛት ያያያዘውን ድልድይ ለማለፍ ከነባሩ የተሻለ ጥበብ ወይም የአንዳች ልዕለተፈጥሮ ኃይል እርዳታ ያሻቸዋል ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም ገና ከጅምሩ ዙሪያውን የታጠረ፣ የመግቢያ በሩ በኃይል የተከረቸመ፣ ድልድዩ የተዘጋ አሊያም መተላለፊያው ሁሉ በአደገኛ አጥር እና በኃይለኛ ጠባቂዎች የተከለለ ሊሆን ይችላልና ነው፡፡

እንደ Hunter (2007) እና Campbell (2004) ገለጻ፣ የተጋዳሊያን የጉዞ (የተጋድሎ) ጥሪ ሁልጊዜም ጉዞውን ወደጨለማ ከሚመራ አደገኛ ነገር ጋር ተዋህዶ ይቀርባል፡፡ ተጋዳሊያን የሚቀርብላቸውን ጥሪ ተከትለው ለተጋድሎ ጉዞ ሲጀምሩ፣ ከፊታቸው ጨለማ ሊያጋጥማቸው ይችላል፡፡ ጨለማ ደግሞ አንዱ የተጋዳሊያን ፈተና እንጅ ብቸኛው አይደለም፡፡ ይልቁንም ከፊታቸው ቀድሞ የማያውቋቸው ሌሎች ጠንካራ እንቅፋቶች ይኖራሉ፡፡

ጨለማ በማይታወቅ እና አደገኛ ወይም አስፈሪ ነገር (የሚመሰል) የሚገለጽ ሲሆን፤ የተጋዳሊውን ጉዞ በእንቅፋት የተሞላ በማድረግ እንዲሁም በመሻገሪያ መንገዱ ላይ ጥቁር ጥላውን በማጣላት ጀግንነቱን እና አዕምሮውን በከፍተኛ ሁናቴ የሚፈታተን ነው፡፡ በሌላ አባባል፣ የተጋዳሊያንን ጉዞ ጨለማ በማድረግ መንገዱ እንደልብ እንዳይታያቸው፣ እንደፈለጉ እንዳይረግጡ፣ እንዳሻቸው እንዳይዘሉ የሚያደናቅፍ እንቅፋት ሁልጊዜም ከፊታቸው አይጠፋም፡፡ ስለሆነም ይህን ጨለማ በዳበሳም ይሁን በአንዳች ጭላንጭል ታግዘው ማለፍ እና ከወገግታው ደማቅ ብርሃን ለመድረስ የተጋዳሊያኑን ትዕግስት፣

ቁርጠኛነት እና ብርታት በእጅጉ ይጠይቃል፡፡ ይህ ሳይሆን ሲቀር ግን ተጋድሏቸው ከንቱ ውጤታቸውም ኪሳራ ይሆናል፡፡

የጠባቂዎቹ ሚናም ይህንን ታላቅ የድል አድራጊነት ዓላማቸውን ማክሸፍ ነውና፣ ተጋዳሊያን ቅጽር ጠባቂዎችንም ሆነ ቀጥሎ የሚመጣውን የመንገድ ላይ አሜከላ ጥሶ ማለፍ፣ ጉዳትን አስተናግዶም ቢሆን አገግሞ መነሳት እና ድል ነስቶ ወደፊት መገስገስ፣ አባጣ ጎባጣውን ማቅናት፣ ቆሻሻውን መጥረግ፣ አሜከላውን መንቀል ግድ ይላቸዋል፡፡ ቆስሎ መነሳትን፣ አለመበገርን፣ ሃያል የሚመስልን ኃይል ድል የማድረግ ስነልቦናን መፍጠር እና ጠንካራ የአካል ብቃት መገንባት ይጠበቅባቸዋል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ፣ ተጋዳሊያን ወደተጋድሎው ቅጽር ለመግባት በሩን ሲረግጡ ወይም ገና ጉዟቸውን ሲጀምሩ በአራቱም አቅጣጫ እንዲሁም በላይ እና በታች የተጋድሎ አድማሳቸውን ወይም የጉዞ ዓላማቸውን ለመወሰን በንቃት የሚጠብቁ ዘቦች ይኖራሉ፡፡ ከእነዚህ ጠባቂዎች ባሻገርም እንደ ድቅድቅ ጨለማ፣ በግልጽ የማይታወቁ ሌሎች ነገሮች፣ አደገኛ ግለሰቦች፣ ሕፃናት፣ ቤተሰቦች፣ አሊያም ማኅበረሰቦች እንዲሁም የማኅበረሰብ አባላት (ጎሳዎች) እና የመሳሰሉት ነገሮች ከተጋዳሊያኑ ፊት ለፊት ሊጋረጡ እና ጉዞውን ሊያደናቅፉ የሚችሉ እንቅፋቶች ናቸው፡፡ ይህ ተዓምራዊ የሆነ የመጀመሪያው ቅጽር መግቢያ በር፣ በአሳነባሪ ሆድ ለሚመሰለው እና እንደ ዓለማዊ ማሕፀን ለሚቆጠረው እንዲሁም ለዳግም ውልደት ተጋዳሊያኑን ለሚጸንሰው አዲስ ግዛት መዝለቂያ ወይም ደግሞ መሸጋገሪያ ነው (Campbell፣ 2004፤ 71)፡፡

## 2.1.4.1.5. የአሳነባሪ ሆድ

ተጋዳሊያን በመጀመሪያው ቅጽር መግቢያ በር ያጋጠሟቸውን ኃይላት ድል አድርገው ወይም ስምምነት ፈጥረው ካለፉ በኋላ ወደ ሌላ እንግዳ እና የማይታወቅ ሥፍራ ይሰርጋሉ፡፡ በዚህ ውስጥም እንዲሁ እስከ ሞት ሊያደርስ የሚችል አጋጣሚ ሊደቀንባቸው ይችላል፡፡

ይህ እንግዳ እና አዲስ ስፍራ ደግሞ በርካታ ጸጋዎችን (treasures) እና አደገኛ ተፋላሚዎችን በአንድ ላይ አካቶ የያዘ እንደሆነ ይታመናል፡፡ በዚህ መልኩ ሁለት ተቃራኒ ጉዳዮችን በአንድ ላይ አዋህዶ የያዘ ቦታ ደግሞ፣ በሩቅ አገር፣ በጥቅጥቅ ደን (ጫካ)፣

ከምድር በውስጥ ወይም ከሰማይ በላይ ባለ ግዛት፣ ሁልጊዜም የተለየ እና አዲስ መልክ ያለው እንዲሁም የተለያዩ ፍጡራን መገኛ (መኖሪያ) በሆነ ቦታ፣ ባልተለመዱ እና ባልተጠበቁ ስቃዮች፣ በልዕለሰብ ተግባራት እና እንግዳ በሆነ ብርሃን ይገለጻል ወይም ይወከላል (Campbell፣ 2004)፡፡

## 2.1.4.2. መነሳሳት

ሚታዊ ተጋዳሊያን ከተጋድሎው የመጀመሪያ ቅጽር መግቢያ ቀጥሎ በሚገበቡባቸው አዳዲስ እና ፍጹም እንግዳ በሆኑ ግዛቶች ውስጥ የሚያደርጉት የተጋድሎ ጉዞ በሚስጥራዊ ተጻራሪ ኃይላት የታጀበ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለሆነም አንዳንዶቹ ኃይላት ፈተና ያቀርቡላቸዋል፣ ይመዝኗቸዋል፣ በሚገባ ይለኳቸዋል፣ በውል ይመረምሯቸዋል፡፡ ከዚህ በተቃራኒው ደግሞ ሌሎቹ አካላት ተዓምራዊ እርዳታቸውን፣ ያላሰለሰ ድጋፋቸውን እና ጽኑ ምርኩዝነታቸውን ይቸሯቸዋል፣ ከክፉ ነገር ነቅተው ይጠብቋቸዋል፣ ውጣውረዱን ያሳልጡላቸዋል፣ ለጉዟቸው ስንቅ ይሆኗቸው ዘንድ ለድል የሚያበቋቸውን ዘዴዎች ያስታጥቋቸዋል፡፡ በርካታ አይነት ያላቸው ጸጋዎች እና ፈታኝ የተጋድሎ እንቅፋቶች በአንድ ላይ ይቀርቡላቸዋል፡፡ በዚህ ጊዜ የሚያገኟቸውን በረከቶች በተሻለ ለማብዛት እና የተጋድሏቸውን የመጨረሻ ጽዋ ለመጎንጨት ሲሉ የበለጠ ወደፊት ይገሰግሳሉ፣ ለተጨማሪ ድል እና ተክህኖ ወደ ውስጥ ለመዝለቅ ይነሳሳሉ፣ (Campbell፣ 2004)፡፡

እንደ Campbell (2004) ሐተታ፣ ይህ መነሳሳት የተሰኘው ዓብይ የተጋድሎ ጉዞ ደረጃ የምርመራ መንገድ (The Road of Trials)፣ ከእንስት ጣዖት ጋር መገናኘት (The meeting with Goddess)፣ ሴትነት እንደማሳሳቻ ፈተና (Woman as the Temptress)፣ ከፈጣሪ ጋር መታረቅ (Atonement with the Father)፣ መድኃኔ ህላዌ (Apotheosis) እና የመጨረሻ ባርኮት ወይም ምርቃት (The Ultimate Boon) የሚሉትን ስድስት ዝርዝር ሂደቶች አቅፎ የያዘ ነው፡፡ በዚህ መሠረት በዚህ ጥናት ውስጥ የምርመራ መንገድ፣ ከእንስት ጣዖት ጋር መገናኘት እና ሴትነት እንደማሳሳቻ ፈተና የሚሉት ሦስቱ ዝርዝር ሂደቶች ብቻ ለዚህ ምርምር ካላቸው አስፈላጊነት አንጻር ተመርጠው ከዚህ ቀጥሎ ጽንሰሃሳባዊ ቅኝት ተደርጎባቸዋል፡፡

### 2.1.4.2.1. የምርመራ ወይም የሙከራ መንገድ

ሚታዊ ተጋዳሊያን የመጀመሪያውን ቅጽር መግቢያ በር ከተሻገሩ በኋላ ወደ አዲስ እና ወደተመኙት መልክዓምድር እንዲሁም አወዛጋቢ የሆነ ቅጽር ወዳለው ስፍራ የሚንቀሳቀሱበት ምዕራፍ ነው፡፡ በዚህ ግዛት ውስጥም እንደዚሁ ተጋዳሊያኑ የሚደረግባቸውን ምርመራ ወይም የሚቀበሉትን የሙከራ ፈተና በብቃት መወጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከዚህ ባለፈ ደግሞ ይህን ፈተናቸውን ተከትሎ የሚመጣውን ነገር ለመቋቋም እራሳቸውን የበለጠ የሚያዘጋጁበት ክፍልም ነው፡፡

እንደ Campbell (2004) ሃሳብ፣ ይህ ምዕራፍ ለሚታዊ ተጋዳሊያን የተሻለ ወሳኝ እና ተመራጭ ምዕራፍ ነው፡፡ ስለሆነም ትግላቸውን ከዳር ለማድረስ ወደዚህ ግዛት ከመግባታቸው አስቀድሞ በአንዳች ምስጢራዊ ልዕለተፈጥሮ እገዛ፣ ምክር እና ክታብ (amulet) ወዘተ መታጀብን፣ መሸፈንን ወይም መከለልን ይጠይቃቸዋል፡፡ በሌላ አባባል፣ በዚህ የሙከራ ክፍል ውስጥ ምንጊዜም ቢሆን ከአደጋ የሚጠብቃቸው እና የማይለያቸው እንዲሁም ማለፊያውን ከሚዘጋባቸው ጠባቂ የሚያሳልፋቸው ጠንካራ አለያም ከጠባቂዎች ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ኃይል ያለው የልዕለሰብዕ ድጋፍ ያሻቸዋል ማለት ነው፡፡

### 2.1.4.2.2. ከእንስት ጣዖት ጋር መገናኘት

ይህ የተጋድሎ ሂደት ለተጋዳሊያኑ ከሁሉም የላቀ እና ተስፋ ከሚያስቆርጥ ወይም ከሚያሳዝን እንዲሁም ከፍተኛ ከሆነ ችግር ጋር የሚፋጠጡበት፣ እስከቻሉት የምድር ጫፍ ወይም እስከ ዓለም ማዕከላዊ እምብርት ድረስ የሚዘልቅ እና ትልቁ የልቦና አዳራሽ የሚጨልምበት፣ የአምልኮ ቅዱስ ቦታዎች ሁሉ ሊዘጉ የሚችሉበት እጅግ ውስብስብ እና በችግር የተሞላ ተጋድሎ የሚከወንበትን ስፍራ የሚመለከት ነው፡፡ "ሁሉንም የሚያጋጥሙትን መሰናክሎች እና ቀሳፊ ጭራቆች ድል ያደረገ የመጨረሻ ተጋዳሊ ነፍሱ ሁሉ በረቀቀ መንገድ ወይም በጸሎት በውስብስቡ ዓለም ውስጥ ከምትገኝ እንስት ጣዖት ጋር እንደተጋባች ይቆጠራል፤ The ultimate adventure, when all the barriers and ogres have been overcome, is commonly represented as a mystical marriage of the triumphant hero-soul with the Queen Goddess of the World" (Campbell፣ 2004፤ 100)፡፡

እንደ Campbell ሃሳብ፣ ይች እንስት ጣዖት ደግሞ እጅግ በውስብስቡ የተጋድሎ ዓም ውስጥ የሚገኙ ሁሉንም ነገሮች የምታውቅ ስትሆን፤ ተጋዳሊው ደግሞ ለማወቅ ወደዚህኛው ዐለም የዘለቀ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ ስለሆነም በዚህ ግዛት ውስጥ የሚገጥሙትን ፍጹም ያልተጠበቁ እና ያልታሰቡ እንቅፋቶችን ይወጣ ዘንድ ታግዘዋለች፤ ትመራዋለች፤ ያልተጠበቀ የድል አድራጊነት ስሜትን ታላብሰዋለች፡፡

## 2.1.4.2.3. ሴትነት እንደ መሳሳቻ ፈተና

ከዓለም እንስት አማልክት ጋር የሚፈጠር ሚታዊ ጋብቻ ለሚታዊ ተጋዳሊያኑ ትልቁ የሕይወት እውቀታቸው ተደርጎ ይታሰባል፡፡ እንስቶቹ በሕይወት ይመሰላሉ፤ ተጋዳሊያኑ ደግሞ ይህንን ሕይወት በሚያውቅ እና ዋና የዕውቀት ባለቤት በሆነ አካል ይወከላል፡፡ ለተጋዳሊያኑ በቅድሚያ የሚሰጣቸው የመጨረሻ ፈተና ወይም መመዘኛ እና ተጋድሎ፣ የአዕምሮ ንቁነቱን የሚያጎሉ እና እንስቶቹን ወይም የወደፊት ሴት ሙሽራዎችን የሚቃወሙ አካላትን ሙሉ በሙሉ የመቋቋም ችሎታን የሚጠይቁ ሆነው ይቀርቡላቸዋል (Campbell፣ 2004፤ 111)፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥም የገዛ እራሳቸውን ከአባትነት ወንድ አማልክትነት ቦታ ላይ ሆነው ያገኙታል፤ በሌላ አባባል፣ አባት (ወንድ አምላክ) እንደሆኑ ያውቃሉ፡፡

## 2.1.4.3. መመለስ

ተጋዳሊያን ያጋጠሟቸውን ፈተናዎች እና መሰናክሎች ጨርሰው ወደማህበራቸው (ወደ ቀድሞ ቤተሰቦቻቸው፣ አካባቢያቸው፣ ማኅበረሰባቸው እና ግዛታቸው) ሲመለሱ ምዘናዎቻቸውን የተወጡባቸው እና የተመለሱባቸው መንገዶች በእያንዳንዱ ሚት እና ታሪክ ልዩነት ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም አንዳንድ ጊዜ ከሚከተሏቸው ኃይላት በመሸሽ፣ በልዕለተፈጥሮ አካላት ዕርዳታ፣ እንዳንድ ጊዜም በሁኔታዎች መመቻቸት (ሁኔታዎች በራሳቸው ሲፈቅዱ)፣ ወደ ቀድሞ መኖሪያቸው ይመለሳሉ፡፡ ይሁን እና ሲመለሱ በአካል፣ በዕድሜ፣ በስነልቦና እና በመሳሰሉት ማንነቶቻቸው ላይ ለውጥ ሊኖር ይችል፡፡ በተጋድሏቸው ወቅት ባጋጠሟቸው ሳንካዎች ምክንያት በዕድሜ ገፍተው (አርጅተው)፣ ከቀድሞ የተሻለ አስተዋይ እና አዋቂዎች ሆነው፣ በአካላቸው ጠንክረው፣ ከበፊቱ የበለጠ ጠቢብነትን ተክነው ወዘተይመለሳሉ (Hunter፣ 2007)፡፡

እንደ Hunter (2007) ማብራሪያ፣ ተጋዳሊያን በሕይወታቸው ውስጥ ከሚያጋጥሟቸው አስደሳች እና የህላዌ ምሉዕነት ልምዶች ባሻገር ሌሎች እንደ ደስታ እና ሃዘን፣ ብርሃን እና ጨለማ፣ ማግኘት እና ማጣት፣ ስቃይ እና ተድላ፣ ወዘተ የሕይወት አስቀያሚ እውነቶችንም አምኖ መቀበል ይጠበቅባቸዋል፡፡ ምክንያቱም፣ ሚት የሰዎችን ሁኔታ እንዲሁም የዓለምን እኩይ እና ሰናይ ወይም መልዓካዊ እና ሰይጣናዊ ዕሴቶች በግልጽ አሊያም በህቡዕ ለሰው ልጆች ያስተምራል፤ የሕይወት እውነትን ይገልጣልና ነው፡፡

ተጋዳሊያን በጉዟቸው ውስጥ የሚገጥሟቸውን ፈተናዎች በብቃት ጨርሰው (አልፈው) ከተመለሱ የዕድገት፣ የብርሃን እና የአዲስ ዕውቀት ምልክት ወይም መገኛ ምንጭ ይሆናሉ፡፡ በሚታዊ ሥነጽሑፍ ውስጥ የምናገኛቸው ተጋዳሊያን ሁልጊዜም በአካል ብቃት ጠንካራ ባይሆኑ እንኳን ብልጦች፣ ጠቢባን እና በስነልቦናም ጽኑዎች ሊሆኑ ይገባል፡፡ ምክንያቱም ይህ አይነቱ የተጋዳሊያን ክህሎት እጅግ አስፈላጊ እና በተጋድሏቸው ወቅት ድልን ለመቀዳጀት የሚያስችል በመሆኑ ነው፡፡ ሁሉም የተጋዳሊያን ፈተናዎችም ቢሆኑ ጥንካሬ (ኃይል) ብቻ አይጠይቁም፤ ይልቁንም ልክ እነደ አካላዊ ጥንካሬ ሁሉ አስተዋይነት፣ ሩህሩህነት፣ የማሰብ እና ፈጥኖ የመረዳት ችሎታ ከተጋዳሊያኑ የሚጠበቁ እና ወሳኝ የሆኑ ባህርያት ናቸው (Hunter፣ 2007)፡፡

ተጋዳሊያን መኖሪያ ግዛታቸውን ወይም ቤታቸውን ሲለቁ በባህርያቸው የዋህ፣ ገራገር፣ ቂል (በአስተሳሰብ፣ በአመለካከት እና በዕውቀት በውል ያልበሰሉ) ሆነው ሊሆን ይችላል፤ ከተጋድሎ በኋላ ግን በጉዟቸው ባጋጠሟቸው ፈተናዎች (መሰናክሎች) ሳቢያ በዕውቀት በስለው፣ የተሻለ ጠቢብ ሆነው፣ በዕድሜ ትልቅ ሆነው፣ በአካል እና በመንፈስ ጠንክረው እንዲሁም የተሻለ አስተሳሰብ እና አመለካከት ይዘው ይመለሳሉ፡፡ ይሁን እንጅ ተጋዳሊያኑ በጉዟቸው ወቅት ምናልባትም ሕይወታቸውን አደጋ ላይ ሊጥል የሚችል (ለከፋ አደጋ የሚያጋልጥ) የተለያየ አይነት አካላዊ ወይም አዕማሯዊ እንቅፋት ከፊታቸው ላይ ሊደቀንባቸው ይችላል፡፡ ይሁን እና በስተመጨረሻ ከፍተኛ ዋጋ ያለው ሽልማት እና ጥሩ ተስፋ ይዘው ይመለሳሉ፤ (Hunter፣ 2007 እና Campbell፣ 2004)፡፡

እንደ Campbell ሃሳብ በዚህ መመለስ በተሰኘው እና የመጨረሻው የተጋዳሊ ጉዞ ደረጃ ውስጥ መመለስ አለመፈለግ (Refusal of the Return)፣ ተዓምራዊ በረራ (The Mgic Flight)፣ ካለታሰበ ነገር ማዳን (Rescue of Without)፣ የመመለሻውን በር ማለፍ (The

Crossing of the Return Threshold)፣ *የሁለት ዓለማት ገዥነት* (Master of the Two Worlds) *እና የመኖር ነፃነት* (Freedome to Live) *የሚሉት ስድስት የጉዞ ሂደቶች ይገኛሉ፡፡ ታዲያ ከእነዚህ መካከል በዚህ ክፍል ውስጥ ንድፈሃሳባዊ ቅኝት የተደረገባቸው የሚከተሉት ሦስቱ ብቻ ናቸው፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ከፍ ሲል በተደጋጋሚ እንደተነሳው፣ ከዚህ ጥናት ዓላማ ጋር ካላቸው ቅርበት አንጻር መሆኑን ልብ ይሏል፡፡*

## 2.1.4.3.1. *መመለስ አለመፈለግ*

*ሚታዊ ተጋዳሊያን በተጋድሎ ጉዟቸው ውስጥ የተለያዩ የተጋድሎ ዓለማትን በተሻገሩ ቁጥር የልፋታቸውን እና ሲጓጉለት የቆዩትን የፍላጎታቸውን ዋጋ ማግኘት ይጀምራሉ፤ የሚያገኙት በረከትም እንዲሁ ከፍ እያለ እና እየጨመረ ይመጣል፡፡ ታዲያ ቀድሞውንም ቢሆን ወደ ተጋድሎ አገባባቸው፣ በተጋሏቸው ወቅት የሚያገኟቸውን ትሩፋቶች ለሌሎችም ለማጋራት ነውና፤ ከዚህ ሁሉ ውጣውረድ የሞላበት የትግል ጉዞ በኋላ መጀመሪያ ወደ ተነሱበት ዘወትራዊ ዓለም መመለስ ይጠበቅባቸዋል፡፡*

*ተጋዳሊያን ከምንጩ ዘልቀው በመግባት፣ በአንዳች ሴትም ሆነ ወንድ፣ ሰውም ሆነ እንሰሳ እንዲሁም ሌሎች እንደ ሰው የሚቆጠሩ ሕይወት አልባ ግዑዛን ነገሮች ወይም አማልክት ምህረት፣ ጸጋ እና በረከት ረጅሙን እና ጥልቁን የዕውቀት እና የእውነት ፍለጋ ሲጨርሱ፤ ከተለወጠው ህላዌያቸው አሊያም የቀድሞ ሕይወታቸውን እና ማንነታቸውን ከለወጠው ሽልማታቸው ጋር ወደ ቀድሞ ግዛታቸው ሊመለሱ ይገባል፡፡* “WHEN the hero-quest has been accomplished, some male or female, human or animal, personification, the adventurer still must return with his life-transmuting trophy” (Campbell፣ 2004፤ 179). *ይሁን እንጅ አንድ ተጋዳሊ ይህንን ተልዕኮ ችላ በማለት አንዳች በረከት እና ምህረትን ይዞ ወደ ቀድሞው ፈለክ* (planet)፣ *አካባቢ፣ ሥርዓተማህበር ወዘተ ይዞ የማይመለስ አሊያም በዚያው በተጋድሎው ዓለም ውስጥ የሚቀር ከሆነ፤ መመለስ አልፈለገም ወይም ደግሞ “እምቢ” አለ ማለት ነው፡፡*

*ከዚህ አንፃር መመለስ አለመፈለግ ልክ እንደ “ጥሪን አለመቀበል” ሁሉ ከአንድ ግዛት ወጥቶ ወደ ሌላ ግዛት ለመሄድ ፈቃደኛ አለመሆን ተደርጎም ሊወሰድ ይችላል፡፡ ከላይ በጥቂቱ እንዳየነው፣ “ጥሪን አለመቀበል” ማለት ወደ ተጋድሎ ለመሄድ አለመፍቀድ ማለት*

ሲሆን፣ ይህ መመለስ አለመፈለግ (መመለስን አለመቀበል)ም እንዲሁ ከተጋድሎው ዓለም ወጥቶ ወደ ነባራዊው ዓለም ለመመለስ ፈቃደኛ አለመሆን ማለት ነው፡፡

ተጋዳሊያኑ ወደ ነባሩ ግዛታቸው መመለስ የማይፈልጉበት የየራሳቸው የሆኑ ምክንያቶች ይኖሯቸዋል፡፡ ባገኟቸው በረከቶች አለመርካት እና ተጨማሪ በረከት መፈለግ፣ እራሳቸውን በበለጠ ለማብቃት መሻት፣ በተጋሎው ዓለም መማረክ፣ ሌላ ታላቅ ተክህኖ ፍለጋ ወዘተ ተጋዳሊያኑ መመለስ ከማይፈልጉባቸው ምክንያቶች ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉ ጉዳዮች ናቸው፡፡

## 2.1.4.3.2. ተዓምራዊ በረራ

ተጋዳሊያን በስኬታቸው ወቅት የእንስት አማልክትን (ጣዖታትን) ወይም የፈጣሪን ባርኮት ካገኙ በኋላ ከጸጋዎቻቸው ጋር ወደዓለም እና ወደ ማኅበረሰባቸው ለመመለስ በግልጽ ከወሰኑ በኋላ የመጨረሻው ደረጃ የሚሆነው ደግሞ በሁሉም የልዕለተፈጥሮ ጠባቂዎች መደገፍ (መታገዝ) ነው፡፡ የተጋዳሊያኑ ሽልማት አሁንም በድጋሜ በተቃዋሚዎች ከተያዘ ወይም የተጋድሎው ተቃዋሚዎች ካገኙት አሊያም ደግሞ የተጋዳሊኑ ወደ ዓለም የመመለስ ፍላጎት ፈጣሪን ወይም ሌሎች ሰይጣናዊ መናፍስትን ቅር የሚያሰኝ ከሆነ፣ በመጨረሻ ደረጃ ሚታዊ ዙሪቱ በኃይል የተሞላ (Lively) እየሆነ እና አብዛኛውን ጊዜ ደግሞ አስቂኝ መልክ ይዞ አሊያም ተከታታይ እየሆነ ይመጣል፡፡ ታዲያ ይህ በረራ ደግሞ ተጨባጭ ባልሆነ፣ ተዓምራዊ እና ድንቅ በሆነ መሰናክል ሊወሳሰብ ይችላል (Campbell፣ 2004)፡፡

## 2.1.4.3.3. የመመለሻውን በር ማለፍ

የሰው ልጅ እና መለኮታዊ ኃይል (divine) የተሰኙት ሁለት ቃላት የተለያዩ ጽንሰሃሳቦች እንደሆኑ ይታሰብ ነበር፡፡ እንደ ሕይወት እና ሞት፣ ብርሃን እና ጨለማ፣ ቀን እና ማታ ወዘተ የተለያዩ ተደርገው ይቆጠራሉ፡፡ የፈጣሪ ግዛት ከምናውቀው ዓለም ውጭ የሆነ እና የተረሳ ሰፈራ ነው፡፡ ወደደም ጠላም ይህንን ግዛት መፈለግ ደግሞ የአንድ ተጋዳሊ ሁለንተናዊ ተግባር ነው፡፡ ወደ ዓለም ለሚመለስ ተጋዳሊ የመጀመሪያው ችግር የነፍስ ደስታ የማግኘት ራዕያቸውን ካሳኩ በኋላ ያለፉባቸውን የሕይወት ደስታ እና ሃዘን፣ ተራ እና ውስብስብ፣ መልኮችን እንደ እውነት መቀበል ነው (Campbell፣ 2004)፡፡

እንደ Campbell ሃሳብ፣ ተመላሽ ተጋዳሊያን ተጋድሏቸውን አጠናቀው ሲመለሱ የዓለምን ተጽዕኖ መቋቋም ወይም መልመድ አለባቸው፡፡

## 2.2. የቀደምት ጥናቶ ቅኝት

በዚህ ንዑስ ክፍል ስር የሚታዊ ሂስ የትችት አንጻርን በዋነኛ መነጽርነት በመጠቀም የተለያዩ ሚታዊ ጭብጦችን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የዳሰሱ እና በአጠቃላይ ከዚህ ጥናት ጋር በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ዝምድና ያላቸው የምርምር ሥራዎች ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸውን ተዛምዶ በሚያሳይ መልኩ ቅኝት ተደርጎባቸዋል፡፡

የሚታዊ ሂስ የትችት አንጻርን ዋነኛ ማዕቀፍ በማድረግ የተለያዩ የሚታዊ ጉዳዮችን ለመተንተን የሞከሩ በርካታ የሃገር ውስጥም ሆነ የውጭ ጥናቶች አሉ፡፡ ይሁን እንጅ በዚህ ጥናት በተለይም ደግሞ በዚህ ንዑስ ክፍል ውስጥ ቅኝት የሚደረግባቸው የሃገር ውስጥ ጥናቶች ብቻ ናቸው፡፡ ምክንያቱም የዚህ ጥናት ዋነኛ ዓላማ በኤቶᵨጵ ረጅም ልቦለድ ውስጥ የተገለጹ የሚታዊ ተጋዳሊያን ጉዞ ደረጃዎችን መለየት እና አጉልቶ ማሳየት በመሆኑ፤ በአገር ውስጥ እና በአማርኛ ሥነጽሑፍ ሥራዎች በተካሄዱ ጥናቶች ላይ ትኩረት ማድረጉ የተሻለ እና ተመራጭ ይሆናል በሚል ጽኑ እምነት ቅኝቱ በአራት የአማርኛ ሥነጽሑፍ ጥናቶች ላይ አነጣጥሯል ማለት ነው፡፡ በሌላ አባባል፣ ይህ ጥናት በአማርኛ ሥነጽሑፍ ላይ ትኩረት ያደረገ በመሆኑ፣ በሃገር ውስጥ ወይም በአማርኛ ሥነጽሑፍ ላይ ከተካሄዱ ቀደምት ጥናቶች ጋር ያለው ዝምድና የበለጠ ቅርብ ነው፡፡ ስለዚህ በእነዚህ የሃገር ውስጥ ጥናቶች ላይ ልዩ ትኩረት አድርጎ ቅኝት ማድረጉ ተመራጭ እንደሆነ አጥኚዋ በጽኑ ታምናለች፡፡

በተጨማሪም ሚትን ዋነኛ ጉዳያቸው አድርገው በአማርኛ ሥነጽሑፍ ሥራዎች ላይ የተካሄዱት ጥናቶችም ቢሆኑ ሙሉ በሙሉ ቅኝት አልተደረገባቸውም፡፡ ምክንያቱ ደግሞ፣ ምንም እንኳን አጥኚዋ ሌሎች ተጨማሪ ሚት ነክ ጥናቶች መኖራቸውን በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ብትረዳም፤ ከጥናቶቹ ሙሉ መረጃዎችን ወስዳ ቅኝት ለማድረግ በሚያስችል መልኩ ሙሉ ጥናቶችን በቀላሉ ማግኘት ባለመቻሏ በሆኑን ልብ ይሏል፡፡ ባጭሩ ሌሎችን ቀደምት ጥናቶች ጠለቅ ባለ መልኩ ቅኝት ለማካሄድ ካጋጠማት የጊዜ ውሱንነት እና የመረጃ እጦት አንጻር እንደሆነ መገንዘብ ያሻል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ፣ ለዚህ ጥናት በተመረጠው እና የደራሲ ኤልያስ ገብሩ አዕምሮ (ዶ/ር) ሥራ በሆነው ኤቶዬጵ ረጅም ልቦለድ ላይ እስካሁን በተደረገ ፍተሻ መሠረት ምንም አይነት ጥናት ያልተካሄደበት መሆኑን አጥኚዋ ባደረገችው ቅኝት አረጋግጣለች፡፡ በሌሎቹ የደራሲው ሥራዎች ላይም ቢሆን እንደዚሁ የተካሄዱ ሌሎች ጥናቶች አላጋጠማትም፡፡ በዚህ መሠረት ከዚህ ጥናት ጋር የተሻለ ቅርበት አላቸው ተብሎ የታመነባቸው አራት ጥናቶች ብቻ ተመርጠው ጥናቶቹ ከተካሄዱበት ወቅት (ዓ.ም) አንጻር እንደሚከተለው በቅደም ተከተል እና በአጭር-በአጭሩ ቀርበዋል፡፡

የቴዎድሮስ ገብሬ (2001 ዓ.ም) *"የመባያ ጉዳዮች በገድለ ተክለ ሃይማኖት ውስጥ"* የተሰኘው "መጣጥፍ" ከዚህ ጥናት ጋር ተዘማጅ እንደሆነ የታመነበት ቀዳሚው ጽሑፍ ነው፡፡ በዚህ "መጣጥፍ" ውስጥ "ስያሜ፣ የልዕለ ተፈጥሮ እርዳታ፣ መስበክ/መመለስ፣ ፈውስ፣ ምስለ አጋንንት፣ ስእመት፣ በረከት ወይም ጽድቅ" እና "ቁጥር" የተሰኙ መባያዎች (ሚታዊ ጉዳዮች) በተመረጠው የገድል መጽሐፍ ውስጥ እንዴት ተመላልሰው እንደመጡ እና የእነዚህ መባያዎች ተምሳሌትነት ምን እንደሆነ ለመግለጥ የተሞከረበት "መጣጥፍ" ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ይህ የቴዎድሮስ "መጣጥፍ"ም እና የእኔ ጥናት በአንጻር ምርጫ ተመሳሳይነት ያላቸው ሲሆን፣ በተነሱት አንዳንድ ጉዳዮችም እንዲሁ በተወሰነ መንገድ ይገናኛሉ፡፡

"የልእለተፈጥሮ እርዳታ" እና በጥቂቱም ቢሆን "መመለስ" የተሰኙትን ጉዳዮች ያየን እንደሆነ ከስያሜያቸው ጀምሮ አንድ አይነት ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ይሁን እንጅ ይህ የእኔ ጥናት የእነዚህን ርዕሰነገሮች "መባያ"ነት ሳይሆን የተጋድሎ ደረጃዎች መሆናቸውን ለማሳየት የሚሞክር በመሆኑ ከቴዎድሮስ "መጣጥፍ" ጋር የተለየ ያደርገዋል፡፡ ከዚህ ባለፈ ግን በሁለቱም ሥራዎች ውስጥ የተነሱት ሌሎች ጉዳዮች በተነሱበት መንገድም ሆነ ሁኔታ የተለያዩ ናቸው፤ የናሙና ምርጫዎቻቸውም እንዲሁ፡፡

ሌላው እና ሁለተኛው ከዚህ ጥናት ጋር ዝምድና ያለው ደግሞ፣ "ሚቶሎጂያዊ ጥናት በእቴሜቴ የሎሚሽታ እና ይወስዳል መንገድ ያመጣል መንገድ" የሚል ስያሜ የተሰጠው እና ለሁለተኛ ዲግሪ መሟያነት የቀረበው የታደሰ ሽበሽ (2005 ዓ.ም) ጥናት ነው፡፡ ይህ የታደሰ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር በንድፈሃሳብ ምርጫ ይመሳሰል እንጅ፤ የታደሰ ጥናት በተመረጡት ልቦለዶች ውስጥ ደራሲው የተጠቀማቸውን ሚታዊ ቋንቋዎች እና በልቦለዶቹ ውስጥ የተስተዋሉትን ስነልቦናዊ ሚቶች በስፋት ተንትኖ አቅርቧል፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩ፣ የታደሰ ጥናት ለምርምር በተመረጡት የአዳም ረታ ልቦለዶች ውስጥ የቀረቡ ሚታዊ ጉዳዮችን እና የደራሲውን ሚቶከያኒነት በማዛመድ ለማሳየት የሞከረበት ጥናት ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ከአፃፃፍ ስልት (በጥቂቱም ቢሆን) ወደ ጭብጥ እየተመላለሰ በዓላማው ላይ የነደፈውን ጉዳይ ለማጉላት ጥረት አድርጓል፡፡ በዚህ ሂደት በተለይ ደግሞ ሚት እና ከስነልቦና በአንድ ላይ ተወዳጅተው እና ሰምረው እንዲቀርቡ ተደርጓል፡፡

ከዚህ ባለፈ ግን ይህ የእኔ ጥናት በተመረጠው ልቦለድ ውስጥ የቀረቡ የሚታዊ ተጋድሎ ደረጃዎችን ለይቶ በማውጣት ተንትኖ አቅርቧል፡፡ ከዚህ አንንጻር እነዚህ ሁለቱ ጥናቶች በዓላማ አነዳደፍም ሆነ በሚያነሷቸው ሃሳቦች የተለያዩ ናቸው፡፡ የልቦለድ (የናሙና) ምርጫም ቢሆን እንደዚሁ እነዚህን ጥናቶች የሚያለያይ ጉዳይ ነው፡፡

በሦስተኛ ደረጃነት ድግሞ የቀና ለሚ (2010 ዓ.ም)ን "የኦሮሞ ሚቶሎጅ ይዘታዊ ትንተና" የተሰኘ እና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፎክሎር ትምህርት ክፍል ለሦስተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት እናገኛለን፡፡ ይህ ጥናት የተለያዩ ሚታዊ ጉዳዮችን እዚህም-እዚያም የሚያነሳ በመሆኑ እና ስለሚት ምንነት፣ ስለሚት አከፋፈል፣ ስለሚት አፈጣጠር እና መሰል ሚት ነክ ጉዳዮችን የሚነሳ በመሆኑ ከዚህ (ከእኔ) ጥናት ጋር ይመሳሰል እንጅ፣ የመረጃ መተንተኛ ንድፈሃሳቦቹም ሆነ በትንተናው የቀረቡ ጉዳዮች ከዚህ የእኔ ጥናት ጋር የተለያ ናቸው፡፡

የቀና ጥናት በዋነኛነት የአንድን ብሔር ባህላዊ ሚት ነክ ጉዳዮች ለማሳየት የሞከረ እና እነዚህን ጉዳዮችም ከተረት፣ ከአፈታሪክ እና መሰል ፎክሎራዊ ጉዳዮች ጋር በማገናኘት የተተነተነበት ጥናት ሲሆን፣ የእኔ ጥናት ደግሞ በተመረጠው ልቦለድ ውስጥ የቀረቡትን ሚታዊ ጉዳዮች በተለይም ደግሞ የተጋድሎ ደረጃዎችን መሠረት ያደረገ ጥናት ነው፡፡ ስለሆነም እነዚህ ሁለት ጥናቶች ሚታዊ ጉዳችን የሚመለከቱ በመሆናቸው ይመሳሰሉ እንጅ፣ በዓላማ አነዳደፍ፣ በንድፈሃሳብ አወሳሰን፣ በናሙና አመራረጥ እና በትንተና አቀራረብ ሁሉ የተለያዩ ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ግን ይህን የቀናን ጥናት የእኔን ጥናት ጨምሮ በዚህ ንዑስ ክፍል ውስጥ ከተነሱት ሌሎች ጥናቶች ለየት የሚያደርገው በአማርኛ ልቦለድ ወይም በጽሑፋዊ ሥራ ላይ መሠረት ያደረገ አለመሆኑ ነው፡፡

ሌላው እና የመጨረሻው ከዚህ ጥናት ጋር ዝምድና ያለው ደግሞ፣ የአለማቀፍ ተናገር (2011 ዓ.ም) "ሚታዊ ንባብ በይስማዕከ ወርቁ ዴርቶጋዳ እና ራማቶሓራ ረጅም ልቦለዶች" በሚል ርዕስ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ለሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል የቀረበው ጥናት ነው፡፡ ይህ የአለማቀፍ ጥናት፣ በንድፈሃሳብ ትንተና ክፍሉ ላይ "ተደጋግመው የሚመጡ የሚት አይነቶች" አራት መሆናቸውን ከጠቀሰ በኋላ፤ "ሁነታዊ፣ ምልክታዊ፣ ሚታዊ ገፀባህርያት" እና "መባያ" በሚሉ ዋና ዋና ክፍሎች ተከፋፍሎ የንድፈሃሳብ ትንተና ተደርጎበት እናስተውላለን፡፡ በዚህ (በእኔ) ጥናት ውስጥ ደግሞ መለየት፣ መነሳሳት እና መመለስ የሚሉት ሦስት በየራሳቸው ወደተለያዩ ክፍሎች የሚከፋፈሉ ዓበይት የሚታዊ ተጋዳሊያን የተጋድሎ ጉዞ ደረጃዎች የቀረቡ ሲሆን፤ በእያንዳንዱ ስር ደግሞ ከምርምሩ ዓላማ አንጻር ቅርብ ናቸው ተብሎ የታመነባቸው ዝርዝር ሂደቶች ተተንትነዋል፡፡ ስለዚህ እነዚህ ሁለት ጥናቶች ገና ከመነሻው በዓይነት አከፋፈል በዚህ መልኩ ይለያያሉ ማለት ነው፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩ፣ በዚህ በእኔ ጥናት ዓበይት እና ንዑሳን የሚታዊ ተጋዳሊያን የጉዞ ወይም የተጋድሎ ደረጃዎች በሚል በዋና እና ዝርዝር ተከፋፍለው የተቀመጡ ጉዳዮች፤ በአለማቀፍ ጥናት ውስጥ ደግሞ "ሁነታዊ ሚት" በሚል ርዕስ ስር ወደ አስራ አምስት የሚደርሱ ርዕሰጉዳዮች በእኩል እና ትይዩ በሆነ መንገድ በአንድ ተደበላልቀው ተቀምጠው እናገኛለን፡፡ ይህ ብቻ አይደለም፤ በንድፈሃሳብ ትንተና ክፍሉ ውስጥ በዋና እና ዝርዝር ተቀምጠው የነበሩ ሃሳቦች በዋናው ትንተና ክፍል (ምዕራፍ ሶስት) ውስጥ አንዱ ከሌው ተቀላቅለው፣ ቀድሞ ዝርዝር የነበሩ ጉዳች በዚህ ክፍል እንደዋነኛ ጉዳዮች ተተንትነው እናገኛቸዋለን፡፡ ከዚህ አንጻር ይህ (የእኔ) ጥናት ከአለማቀፍ ጥናት ጋር በርዕስም ሆነ በንድፈሃሳብ ምርጫ ተመሳሳይ ይሁን እንጅ፣ ሁለቱም ጥናቶች በሚያነሷቸው ርዕሰጉዳዮች እና ንድፈሃሳባዊ ምደባዎች ግን በእጅጉ የተለያዩ ናቸው፤ የናሙና ምርጫዎቻችንም ቢሆን እንደዚሁ፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## የሚታዊ ተጋዳሊያን የተጋድሎ ጉዞ ደረጃዎች ትንተና በኤቶᵨጵ ረጅም ልቦለድ ውስጥ

በዚህ ምዕራፍ፣ በምዕራፍ አንድ ስር በተገለጸው የመተንተኛ ወይም የመፈከሪያ ስልት እንደዚሁም በምዕራፍ ሁለት ስር በተደራጁት ንድፈሃሳባዊ ትንታኔዎች መሠረትነት፣ በዚህ ጥናት ለትንታኔ በተመረጠው ኤቶᵨጵ ረጅም ልቦለድ ውስጥ የተንጸባረቁ ዋና ዋና የሚታዊ ተጋዳሊያን የተጋድሎ ጉዞ ደረጃዎች ተለይተው እና ተተንትነው የሚቀርቡ ይሆናል፡፡

በምዕራፍ ሁለት ላይ በግልጽ እንደሰፈረው ሦስት ዋና ዋና የጉዞ ደረጃዎች ያሉ ሲሆን፣ እነዚህ ዋና ዋና የተጋድሎ ደረጃዎች ደግሞ በየራሳቸው ወደሌሎች ንዑሳን ክፍሎች የሚሸነሸኑ ናቸው፡፡ በዚህ ምዕራፍ ደግሞ ለምርምር በተመረጠው ልቦለድ ውስጥ ተንጸባርቀዋል ተብሎ የታመነባቸው የተጋዳሊያን የተጋድሎ ጉዞ ደረጃዎች ብቻ ተለይተው ትንተና ተደርጎባቸዋል፡፡ ተጋዳሊያኑም ቢሆኑ ሙሉ የልቦለዱ ገፀባህርያት አይደሉም፡፡ ስለዚህ ሁሉም ገፀባህርያት ለትንተና አይቀርቡም ማለት ነው፡፡

በዋናነት ትንተናው የሚያተኩረው የልቦለዱ መሪ በሆኑት ስምንት ያህል ተጋዳሊ ገፀባህርያት (ኢትኤል፣ አብርሃም፣ ዘይኔ፣ መርየም፣ ናያድ፣ ዮሴፍ፣ ቶላ እና ፐ/ር እሴ) እና አብረዋቸው በሚጓዙት ሦስት ልዕለሰብዕ (አባገዳ ኦቦ አራርሳ፣ ሸህ ከድር እና አባ ኤልካኖ) ገፀባህርያት ላይ ሲሆን፣ አልፎ አልፎ ግን ሌሎችም ንዑሳን ገፀባህርያት እናዳስፈላጊነቱ ብቅ ሊሉ እንደሚችሉ ግን ልብ ይሏል፡፡ በዚህ መሠረት እነዚህ ገፀባህርያት ያለፉባቸውን የተጋድሎ ውጣውረዶች፣ ለተጋድሎው የነሳሷቸው ምክንያቶች እንዲሁም ያተረፏቸው ቱርፋቶች በልቦለዱ ውስጥ በሰፈረው ታሪክ ማሳያነት ይተነተናሉ፡፡

## 3.1. የልቦለዱ አጽመ ታሪክ

ኤቶᵨጵ ልቦለድ በአሥራ ሦስት ምዕራፎች እና በሦስት መቶ ሰማኒያ ሰባት (387) ገፆች የተዋቀረ እንዲሁም ታሪክን እና መንፈሳዊነትን ከፈጠራ ጋር በአንድ አዋህዶ የያዘ ሥራ ነው፡፡ በዚህ ልቦለድ ውስጥ ከኢትዮጵያ ልማዳዊ ሁነቶች ጋር የተገናኙ ልዩ ልዩ ታሪካዊ ክዋኔዎች እና ሃይማኖታዊ ጉዳዮች “ድር አና መግ” ሆነው ታሪኩ ወደፊት እንዲገሰግስ

አገልግለዋል፡፡ በተጨማሪም በአማናዊነት እና በእምት አልባነት፣ በጽኑ ሃይማኖተኛነት እና በባዕድ አምላኪነት፣ በአንደኛው እና በሌላኛው ሃይማኖት መካከል ያለውን መስተጋብር፣ የእምት እና የታሪክ እውቀት ፋይዳ ወዘተ በማሳየት ለጭብጡ ማድመቂያ ሎሙራ ሆነዋል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ የልቦለዱ አጠቃላይ አጽመታሪክ ተቀምጧል፡፡

ኢትኤል ከልጅነት አብሮ አደጉ ፅዮን ጋር በአንድ የትምህርት ተቋም ለመከታተል ካለው ጽኑ ፍላጎት የተነሳ ወደ ጅማ ዩኒቨርሲቲ ይሄዳል፡፡ በዚሁ አጋጣሚም ከፅዮን በተጨማሪ ልክ እንደእርሱ ሁሉ የህክምና ተማሪዎች የሆኑ አብርሐም፣ ዘይኔ፣ ቶላ፣ ናዖድ እና ዮሴፍ የተባሉ ሌሎች አምስት ጓደኞችን ያፈራል፡፡

ኢትኤል፣ አብርሐም፣ ናዖድ፣ ዮሴፍ፣ ዘይኔ እና መርየም (በአጋጣሚ ቤተመጻሕፍት ውስጥ ከአብርሐም ጋር የተዋወቀች እና በፍቅርም የተጎዳኘችው ገፀባህርይ) ከጅማ ዩኒቨርሲቲ ወደ ወሎ-ቁራኒ በመሄድ በዋሻ ውስጥ የሚኖር እና ሼህ ከድር የሚባል ሰው ያገኛሉ፡፡ ሼህ ከድርም የተለያየ ይዘት ያላቸው ሦስት ዋና ዋና ሰፋፊ ታሪኮችን ይነግሯቸዋል፡፡ በእነዚህ ታሪኮች እጅጉን ከተማረከው እና ሌላ መሰል ተጨማሪ እውቀትን ለማግኘት ይበልጥ ከቋመጠው ዘይኔ በስተቀር ሌሎች ጓደኞች ወደ ሁለተኛው እና ከዚህ ከሼህ ከድር ሰፈር "ቁራኒ" በስተሰሜን ወደሚገኝ ኦሮሞ ወደሚባል አካባቢ ለመሄድ ይነሳሉ፡፡

ኢትኤል፣ አብርሐም፣ መርየም፣ ናዖድ እና ዮሴፍ ኦሮሞ አካባቢ ወደሚገኙት እና አቦ አራርሳ ከሚባሉት አባገዳ ለመሄድ መኪና ላይ ተሳፍረው በመጓዝ ላይ እያሉ፤ በሃንጋሪ ካሉ ራስታዎች ጋር የማሪዋና ጥናት በማካሄድ ላይ ካለ አንድ እራስታ ጋር ይገናኛሉ፡፡ በተለይም ዮሴፍ በዚህ እራስታ የሃይማኖት፣ የታሪክ እና የሳይንስ እውቀት በእጅጉ ተመርኮ፤ በአደገኛ ሱስ ለተጠመዱ መድኃኒት የሚሆን እና ተስፋ ለቆረጡ ኢ-አማንያን የተስፋ ብርሃን የሚፈነጥቅ "ዊድ" የተባለ ተክል በመፈለግ ላይ ካለው እራስታ ጋር አብሮ ዕጹ ይገኛል ወደተባለበት ቦታ ይሄዳል፡፡ ሌሎች አራት ጓደኞች ደግሞ ወደ ኦሮሞ አቦ አራርሳ መንደር በመሄድ ላይ እያሉ፣ መንገዳቸው ላይ ቀደም ሲል ጅማ ዩኒቨርሲቲ ትተውት የመጡትን ጓደኛቸውን ቶላን ያገኙታል፡፡

ኢትኤል፣ አብርሐም፣ መርየም፣ ናዖድ እና ቶላ ኦሮሞ ከተባለችው አካባቢ ደርሰው፤ የቀድሞውን የኦሮሞ ታሪክ ተመራማሪ እና የአሁኑን አባገዳ ሽማግሌ አቦ አራርሳን ያገኟቸዋል፡፡ እርሳቸውም በመጀመሪያ፣ ስለ ኢትዮጵያ የቀድሞ ታላቅነት፣ ስለ

ኢትዮጵያውን የታሪክ፣ የባህል እና የእምነት ዕውቀት ውሱንነት ስላደረሰባቸው ኪሳራ እና ለዚህ ኪሳራ መፍትሔ ስለሆኑ ጉዳዮች የሚያስረዱ ሦስት ገለፃዎችን ይነግሯቸዋል፡፡ ቀጥለውም ከቶላ በስተቀር ሌሎቹ ወደሚቀጥለው “ራማ” ገዳም ወደሚገኙት አባ ኤልካኖ ወደተባሉት ባህታዊ እንዲሄዱ ነግረዋቸው፤ በቅድሚያ ግን ወልድያ ዩኒቨርሲቲ ሄደው ፕ/ር እሴ ለተባሉ ግለሰብ ይሰጧቸው ዘንድ መልዕክት (ደብዳቤ) ሰጥተው ይሰናበቷቸዋል፡፡

ኢትኤል፣ አብርሐም፣ መርየም እና ናየድ ወልድያ ዩኒቨርሲቲ እንደደረሱ ፕ/ር እሴን ያገኟቸው እና መልዕክታቸውን አድርሰው ወደ ዋናው መንገዳቸው ለመሄድ በዝግጅት ላይ እያሉ፣ ከጅማ አንስተው እዚሁ ወልድያ ዩኒቨርሲቲ በድንገት መገኘታቸውን ተከትሎ በወንጀለኛነት ተጠርጥረው ወልድያ ማረሚያ ቤት እንዲሄዱ ይደረጋል፡፡ ነገር ግን በዚያች ደብዳቤ መልዕክት ምክንያት ከአንድ ቀን አዳር በኋላ ይለቀቃሉ፡፡

ከወልድያ ቆይታ በኋላ ታዋቂው የታሪክ ተመራማሪ ፕ/ር እሴ ከውጭ ሃገር ድረስ ወደመጡለት ሚስጥራዊ ስፍራ ወደ አክሱም፣ እነኢትኤል ደግሞ ወደ “ራማ” ገዳም ይሄዳሉ፡፡ ከብዙ አድካሚ ጉዞ በኋላ እነኢትኤል አባ ኤልካኖን ያገኟቸዋል፡፡ እርሳቸው ሰፊ የሃይማኖት፣ የታሪክ እና የባህል ትምህርቶችን ይሰጧቸዋል፡፡ በተለይም ስለ መንፈሳዊነት ፋይዳ ሲያስተምሩ ናየድ የሳተው ነገር እንዳለ ይገነዘብና “ማስተካከል ያለብኝ ነገር አለ” ብሎ ወደ አዲስ አበባ ይመለሳል፡፡ ኢትኤል፣ አብርሐም እና መርየም ግን ከባህታዊው የሚሰጡትን አስተምህሮዎች እስከመጨረሻው በመከታተላቸው፤ ኢትኤል፣ የ**“ኢቶዮጵ”ን ሰው የማዳን መንፈስ** በአባ ኤልካኖ አማካኝነት ይካናል፡፡ አብርሐም እና መርየም ደግሞ ለኢትዮጵያ ሙስሊም እና ክርስቲያኖች ዘለዓለማዊ **የፍቅር ተምሳሌት** ሆነው ያበሩ ዘንድ አባ ኤልካኖ እና ሼህ ከድር ከዚያው የራማ ተራራ ላይ በንድ ላይ ተገኝተው ታላቅ ተክህኖን ይሰጧቸዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ፣ ፕ/ር እሴ ከአክሱም ሐውልት ስር ደርሰው የእያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ የእምነት በር ይከፍታሉ፡፡

በስተመጨረሻም ኢትኤል፣ በወላጆቹ በጠንቋይ ድግምት አማካኝነት “ባህር ሃጠራ” ከተባለ ሐይቅ ውስጥ በኢጋንንት ሰራዊት የተያዘችውን አብሮአደጉን ፅዮንን፤ በሌሎች መንፈሳዊ ቅዱሳት እርዳታ፣ በሄዱባቸው ታላላቅ አባቶች እና በጓደኞቹ ጸሎት እንዲሁም በተሰጠው ተክህኖ አማካኝነት ከገባችበት የኢጋንንት መንጋጋ ፈልቅቆ ያወጣታል፡፡ ፅዮንም ከዚያ ሁሉ ያልታሰበ ነገር በኋላ በዚህ አይነት ተዓምራዊ ሁነት ወጥታ፣ ወደ ጅማ ዩኒቨርሲቲ

በመሄድ ትምህርቷን ቀጥላ፤ ኢ.ትኤል፣ አብርሐም፣ መርየም፣ ዘይኔ፣ ናፆድ፣ ቶላ እና ዮሴፍ ሁሉም በጋራ በተገኙበት ትመረቃለች፡፡

## 3.2. መለየት

መለየት የሚታዊ ተጋዳሊያን ጉዞ የመጀመሪያው ደረጃ ስለመሆኑ የዘርፉ ልሂቃን ሃሳባቸውን ያስቀምጣሉ፡፡ የመጀመሪያው ደረጃ እንደመሆኑም የትኛውም ተጋዳሊ ለተጋድሎ ሲነሳ ይህን ደረጃ የግድ ይረግጣል ማለት ነው፡፡ "የየትኛም ጉዞ መጀመሪያው አንድ እርምጃ ነው" እንዲሉ በዚህ ለትንተና በተመረጠው ልቦለድ ውስጥ የምናገኛቸው ተጋዳሊ ገፀባህርያትም በሙሉ በዚህ ውስጥ ያለፉ ናቸው፡፡

ሚታዊ መለየት የሚባለው አንድ ተጋዳሊ ለአንጻች የተቀደሰ ዓላማ ነባር መኖሪያውን ትቶ ወደሌላ የማያውቀው እና አዲስ ወደሆነ ስፍራ መሄድ ነው (Campbell, 2004፣ Hartman & Zimberoff፣ 2009 እና ሌሎቹም)፡፡ ስለዚህ መለየት ከቤተሰብ፣ ከአካባቢ፣ ከማኅበረሰብ በመነጠል እርቆ መሄድ እንደሆነ እንገነዘባለን፡፡ በዚህ መሠረት ቀደም ብየ እንደጠቆምኩት፣ ለዚህ ጥናት በተመረጠው ልቦለድ ውስጥ ያሉት ተጋዳሊ ገፀባህርያትም ተጋድሏቸውን የሚጀምሩት ቢያንስ የዓለማዊ ህላዌ ዕቅዳቸውን ለማሳካት ሲሉ ከቤተሰቦቻቸው፣ ከአካባቢያቸው ወይም ከተወለዱበት ሰፈር ተነጥለው በመሄድ ነው፡፡ እነዚህ ተጋዳሊያን ከዚያው ተለይተው ለዓማዊ ሕይወታቸው ሲሉ ደፋ ቀና እያሉ ካሉበት ስፍራ፣ ለተመሳሳይ መንፈሳዊ እና ታሪካዊ ተጋድሎ ታጭተው በዚያው ለታጬበት ተጋድሎ ይፋለማሉ፡፡

ባጭሩ ሁሉም ተጋዳሊ ገፀባህርያት በትምህርት እና በምርምር ምክንያት ይኖሩበት ከነበረው የቀድሞ ቀያቸው ተለይተዋል፡፡ ይህ መለየት ደግሞ በአንድም ሆነ በሌላ አጋጣሚያዊ ጥሪ አሊያም ቀድመው ባስቀመጡት ዓላማ ወይም ደግሞ በገዛ ፍላጎታቸው (ትምህርታቸውን ለመከታተል ሲሉ) ምክንያት የመጣ ነው፡፡ ጥሪው በምንም ይሁን በምን ዋናው ነገር ግን የተጋዳሊያኑ የመጀመሪያው እርምጃቸው ከነባሩ ዓለማቸው መለየት መሆኑን ለማጠየቅ ነው፡፡

እንደ Campbell (2004) ሐተታ ሚታዊ መለየት አምስት ንዑሳን ክፍሎች አሉት፡፡ በዚህ መሠረት እነዚህ አምስቱም ክፍሎች ደግሞ በዚህ ጥናት ውስጥ ተካተው እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 3.2.1. ወደ ተጋድሎ መጠራት

ተጋዳሊያን ለአንዳች ዓላማ ታጭተው ወደተጋድሎ እንደሚገቡ ከፍ ብየ ጠቁሜያለሁ፡፡ ይህ ንዑስ ክፍል ደግሞ፣ ይህ አይነቱ ለአንዳች ዓላማ ለተጋድሎ መታጨታቸው ለተጋዳሊያኑ እንዴት ባለ መንገድ ይቀርብላቸዋል? ወይም ደግሞ ለተጋድሏቸው መነሻ የሆኗቸው ምክንያቶች ምን ምን ናቸው? የሚሉትን ጥያቄዎች ያነገበ እና እነዚህን በመመለስ ላይ ያነጣጠረ ነው፡፡

በዚህ መሠረት፣ አንድ ሚታዊ ተጋዳሊ ከመሬት ተነስቶ ወደ ተጋድሎ አይገባም፡፡ ይልቁኑ አንዳች ሊደርስበት የፈለገው፣ ለማወቅ የሚሻው፣ ለማግኘት የሚጓጓለት መሠረታዊ ጉዳይ ይኖረዋል፡፡ ይህ ሲባል ተጋዳሊው በሚኖርበት ዓለም ውስጥ ያልተመለሱለት አሊያም ምቾት የነፈጉት ጥያቄዎች አሉት ማለት ነው፡፡ ስለዚህ እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ ሲል በገዛ ፈቃዱ (ልክ እንደ ፕ/ር እሴ) ወደ ተጋድሎ ይገባል ማለት ነው፡፡ በኤቶፖጵ ረጅም ልቦለድ ውስጥ ከምናገኛቸው ተጋዳሊ ገፀባህርያት መካከል ፕ/ር እሴ አንዱ ናቸው፡፡ ፕ/ር እሴ፣ እስካሁን ድረስ በውል አልታወቁም፣ አልተደረሰባቸውም ብለው የሚያስቧቸውን ታሪካዊ ክዋኔዎች ለዓለም ህዝብ ለመግለጥ የሚኳትኑ ገፀባህሪ ናቸው፤ “[…] በግላቸው ስለ አክሱም እና ጥንታዊ ግብፅ ፒራሚዶች ትርጉም እና የመሰራታቸው ተክክለኛ አላማ ለማጋለጥ ጥናት ከጀመሩ 13 ዓመታትን አስቆጥረዋል” (ኤልያስ፣ 2010፤ 53)፡፡

በእርግጥ፣ ፕ/ር ከመነሻው በዚህ የጥናት መስክ ላይ እንዲሰማሩ የገፋፋቸው አካል ባይኖርም፤ የኋላ የኋላ ግን ተጋድሏቸውን ከመቼውም ጊዜ በላይ አጠናክረው እንዲቀጥሉ እንዲሁም ዓለማዊ እና መንፈሳዊ ዕውቀትን በአንድ ላይ አጣምሮ የያዘውን የኢትዮጵያን ታሪክ ለህዝቦቿ ለመግለጥ ቆርጠው እንዲነሱ የሚያደርግ አጋጣሚ ተፈጥሯል፡፡ ይኸውም በአንድ አጋጣሚ በንባብ ላይ እያሉ ያገኙት ታሪክ ታላቅ ተጋድሎ እንዲጀምሩ ቀስቅሷቸዋል፡፡ ተጋዳሊያን ለተጋድሎ ከሚጠሩባቸው ዋነኛ መንገዶች መካከል ደግሞ እድል ወይም አጋጣሚ አንደኛው ስለመሆኑ Campbell (2004) ያስረዳሉ፡፡

ፕ/ር እሴ ከዕለታት በአንዱ ቀን፣ እንደ ሁልጊዜው ሁሉ የ"ላፕቶፕ" በይነ መረባቸውን (ኢንተርኔታቸውን) ከፍተው የታሪክ መረጃዎችን በማንበብ ላይ ሳሉ ያገኙት አንድ ታሪክ ከወትሮው በተለየ ወደ ውስጣቸው ዘልቆ እንደገባ እና ለታላቅ ተጋድሎ እንደተነሳሱ የልቦለዱ ታሪክ እራሱ እንዲህ ይነግረናል፤

> "እስካሁን ይሄ ሁሉጉድ የት ተደብቆብን ነበር!?... ከፊታችን የተቀመጠውን ተዓምር እኳን ማይት የተሳነን ምን አይነት ከንቱዎች ነን!" አሉ በንዴት፤ ሲያነቡ የነበረውን ላፕቶፕ እየዘጉ፤ በልባቸውም ይህንን መንፈሳዊ እና ዓለማዊ የከፍታ ዕውቀት ለመላው ኢትዮጵያዊ ይፋ ለማድረግ ቃል ገቡ፡፡ (ኤልያስ፣ 2010፤ 53)፡፡

የየትኛውም ተጋዳሊ ተቀዳሚ ዓላማ ከራሱ እውቀት እና ደስታ ባለፈ ለሌሎች ሰዎች እውቀት እና ድኅነት (መድኃኔ ሕይወት) ሲል እራሱን ለመስዋዕትነት የሚያቀርብ አካል እንደሆነ በምዕራፍ ሁለት ላይ ለማንሳት ተሞክሯል፡፡ ፕ/ር እሴ አሁን በእርሳቸው እውቀት ላይ ሌላ እውቀት ለማከል፣ አሊያም በምርምራቸው ዳጎስ ያለ ትርፍ ለማጋበስ እና እራሳቸውን ለማስደሰት ሆነ ብለው ለተጋድሎ አልተነሱም፤ ይልቁንም ለሃገሪቱ ህዝቦች ስውር ሆኖ የቆየውን ታሪክ እና እምነት ለመግለጥ እንጅ፡፡ ለዚህ ቁርጠኛ ተጋድሏቸው ደግሞ በንባባቸው ወቅት አእምሯቸውን ያነቃ ታሪክ ማግኘታቸው በመሆኑ፤ይኸውም እንደ ዋነኛ የተጋድሎ ማንቂያ ጥሪ ሆኗል ማለት ነው፡፡

በእርግጥ የተጋድሎ ጥሪ ይህ ነው ተብሎ ከማይገለጽ ወይም በውል ከማናስተውላቸው እና በዘወትራዊው ዓለም ሳይቀር ተደጋግመው ከሚከሰቱ አጋጣሚዎች መካከል አንዱ ሊሆን እንደሚችል የዘርፉ ምሁራን ያትታሉ፤ "... በዕለት ተለት ኑሮ በሚፈጸሙ ድርጊቶች፣ በሚደርሱ ሁነቶች መሃል የሰርክ በመሆናቸው ተጋዳሊው ልብ በማይላቸው ጉዳዮች ትዕምርትነት ሊከሰት ይችላል" (ቴዎድሮስ፣ 2001፤ 6)፡፡ ተጋዳሊው እነዚህን አይነት ጥሪዎች በውል አያጢናቸው እንጅ፤ እነዚህ ሰርካዊ ሚመስሉ አጋጣሚዎች የሚፈጥሩት ድባብ ሃሳበቡን ወደ አንድ አቅጣጫ በመዘወር በአጋጣሚዎች ወደተጋድሎ እንዲገባ ይገፋታል ማለት ነው፡፡ ከዚህ በላይ በፕ/ር እሴ ያስዋልነውም ይህንኑ ነው፡፡

ከፕ/ር እሴ በተጨማሪም በአንድ ምሽት በእነ ናያድ፣ ዘይኔ፣ አብርሃም እና ኢትኤል መካከል የተነሳው ሃይማኖታዊ ክርክር ለእነዚህ ተጋዳሊያን የመጀመሪያው ማንቂያ ደዎል ነው፡፡ በዚህ አጋጣሚያዊ የሃይማኖት ክርክር ውስጥ ስለ ሃይማኖት የማወቅ ጉጉታቸውን

አነሳስቶታል፡፡ በተለይ ደግሞ ኢትኤል በዚህ ሃይማኖታዊ ክርክር የተነሳ የሚከተሉት ጥያቄዎች እንቅልፍ ሲነሱት ከልቦለዱ እንዲህ እናነባለን፡፡

*እውን አምላክ አለ? የት ነው ያለው? ምን አይነት ነው? ካለስ ለምን ፈጠረን? ፈጥሮስ ለምን ስንሰቃይ ዝም ብሎ ያየናል? ሁሉም የኔ ልክ ነው ብለው ካስተማሩ ትክክለኛው ሃማኖት የቱ ሊሆን ይችላል? ኢትዮጵያስ የእውነት ቅድስት ሃገር ናት? ከሆነችስ ይሄ ሁሉ ሃይማኖተኛ እያለባት ችግር፣ ርሃብ፣ ጦርነት፣ በሽታ እና ስደት ለምን ይወርሳታል? ለህመሟ መፍትሔውስ ማን ይሆን? እምነትስ ምንድን ነው? እውነትስ?...* (ኤልያስ፣ 2010፤ 51)፡፡

በእርግጥ ኢትኤል ይህን ያህል በግልጽ እራሱን ይጠይቅ እንጅ ሌሎቹም ቢሆኑ ክርክራቸው “የእኔ ሃይማኖት ይበልጣል” የሚል በመሆኑ እንደኢትኤል ሁሉ እነዚህ ጥያቄዎች በውስጣቸው መኖራቸውን ማሳያ ነው፡፡ ስለዚህ ለእነዚህ ሁሉ ጥያቄዎች መልስ የሚያገኙበትን አጋጣሚ መሻታቸውን እንረዳለን፡፡ በተጋድሏቸው መጨረሻ ከሚያገኟቸው ቱርፋቶች መካከልም የእነዚህ ጥያቄዎች ምላሽ ዋነኛው ሆኖ እናስተውላለን፡፡

በተመሳሳይ መልኩ፣ ቶላ እንደ ወትሮው ሁሉ “ዋርድ” (የህክምና ተግባር መለማመጃ ክፍል?) ቆይቶ ምሳውን ከበላ በኋላ በሥራ የደከመ ዕምሮውን በቡና ዘና ለማድረግ አስቦ ቡና ወደሚጠጣበት ቦታ ሲያመራ ነበር፤ በድንገት ከኋላው ፈጽሞ አይቷቸው በማያውቅ ትልቅ ሰው አንደበት ስሙ ሦስት ጊዜ በተከታታይ የተጠራው፡፡ ምናልባትም ሦስት ጊዜ መጠራቱስ እራሱን የቻለ ተምሳሌት ይሆን? የሆነው ሆኖ፣ በዚህ ግርማ ሞገሳም አባገዳ ለሦስት ጊዜያት ያህል ስሙ ተጠርቶ የመጀመሪያውን የተጋድሎ ትዛዝ አዘል ጥሪ ተቀብሏል፡፡

> *“ቶላ...ቶላ...ቶላ...” አሉት ማራኪ ፈገግታ ፊታቸው ላይ እየተነበበ፤*
> *“አ..አቤት፤” አለ ቶላ ህይወቱን በሙሉ አይቷቸው በማያውቅ አንድ ሰው* ***ሦስቴ*** *መጠራቱ እንቆቅልሽ እየሆነበት፤*
> *“... አንተን ዛሬ የማበስርህ ደስታ እና የምነግርህ ማስጠንቀቀቂያ ስላለኝ መጥቻለሁኝ፡፡ እናማ...”*
> *“ለመሆኑ የስምህን ትክክለኛ ትርጉም ታውቃለህ? ይህቺ ያሰርካት የኦዳችን፣ የአድባር ዛፍስ ትርጉሟን ታውቀው ይሆን? ... አይመስለኝም!...ስለዚህ ጉዞህን እወቅ! እጣ ፋንታህን አንተ ቅርፅ ታስይዛለህና፡፡” አሉት፤* (ኤልያስ፣ 2010፤ 51)፡፡

በዚህ መልክ ነው እንግዲህ ቶላ የመጀመሪያውን ጥሪ የተቀበለው፡፡

ቶላ በእንደነዚህ አይነት ልዕለሰዎች ወይም የተለየ አይነት ተክህኖ ባላቸው ሰዎች አማካኝነት ከሌሎች ለተጋድሎ ከታጩ ጓዶቹ (ኢትኤል፣ አብርሃም፣ ዘይኔ እና ናኦድ) ጋር

አሁንም ለሁለተኛ ጊዜ ጥሪ ደርሶታል፡፡ እንግዲህ፣ እነዚህ በጅማ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ በጤና ትምህርት መስክ እየተማሩ የሚገኙ ጓደኛሞች፣ ከሚማሩት የጤና ትምህርት ባሻገር ስላላስተዋሏቸው ሃይማኖታዊ እና ትውፊታዊ ጥበባት በውል ያውቁ እና ያሳውቁ ዘንድ በተለያየ ጊዜ፣ በተለያየ መልክ የተጋድሎ ጥሪ እየቀረበላቸው ይገኛል፡፡

አንድ ጊዜ ለታላቅ ልዕልና ታጭተዋልና፤ ከእለታት ባንዱ ቀን እነዚሁ ተማሪዎች ከዋርድ ቆይታ በኋላ ለምሳ በጋራ በሚወጡበት ሰዓት የተሰነዘረላቸውን ሁለተኛ ማንቂያ ደወል ልቦለዱ እንዲህ ይነግረናል፡፡

> ኢትኤል፣ አብርሃም፣ ዘይኔ፣ ቶላ፣ ናሃድ እና ዮሴፍ ስለዶ/ር ሳሙኤል ለየት ያለ አመለካከት በመገረም እያወሩ ከሆስፒታሉ ወጡ፡፡ […] በድንገት ግን አንድ አባት ከፊታቸው መንገዱን ዘግተው ቆሙ፡፡ […] "የሰራዊት ጌታ በእናንተ በኩል ለዚህ ትውልድ ያስተምራልና፡፡ እንግዲህ ይህች ምድራዊ የአስኳላ ት/ት [ስህተት ከምንጩ] ፈተናችሁ ስታበቃ ሁላችሁም አንድ አይነት ህልም ታያላችሁ፡፡ […] እነሆ ይህንን ህልም ካያችሁ በኋላ፤ 3 ቦታዎች ሄዳችሁ 3 ሰዎችን ታገኛላችሁ፡፡ ይህም ታላቅ መገለጥ ይሆናልና፡፡" አሏቸው፤… (ኤልያስ፣ 2010፤ 151-152)፡፡

ከልቦለዱ ታሪክ ላይ እንደሰፈረው፣ ይህ ጥሪ የተበረከተው ዮሴፍ ለጊዜው ካርድ ለመግዛት ወደሱቅ ባመራበት ቅጽበት ከዮሴፍ ውጭ ላሉት ለሌሎች ሁሉም (ለአምስቱም) ጓደኛሞች ነው፡፡

እንደ ቴዎድሮስ (2001፣ 6) ማብራሪያ፣ "ሕልም እና ራዕይ ተዘውታሪ የጥሪ ማድረሻ፣ ለገድል የመቀስቀሻ መንገዶች ናቸው፡፡ በሕልም እና በራዕይ ጥሪው በዝርው እንዳለ ሊቀርብ፣ አሊያም በሌሎች ነገሮች ተወክሎ በተዕምርትነት ሊመጣ ይችላል"፡፡ በመሆኑም በ*ኢቶ*ቶ*ጵ* ልቦለድ ውስጥ ከዚህ አስቀድሞ በአንድ ልዕለሰብዕ አማካኝነት በተነገራቸው መሰረት ለእነዚህ አምስት ጓደኛሞች ለሦስተኛ እና ምናልባትም ለመጨረሻ ጊዜ የተጋድሏቸው ጥሪ በህልም አማካኝነት "በዝርው" በቀጥታ ቀርቦላቸዋል፤ ተገልፆላቸዋል፤ የትልቁ ተጋድሏቸው ይፋዊ ማስጀመሪያ ፊሽካ ተነፍታለች፡፡ ይህ የህልም ጥሪ (መገለጥ) ግን ካምስቱ ጓደኛሞች በተጨማሪ ሌላ አንዲት እንስትንም ይጨምራል፤ መርየምን፡፡ ይህን ታሪክ ኤልያስ (2010፤ 178) በልቦለዱ ውስጥ እንዲህ አስፍረውት እናነባለን፡፡

> […] እንግዲህ እናንተ ስድስታችሁም ብዙሃኑን ስለምትወክሉ ተመርጣችኋል፡፡ ለቀረው የዘመናችሁ ትውልድ መልዕክቱን እንድታስተላልፉ በተስፋ እንልካችኋለን፤ ሰባተኛዋ ጋርም ትገናኛላችሁ፡፡

> በሉ ሂዱ እና ሦስት ሰዎችን አግኙ፤ ከመጀመሪያው ሰው 3 ታሪኮችን ትሰማላችሁ፡፡ ሁለተኛው ሰው 3 መግለጫዎች ይነግራችኋል፤ ሦስተኛው ሰው ዘንድ ስትሄዱ ደግሞ 3 ማረጋገጫዎችን ይሰጣችኋል [...]፡፡

እነዚህ ተጋዳሊ ገፀባህርያት ለተጋድሎ በተጠሩበት ወቅት የሚታገሉላቸው ዓላማዎች በዚህ መልኩ አብረው ተቆርጠውላቸዋል፡፡ ስለሆነም ተጋድሏቸውን የሚከውኑት ለእነዚህ ሦስት ገፀበረከቶች ለመብቃት እና መልሰውም ለማኅበረሰባቸው ለመድረስ እንደሆነ የተጋድሎ ተልዕኳቸውን ወስደዋል፡፡ ተጋዳሊ ገፀባህርያቱ ለእነዚህ በረከቶች ሲሉ፣ ከዚህ በኋላ የሚመጣውን ፈተና ሁሉ ለመጋፈጥ እራሳቸውን አዘጋጅተዋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ፣ “ስድስታችሁ” የተባለበት ምክንያት ጓደኞቸውን ዮሴፍን ጨምሮ ሲሆን፣ ለእሱ ግን ምንም አይነት ታላቅ የህልም መገለጽ አልታየውም ነበር፡፡ ይሁን እንጅ ከእነዚህ ጓዶቹ ጋር በአብሮነት ወደ ታላቁ ተጋድሎ ሲገባ እናስተውላለን፡፡ ዮሴፍ ከጓደኞቹ ጋር በመሄድ እራሱን ዘና ለማድረግ ሲል በአጋጣሚ ይነሳሳ እንጅ፤ የእነርሱን የጉዞ ምስጢር ከቶውንም አያውቅም፡፡ ከዚህ አንጻር የዮሴፍ የተጋድሎ ጥሪ **አጋጣሚ** እንጅ፣ ይህ ታላቅ የህልም ጥሪ አይደለም ማለት ነው፡፡

> [...] ስድስተኛው የዶርማቸው አባል የሆነው ዮሴፍ እነርሱ ያዩትን ህልም ለማየት አልታደለም፡፡ ነገርግን የዶርሙ ልጆች በሙሉ እንደሚሄዱ ሲሰማ መነጠል ስላልፈለገ፣ [...] ለእነርሱ የእንቆቅልሽ መፍቻ ጉዟቸው ሲሆን ለእሱ ደግሞ እንደ ‹‹ቫኬሽን›› ያለ መፍታቻ ነበር (ኤልያስ፣ 2010፤ 198)፡፡

ቶላ ምንም እንኳን ለህልም ጥሪው ቢታደልም፤ በቸልተኛነት አሊያም በተቃውሞ ሰልፉ ላይ ለመሳተፍ ካለው ፍላጎት፣ የተደረገለትን ታላቅ መገለጥ ባለመቀበል ከሌሎች ጓዶቹ የመጀመሪያ የተጋድሎ ጉዞ ተለይቶ መቅረቱን እንዲሁም ይህ የተደረገለትን ቅዱስ ጥሪ አለመቀበል ደግሞ ሁሉም ነገር እንዳሰበው ሳይሆን ሕይወቱን አደጋ ላይ የሚጥል አጋጣሚ መውለዱን ከዚህ ቀጥሎ “ጥሪን አለመቀበል” በሚለው ክፍል ስር በሰፊው እመጣበታለሁ፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ ግን፣ ይህ ድንገተኛ የሚመስል ክስተት የሕይወትን ከንቱነት የሚረዳበት እና ከዓለማዊ ህላዌ ወደ ተጋድሎ የሚወጣበት አንዱ ቀስቃሽ አጋጣሚ እንደሆነው መረዳት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ለመጨረሻ ጊዜ በአንድ ልዕለሰብዕ ቀጥታ መገለጥ ለታላቅ ተጋድሎ በሚከተለው መልኩ የተጠራው በዚሁ አጋጣሚ እንደሆነ የልቦለዱ ታሪክ እራሱ ምስክር ነው፡፡

"እንዳትረሳ ልጄ ያንተ መንገድ ገና ነው፡፡ ጥይትም ሆነ ዱላ ሊገድሉህ አይቻላቸውም፤ አንተ ደም እና ስጋ ብቻ ሳትሆን ታላቅ ዓላማ ያለህ ማንነት ነህና፡፡ እንግዲህ አሁንም ደህና ሆነሃል እጣ ፋንታህን ተከትለህ ከወልድያ በስተምዕራብ ማዶ ወዳለች ኦሮሞ ወደምትባል አካባቢ አቅና፤ ‹ኦቦ አራርሳን› ብለህ ጠይቅ ታገኘኝማለህ!" አሉት (ኤልያስ፣ 2010፤ 226)፡፡

ቶላ ከዚህ አስቀድሞ በተለያዩ ተምሳሌቶች እንዲሁም በህልም መገለጥ ጥሪ ቢደርሰውም "ጆሮ ዳባ" ብሎ አልፏቸዋል፡፡ አሁን ደግሞ ከዚህ በላይ ባየነው መልኩ አንድ የተለየ ተክህኖ ያለው ልዕለሰብዕ በእውን ተገልጠው የጉዞ ጥሪውን አብስረውታል፡፡ አሁንም ቢሆን ይህንን ቅዱስ ጥሪ መቀበል ወይም አለመቀበል ለእርሱ የተተወ ነው፤ ነገር ግን ያንን ሁሉ ተዓምር አይቷል፤ ከህመሙም ቢሆን ምንም አይነት ጭረት ሳይቀር በአንዲት ቅጽበት ፈጽሞ ድኗልና፤ ይህንን ጥሪ አለመቀበልስ እንደምን ይቻለዋል? አሁን በተዓምር እንዲያምን ተገዷል፡፡ ስለዚህ ከዚህ ጥሪ በኋላ ይህን ቅዱስ ተልዕኮ በጸጋ ተቀብሎ ለታላቅ ተጋድሎ ተነስቷል፡፡

## 3.2.2. ጥሪን አለመቀበል

ጥሪን አለመቀበል አንድን ተልዕኮ፣ ድርጊት ወይም ተግባር ለመፈጸም አለመፍቀድ፤ አሊያም በአንድ አካል የሚቀርብን ትዕዛዝ ለማክበር፣ ካለመፈለግ የሚመነጭ አሉታዊ የሆነ ግብረመልስ ስለመሆኑ ለሁላችንም ግልጽ ነው፡፡ ይህ አሉታዊ ግብረመልስ ደግሞ እራስን ቀድሞ ካለማዘጋጀት፣ በራስ ካለመተማመን፣ የራስን ዕውቀት እና ብቃት ከድርጊቱ በላይ ወይም በታች አድርጎ ከማሰብ፣ ከክፋት፣ ካለማወቅ፣ በሌላ ሥራ ከመጠመድ ወዘተ ሊመነጭ ይችላል (Campbell፤ 2004)፡፡

ቶላ ምንም እንኳን እንደሌሎቹ ስድስት ጓዶቹ ሁሉ በዚያች ቅድስት ሌሊት ቅዱስ የሆነ ጥሪ ቢቀርብለትም፤ በታዘዘው መሠረት ጥሪውን ተቀብሎ አብሯቸው የተጋድሎ መንገዱን ለመቀጠል ግን አዎንታዊ ምላሹን ነፍጓል፤ ጥሪውን ከቁብ ሳይቆጥር ወደኋላ አፈግፍጓል፤ ከሌሎቹ ተጋዳሊያን ጓዶቹ የመንፈሳዊ ተጋድሎ ጉዞ ተለይቶ መቅረትን መርጧል፡፡

[…] ወደ አዲስ አበባ ጉዞ ለመጀመር ተዘገጃጅተው እንደጨረሱ ኢትኤል ቶላ ጋር ስልክ ደወለ፤ ጠራለት፡፡
"[…] በተባባልነው መሰረት ወደ ወሎ ጉዞ ልንጀምር እየተነሳን ነው፡፡ አትመጣም እንዴ?" አለ ኢትኤል፤
"ውይ […] እኔ እንኳን አልችልም፡፡ […]" (ኤልያስ፣ 2010፤ 200-201)፡፡

እንደ Campbell (2004) ሃሳብ፣ በሚት ውስጥ በአብዛኛው ጥሪን አለመቀበል የተጋዳሊውን ጉዞ እና አጠቃላይ ህላዌ ማለት ይቻላል፤ ወደ አሉታዊ አኳኋን ይለውጣል፡፡ ምክንያቱም ጥሪው በራሱ መመረጥ ወይም ቅድስና ነውና፡፡ ስለዚህ ተጋዳሊው በቸልተኛነት፣ በብርቱ ሥራ በፍርሃት ወይም ደግሞ በባህላዊ እሴቶች በመታጠር እና በሌሎችም መሰል ምክንያቶች ሳቢያ የሚቀርብለትን ጥሪ ከገፋ ታላቅ የሆነውን አዎንታዊ ተግባር ያጣ እና ወደ ጥቃት አለፍ ሲልም ወደሞት ይመጣል፡፡ የቶላ ታሪክ ደግሞ ለዚህ ሃሳብ አይነተኛ ማስረጃ ነው፡፡ ቶላ፣ ምንም እንኳን ለተጋድሎ ተመርጠው በህልም ከተገለጠላቸው ተጋዳሊያን መካከል አንዱ ቢሆንም፤ ጥሪውን ተቀብሎ ተልዕኮውን ለመወጣት ፈቃደኛ ባለመሆኑ የተነሳ ክፉኛ የሆነ አደጋ አጋጥሞታል፡፡ እስኪ የሚከተለውን ቅንጫቢ ታሪክ እንመልከት፤

> … ወጣቶቹ የተጎዳውን ልጅ አመጡ እና አልጋው ላይ አስተኙት፤…
> "(ምን ሆኖ ነው?)" አለ ቢሊሱማ…በግራ ጎኑ ቢተኛም ደሙ ቡልቅ ቡልቅ የሚለው ከቀኝ ትካሻው ላይ እንደሆነ ለማወቅ ጊዜ አልፈጀበትም፡፡
> "(ጥይት) ነው የመታው" …
> "አይዞህ… ?" አለው እና የእጅ ጓንቶቹን አጥልቆ የሚደማውን ቦታ በፋሻ ለመጫን ልጁን በጀርባው ገልበጥ ሲያደርገው ቢሊሱማ ክው ብሎ በቆመበት ቀረ፡፡ … "**ቶላ**!" አለ በድንጋጤ፤ … (ኤልያስ፣ 2010፤ 223-224)፡፡

ቶላ ከደረሰበት ከባድ አደጋ የተነሳ አሁን ሕይወቱ ከሞት አፋፍ ላይ ተንጠልጥላ ትገኛለች፡፡ ከእርሱ ጋር ተመሳሳይ የደም ወገን ብቻም ሳይሆን፤ በቂ የሆነደም ማግኘት ግድ ሆኗል፡፡ በቂ የሆነ የደም ሙሌት ካልተደረገለት ደግሞ የመትረፉ ነገር በእጅጉ አጠራጣሪ ደረጃ ላይ ነው፡፡ ይችን ከሞት ጋር የምትፋጠጥ እና ልትበጠስ የደረሰች ቀጭን ህላዌ ለማቆየት አንዳች ተዓምር መፈጠር አለበት፡፡ ቢያንስ እንኳን በደም ባንኩ ውስጥ ከሚገኘው አንድ የደም ወገን ጋር ተመሳሳይ መሆን፤ ካልሆነ ግን እስከመጨረሻው ማለፍ፡፡ ይህ ሁሉ ጣጣ ደግሞ የቀረበለትን **ቅዱስ ጥሪ ካለመቀበል** የመነጨ፣ የተወለደ እንደሆነ መገንዘብ ለማናችንም ቀላል ሆኖ በልቦለዱ ታሪክ ውስጥ ይገኛል፡፡

## 3.2.3. የልዕለተፈጥሮ ዕርዳታ

ከዚህ አስቀድሞ ስድስቱም ተጋዳሊያን ለታላቅ ተጋድሎ ይነሳሱ ዘንድ በህልም መቀስቀሻ ደወል አማካኝነት ጥሪ እንደቀረበላቸው አይተናል፡፡ ነገር ግን ይህ ጥሪ ማንቂያ ደወል ብቻ አልነበረም፤ ወደተጋድሎው ሲገቡም ቢሆን ይዘውት የሚጓዙ የተጋድኗቸው የስኬት ስንቅም ጭምር እንጂ፡፡

በምዕራፍ ሁለት እንደተነሳው፣ የልዕለተፈጥሮ እርዳታ ተጋዳሊያኑ ወደተጋድሎ በሚገቡበት ወቅት አደጋ እንዳይደርስባቸው ቀድሞ የሚያስጠንቀቅ፣ ከፊት ሆኖ የሚመራ፣ ከጎን ሆኖ የሚያግዝ፣ ለሚገጥሙ ችግሮች መፍትሔ የሚያቀርብ እና በጥቅሉ ተጋድሏቸውን በብቃት እንዲፈጽሙት የሚያስችል ትጥቅ ነው (ቴዎድሮስ፤ 2001፣ Campbell፤ 2004፣ Klaus፤ 2010 እና ሌሎችም)፡፡ በዚህ መሠረት ለዚህ ጥናት በተመረጠው ልቦለድ ውስጥ የምናገኛቸው ሰባቱ ተጋዳሊ ገፀባህርያት (ኢትኤል፣ አብርሃም፣ ዘይኔ፣ መርየም፣ ናያድ ቶላ እና ዮሴፍ) ለተጋድሎ ሲነሱ እስከትግላቸው መጨረሻ ድረስ ይዘዋቸው ይጓዙ ዘንድ ሦስት ዋና ዋና የተጋድሎ ትጥቆችን አንዳች ልዕለተፈጥሮ ኃይል ከማንቂያ ደዎላቸው ጋር አዋህዶ እንደሚከተለው አብስሯቸው ተሰውሯል፤ "እንግዲህ የመጀመሪያው የምትሄዱበት ሰው ጋር **ትዕግስትን** ታጥቃችሁ ሂዱ፤ ሁለተኛው ሰው ጋር **ማስተዋልን** ይዛችሁ ተጓዙ፤ ሦስተኛው ሰው ጋር ደግሞ በ**ፍቅር** ድረሱ፤ ጥበቡንም ለትውልድ አስተጋቡ" (ኤልያስ፣ 2010፤ 178)፡፡

ይህ የልዕለተፈጥሮ ኃይል ለጊዜውም ቢሆን ይሰወር እንጅ፤ በየጊዜው ብቅ እያለ በጉዟቸው ወቅት ከሚያጋጥሟቸው መልካም ያልሆኑ እና ለተጋድሏቸው እንቅፋት ከሆኑ ነገሮች ሁሉ በተለያየ መልክ ያድናቸዋል፤ ወደሚፈልጉት አቅጣጫም ይመራቸዋል፡፡ ለአሁኑም ቢሆን ተጋዳሊያኑ የሚሄዱባቸውን ልዩ የበረከት ቦታዎች በግልጽ እንዲህ አብስረዋቸዋል፤ "[…] በቅድሚያ በእኛ በኩሽ ቋንቋ ‹**ወል**› ወይም አንድነት ብለን ወደሰየምናት ወደ ወሎ ታቀናላችሁ፡፡ ቁራኒ ከሚባል ቦታ አክረም ከተባለ ሰው ጋርም ታርፋላችሁ፡፡ እርሱም ሼህ ከድርን እንዲያገናኛችሁ ጠይቁት…" (ኤልያስ፣ 2010፤ 178)፡፡ ይህ የልዩ ቦታ ጥቆማ ደግሞ፣ ተጋዳሊያኑ ለበረከት የሚሄዱባቸውን ስፍራዎች ቀድመው እንዲያውቋቸው እና በጉዟቸው ወቅት የሚያጋጥሟቸውን አድካሚ ውዝግቦች ለመቀነስ ያግዛል፡፡

በሚታዊ ሥርዓት ውስጥ ገና ከመጀመሪያው ቅጽር በር ላይ የሚገኙትን ቅጽር ጠባቂዎች ለማለፍም ሆነ ወደዋናው ተጋድሎ ለማለፍ እና ድልን ተቀዳጅቶ ለመመለስ የአንዳች ልዕለተፈጥሮ (ልዕለሰብዕ) ኃይል እርዳታ ሊኖር ግድ ነው፡፡ ታዲያ፣ ይህ የልዕለተፈጥሮ እርዳታ እንደጥሪው ሁሉ እንዲሁ በውል በማይታወቅ መልኩ (unconsciously) እና በአጋጣሚ ሊበረከት እንደሚችል Campbell ያስረዳሉ፡፡

በኢቶዮጵ ልቦድ ውስጥ የምናገኛቸው ተጋዳሊ ገፀባህርያት በእያንዳንዷ የተጋድሎ እና የሕይወት ጉዟቸው ሁሉ ሲከፋቸው አጽናኝ፣ ሲደክማቸው አበርቺ፣ ሲፈሩ አደፋፋሪ፣ ሲጨነቁ አማካሪ የልዕለተፈጥሮ እርዳታዎችን ይቸራሉ፡፡ ቀድመው ታጭተዋል እና በዓለማዊ ሕይወታቸው ሳይቀር ከመጥፎ ነገር ሁሉ ይጠብቋቸዋል፡፡ ለዚህ ደግሞ፣ ኢትኤል ትልቅ ማሳያ ነው፡፡

የልቦለዱ ታሪክ እንደሚያወሳው፣ ኢትኤል በአንድ ቀን ስህተት "አርፍደህ መጥተሃል" በሚል ጭራ ስንጠቃ ድጋሜ ተመልሶ ወደ ዋርድ እንዳይመጣ በዶ/ር አበራ (እሳቱ) ማስጠንቀቂያ ብቻ አይደለም፤ ከነጭራሹ ዝር እናዳይል የማባረሪያ ቂጣን ተቀብሏል፡፡ አሁን አንዳች ተዓምር ካልተፈጠረ በስተቀር ኢትኤል እድሜውን በሙሉ ሲደክምበት የኖረው ትምህርቱ አደጋ ላይ ወድቋል፤ የእሱም ጭንቀት በእጅጉ አይሏል፡፡

ከሁሉም በላይ ደግሞ የፈተና ቀን ሊፈጠር የሚችለውን ነገር ሲያስብ የሁልጊዜ ውጥረቱን ያባብስበታል፡፡ ይህ ውጥረቱም የመጨረሻውን የቃል ፈተና "ዶ/ር አበራ ይሰጠኛል" ከሚል ስጋት የመነጨ ነው፡፡ እውነትም "የፈሩት ይደርሳል" ነውና ነገሩ፤ ካልጠፋ የኢትኤል ስም ከዶ/ር አበራ የተፈታኝ ዝርዝር ውስጥ አንዱ ሆኗል፡፡ ይህ እንደሆነ ባወቀ ጊዜ ደግሞ በጭንቀት ላይ ጭንቀት፣ በፍርሃት ላይ ፍርሃት፣ በስጋት ላይ ስጋት … ብቻ ሁሉም ነገር ይምታታበታል፡፡

ተራው ደርሶ በድጋሜ በመብረቃማ ድምፁ አስፈንጥሮ እስኪያስወጣው፣ አሊያም ሌላ ተዓምር የሚፈጠር ከሆነ መልካም አጋጣሚውን ለመጠቀም በፈተናው ቀን ተስፋ ሳይቆርጥ ቆሞ እየጠበቀ ይገኛል፡፡ በዚህ ሁኔታ ላይ ሳለ የሆነውን ደግሞ ልቦለዱ እንዲህ ያስነብበናል፤

> ከዚህ ከአቅሙ በላይ በሆነ ፈተና ፊት ብቻውን እንደሆነ ሲሰማው እጅግ ተጨነቀ፤ ወዲያው ግን ውስጡ በአንዳች ሃይል ሲሞላ ተሰማው፡፡ ከህሊና የጠነከረች ጥሪ፣ ዘማም ዜማ ያለው አፅናኝ መልዕክት፤ የእኚያ ባህታዊ ሰው ንግግር በአዕምሮው ውስጥ ያስተጋባ ጀመር፡፡ "[…] ብቻውን ሆኖ ፈተና ያስጨነቀውንም ሁሉ እግዚአብሔር ያግዛል፡፡ […]" (ኤልያስ፣ 2010፤ 181-182)፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ አምኖት የሚለምነው ፈጣሪ ሁልጊዜም አብሮት ነውና፤ በአንዳች ምትሃት እንደመርግ የተጫነውን ፍርሃቱን የሚገፍ፣ ጭንቀቱን የምያስረሳ ብስራት ከፕሮግራም አመቻቹ ሬዝደንት እንዲህ ይሰማል፤

> "ምንድን ነው ጄለሴ ያጠናኸውን እየሸመደድክ ነው እንዴ?" አለው፤ […]
> "አይ ትንሽ ፈርቼ ስለነበር ዕየጸለይኩኝ ነው፡፡" […]
> "እንግዲያውስ ጸሎትህን ሰምቶሃል፡፡" […]
> "እንዴት?" […]
> "ካንተ በፊት ዶ/ር አበራ ጋር የተፈተኑት ሁሉም ልጆች እያለቀሱ ነበር የወጡት፡፡ አንተን ልጠራህ ስሄድ ግን ዶ/ር አበራ ትንሽ አሞት ወጥቶ […] እሱ ጋር የተመደቡት ተማሪዎች ሌላ ሰው እንዲፈትናቸው ነግሮኛል፡፡ […]" (ኤልያስ፣ 2010፤ 182)፡፡

ከኢትኤል ባለፈ ደግሞ፣ አብረውት ለታላቅ ተጋድሎ ተመርጠው የተጠሩት ስድስት ያህል ጓደኞቹም በአንድም ሆነ በሌላ ምክንያት የቃል ፈተናቸው የተሻለ እና ጥሩ ሚባል፣ ሁሉንም የተደሰቱበት አይነት ውጤት ነበር፡፡ ምንም እንኳን የኢትኤልን ያህል ባይሆነም፣ ፈተና ነውና ሌሎቹም ቢሆኑ ለፈተና ከመቅረባቸው አስቀድሞ ማሰባቸው አይቀርም፡፡ ነገር ግን አንዳች ኃይል በግልፅም ሆነ በህቡዕ ውጤታቸውን አስተካክሎ፣ ወደፊት ላለው አንድ አይነት መንፈሳዊ ተጋድሎ ተመሳሳይ ሃሳብ እንዲያስቡ የሚያደርግ ውጤት እንዲያስመዘግቡ አግዟቸዋል፤ "የቃል ፈተናው ለኢትኤል ዶርም 6 አባላት ጥሩ የሚባል ሆኖ ነበር ያለፈው (ኤልያስ፣ 2010፤ 198)፡፡

የልዕለ ተፈጥሮ እርዳታ ከሚገለጽባቸው በርካታ እረቂቅ እና ጉልህ ጉዳዮች መካከል መንገድ ማሳየት እንደሆነ በተደጋጋሚ ጠቁሜያለሁ፡፡ በዚህ መሰረት፣ በኢቶዮጵ ልቦለድ ውስጥ የምናገኛቸው እነዚህ ስድስት ተጋዳሊ ገፀሰዎች ጉዟቸውን በይፋ ሲጀምሩ እና ወደመጀመሪያው የተጋድሎ ቅጽር መግቢያ በር ሲያመሩ፣ ከነአክረም ቤት ጀምሮ የልዕለ ተፈጥሮ መልዕክተኛ በሆነች በአንዲት ግመል እየተመሩ መንገዳቸውን ቀጥለዋል፡፡ ከግመሏም በኋላ ደግሞ በአንድ "ደረሳ" (የሼህ ከድር ተማሪ) ተቀብሎ ቢያንስ እንኳን አቅጣጫቸውን እንዲጠብቁ አቅጣጫ ጠቋሚ፣ መንገድ አመላካች እንደሆኗቸው ከልቦለዱ ታሪክ (204-209) ውስጥ በግልጽ ሰፍሮ እናገኛለን፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የቀረበለትን ጥሪ በእምቢኝታ የቀረውን የቶላን ታሪክ ያየን እንደሆነ፣ በሞት እና በሕይወት መካከል የምትጣጣረው ሕይወቱ ዳግም ወደ ህላዌ የተመለሰችባቸውን ሁለት አጋጣሚዎች እናገኛለን፡፡ አንደኛው እና የመጀመሪያው፣ ቶላ በደረሰበት ከባድ አደጋ ምክንያት ብዙ ደም ፈስሶታል፡፡ በመሆኑም ሕይወቱን ለማትረፍ ከታሰበ ቢያንስ እንኳን ከእርሱ የደም ወገን ጋር ተዛማጅ እና በቂ የሆነ ደም መገኘት አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው፡፡ ይሁን እንጅ ለህክምና በተወሰደበት ሆስፒታል ባለው

የደም ባንክ ውስጥ ያለችው ደም አንድ አይነት የደም ወገን "ሲ ፕላስ" [ቀጥታ ከምንጩ] ብቻ ነበረች፡፡

ቶላ ግን መቸም አንድ ጊዜ ለቅድስና እና ለክብር ታጭቷልና ፈጣሪ አጋጣሚውን አስመስሎ የእርሱን የደም ወገን ከዚች ብቸኛ ጭላጭ ደም ጋር ተመሳሳይ አድርጎታል፤

> "በእናትህ አንድ ‹አክሲደንት› አለ፤ ቶሎ ይህንን ደም ‹ብለድ ግሩፕ እና ክሮስ ማች› ሰርተህ ደም ካለ እይልኝ፤" አለ ቢሊሱማ፤ […]
>
> "ውይ ያለው ሶሰስት ‹ቢ ፕላስ› [ስህተት ከምንጩ] ብቻ ነው፤ […]
>
> […] "እድለኛ ነህ፤ የሱም ደም ቢ ፕላስ ነው […] ማች አግኚቻለሁኝ [ስህተት ከምንጩ]፤" […] (ኤልያስ፣ 2010፤ 224-225)፡፡

ይህ ተዓምርም ብቻውን በቂ አልነበረምና፤ ሌላው እና ሁለተኛው ደግሞ፣ የኃኪሞቹ ሁሉ በተገቢው መንገድ እየሄደ ቢሆንም፤ ቶላ ግን ከገባበት የህመም ሰመመን ውስጥ ከቶውንም ሊነቃ አልቻለም፡፡ ስለሆነም ይህን ሁሉ ያደረገ የልዕለተፈጥሮ እረዳት በመልዕክተኞቹ (በኃኪሞቹ) ሥራ ተጠራጥሯልና፤ ሌላ ልዕለሰብዕ ለማንም ሳይገለጽ የራሱን እገዛ ይዞ፣ ከውድቅት ሌሊት 9፡15 ድንገት ብቅ ብሎ፣ ቶላን ከህመሙ ብቻም ሳይሆን ከለምጹ ሁሉ ያነጻው፡፡ የሚከተለው ከልቦለዱ በቀጥታ የተወሰደው ማስረጃ ይህን ሃሳብ ያጸናዋል፡፡

> ውድቅት 9 ሰዓት ከሩብ ላይ ነበር አንድ ሰው ቶላ የተኛበትን ክፍል በር ከፍተው የገቡት፡፡ […] እራሱን የማያውቀውን ቶላ ትክ ብለው ተመለከቱና ቀይ ብልቃጥ አውጥተው በቁስሉ ላይ ያለው ፋሻ ላይ አፈሰሱት፡፡ ፋሻው ሲርስ የለበሱትን ረጅም ቡልኮ ሰብሰብ አድርገው አንድ የሰላጣ ስፋት ያለው ቅጠል አወጡ፡፡ ከዚያም የተለያዩ የጸሎት ቃላቶችን እያሉ ቅጠሉን ጭምቅ እያደረጉ የቶላ የቀኝ ትከሻ ቁስል ላይ ማንጠባጠብ ጀመሩ፡፡ ከአፍታ በኋላ ቶላ መንቃት ጀመረ፡፡ […] በድንጋጤ ከተኛበት ድንገት ቁጭ ብሎ አይኖቹን ገለጠ፤ (ኤልያስ፣ 2010፤ 225-226)፡፡

እንግዲህ ዋናው ለተጋዳሊነት መታጨት እንጅ፣ በዓለማዊ ሕይወት ውስጥ ሳይቀር የልዕለተፈጥሮ እርዳታ፣ በዚህ መልኩ ሊበረከት እንደሚችል መገንዘብ እንችላለን፡፡

በሚት ሥርዓት ወስጥ ለተጋድሎ ያልበቁ አንዳንድ ተጋዳሊያን ሁልጊዜም ቢሆን ፈተናን በብቃት የመወጣት እና እራሱን ለቅድስና ለማብቃት እንደዚሁም ለነባር ባህሉ እና ማኅበረሰቡ ዓርዓያ የመሆን እድል የለውምና፤ ተጋድሎው እየጠነከረ ሲሄድ ወደ ኋላ ለመመለስ አሊያም በዚያው ባለበት መቆም ሊያስብ ይችላል፡፡ ዮሴፍ ከሌሎቹ ተጋዳሊያን

በተለየ፣ ከጅምሩም ቢሆን ምንም አይነት የልዕለተፈጥሮ ቀጥታ ጥሪ አልተደረገለትም፤ ጥሪው **አጋጣሚ** ነበር እንጂ፡፡ ዓላማውም ከጓደኞቹ ጋር ዘና ለማለት ነበረና፤ ገና የመጀመሪያውን ቅጽር መግቢያ በር እንዳለፈ ያሰበውን ያክል ምቾት በቀላሉ ሳያገኝ በመቅረቱ ወደኋላ ለመመለስ መነሳቱን የልቦለዱ ታሪክ ይነግረናል፡፡ ይሁን እንጅ እንዳሰበው ያለምንም ውጤት የመጣበትን መንገድ አቆራርጦ መመለስ አልቻለም፡፡ እርሱ ለመመለስ ቢከጅለም እንኳን አንዳች ልዕለተፈጥሮ ኃይል በልቦናው ገብቶ የተዛባ ውሳኔውን በማጨናገፍ ዳግም ወደገድል፣ ወደፊት፤፣ እንዲገሰግስ አዙሮ አምጥቶታል፡፡

> የልዕለ ተፈጥሮ እርዳታ ለተጋዳሊያን የሚቀርብበት መንገድ እጅግ ብዙ፣ እረቂቅ እና ውስብስብ ስለመሆኑ በተደጋጋሚ አይተናል፡፡ በዚህ መሠረት ይህ የልዕለ ተፈጥሮ እርዳታ በአንዳች እረቂቅ ኃይል የዮሴፍን ልቦና ትዕግስት አስታጥቆ ለተጋድሎ እንዲዘጋጅ አድርጎታል፤ አቋርጦት ወደሄደው ቅዱስ ታሪክም መልሶ አምጥቶታል፡፡ "እስኪ ቅድም የሄድክበትን ምክንያት ንገረን ዮሴፍ አሉት ሼህ ከድር፤...ዮሴፍ አንገቱን እንደደፋ "...አሁን እራሱ እዚህ ለምን ተመልሼ እንደመጣሁኝ አላውቅም፡፡"... ተመልሰህ የመጣኸውማ ቀጣዩን ታሪክ መስማት እንዳለብህ ፈጣሪ ስላቀደልህ ነው፡፡ ... (ኤልያስ፣ 2010፤ 245-246)፡፡

## 3.2.4. የመጀመሪያውን መግቢያ በር ማለፍ

ቀደም ሲል "መለየት" በተሰኘው ርዕሰነገር ስር እንደጠቆምኩት፣ ፕ/ር እሴ ለታሪክ ምርምር ከትውልድ ሃገሩ ኢትዮጵያ ከወጣ ሁለት ያህል ዓመታትን እንዳስቆጠረ ታሪኩ ይነግረናል፡፡ አሁን ደግሞ በአንዳች አጋጣሚ ለታላቅ ተጋድሎ ዳግም ወደ ሃገሩ ኢትዮጵያ ተጠርቷል፡፡ ነገር ግን ኢትዮጵያ መግባት፣ እንደበፊቱ በድንገት እንደመውጣት ቀላል አልሆንልህ ብሎታል፤ የተጋድሎ ቦታው ይቺ ሃገር ናትና፡፡

በሚታዊ ሥርዓት ውስጥ ገና ከተጋድሎ ቅጽሩ መግቢያ በር ላይ የተጋዳሊያኑን ቁርጠኛነት፣ ውሳኔ እና ጥንካሬ በመፈተን እና በመመዘን ለጉዞው የሚያዘጋጁ ጠባቂዎቸች ይኖራ፡፡ እነዚህን ዘቦች አልፎ እንደገባ ግን በራሱ (በቀድሞ) ግዛቱ እና ተጋድሎውን በሚፈጽምበት ዓለም መካከል የተዘረጉ እምነቶች፣ ክብረበዓላት እና ልዩ ልዩ ሥርዓተባህሎችን የማግኘት ዕድል ይኖረዋል፤ (Campbell፤ 2004፣ Hunter፤ 2007፣ Hartman & Zimberoff፣ 2009 እና ሌሎቹም)፡፡ ስለሆነም ፕ/ር እሴ ገና ከሩሲያ ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ ከመጀመሪያው ቅጽር (አየር ማረፊያ) ያልጠበቀው ዱብዕዳ ተቀብሎታል፡፡

ፕ/ር እሴ ፍቅረኛ መስላ ከቀረበችው ሰላዩ ፍሬድሪካ ጋር ወደተጋድሎ ቦታው ኢትዮጵያ ሲመጡ ለወትሮው እንደሚታወቀው በአበባ ጉንጉን፣ አሊያም በ “እንኳን ደህና መጣችሁ” ደማቅ ጭብጭባ እና አቀባበል ወይም ደግሞ የዘመድ አዝማድ እና የጓደኞች አጀባ አልጠበቃቸውም፡፡ ይልቁኑ፣ ምንም ባልተጠበቀ ሁኔታ ገና ከአየር ማረፊያ በደህንነት ፖሊሶች ተይዘው ወዳልታወቀ ሥፍራ እንዲሄዱ ተገደዋል፡፡ ቀጥሎ ያለውን ታሪክ እንመልከት፤

“ፕ/ር እሴ ከፍሬድሪክ ጋር የቦሌ ዓለም-አቀፍ አየር ማረፊያ ሲደርሱ ዣንጥላ ይዘው የሚቀበሏቸውን ዘመድ አዝማዶች ባይጠብቁም ሽጉጥ የታጠቁ ደህንነቶችን ግን በጭራሽ አልጠበቁም ነበር” (ኤልያስ፣ 2010፤ 115)፡፡ እነዚህ የደህንነት ፖሊሶች የተጋድሎው የመጀመሪያ ቅጽር ጠባቂዎች በመሆናቸው እነዚህን ጠባቂዎች በየትኛውም መንገድ ማለፍ ደግሞ የተጋድሎው የመጀመሪያ ምዕራፍ ሆኗል፤ ከዚህ ጀምሮም ተጋድሎው በይፋ ተጀምሯል ማለት ነው፡፡

ፕ/ር እሴ ምንም እንኳን ገና የተጋድሎውን በር ከመርገጣቸው በከባድ ወንጀል ወይም በአሸባሪነት ተጠርጥረው በተጋድሎ ቅጽር ጠባቂዎች ወይም በደህንነት ሰዎች ተይዘው ወደማያውቁት ቦታ ቢወሰዱም፤ ከአስፈሪ ድባብ እና ምርመራ በኋላ በነጻ ተለቀዋል፡፡ ይሁን እንጅ በጥቂቱም ቢሆን በድንጋጤ እና ምቾት በሌሌው ጠረጴዛ ላይ ተኝተው እንዲያድሩ ግን ተገደዋል፡፡ ታዲያ በዚህ ሁሉ ፈተና መካል ተጋዳሊው አንዳችም መጥፎ ስሜት እና ተስፋ መቁረጥ ሳይታይባቸው የቅጽሩን ተባቂዎች ባስገረመ ትዕግስት እና ጽናት ፈተናቸውን በብቃት ተወጥተው ወደሚቀጥለው የተጋድሎ ግዛት ተሸጋግረዋል፤ “[…] ወንጀል የሌለበት ሰው እኮ አካሉ ቢታሰርም ህሊናው ነፃ ስለሆነ ፈገግታው ቀርቶ ለቅሶውም ይማርካል፡፡ አሉት ፈገግታ ሳይለያቸው፡፡ አርጋታቸው እንቆቅልሽ እንደሆነበት ማታ በኢንፎርሜሽን ባለሙያዎች ሲበረብሩ ያደሩትን ስልክ እና ላፕቶፓቸውን አስረከባቸው” (ኤልያስ፣ 2010፤ 142)፡፡

በ*ኤቶᵨጵ* ልቦለድ ውስጥ ያሉት ተጋዳሊ ገፀሰዎች ወደ ስምንት እንደሚደርሱ ቀደም ብየ ከመንደርደሪያየ ገልጫለሁ፡፡ በዚህ መሠረት ከፕ/ር እሴ በተጨማሪ ሌሎች ቁጥራቸው ስድስት የሚደርሱ ተጋዳሊ ልዑካን ለተመሳሳይ መንፈሳዊ እና ታሪካዊ ዓላማ ታጭተው በተለያዩ ጊዜያት በተደረገላቸው ጥሪ ተጋድሏቸውን ለመጀመር መነሻቸውን ከትምህር

ቦታቸው ከጅማ ዩኒቨርሲቲ አድርገዋል፡፡ እነዚህ ተጋዳሊያን ከሁሉ ነገር አስቀድሞ በልዕለተፈጥሮ አካላት አማካኝነት ዕጣቸው ተቆርጦላቸዋል፡፡ ስለዚህ ቀድመው የሚገለጽላቸውም መልካም ነገር በማሰብ ጉጉታቸው አንድ እና አንድ ወደፊት ብቻ ሆኗል (ምናልባትም ከዮሴፍ በቀር)፡፡ ዮሴፍም ቢሆን የተጋድሎው ዓላማ ልክ እንደሌሎቹ ሁሉ በይፋ አይገለጥለት እንጅ በጉዞው መደሰት፣ መዝናናት እንደሚኖር ስለገመተ እንደሌሎቹ ተጋዳሊ ጓዶቹ መጓጓቱ አልቀረም፡፡

የሆነው ሆኖ ይህ ከልባቸው የመነጨ ጉጉታቸው ሁሉም ተጋዳሊዎች በተጋድሎ ጉዟቸው ወቅት የሚገጥማቸውን ፈተና ሁሉ በብቃት ለመወጣት ቁርጠኛ እንዲሆኑ አስችሏቸዋል፤ እንደ አንድ ትጥቅ ሆኗቸዋል፡፡ ስለሆነም ሁሉም ወደፊታቸው የሚመጣውን ሁሉ ነገር ለመቀበል ስራሳቸውን ቀድመው አዘጋጅተዋል፡፡ የእነርሱ ታላቃ ዓላማ የጉዟቸውን የመጨረሻ ውጤት ማጣጣም ነውና፤ እርስ በእርስ እየተደጋገፉ ከጅማ አዲስ አበባ፣ ከአዲስ አበባ ወሎ፣ ከወሎ ቁራኒ ጉዞዋቸውን አድርገው ከመጀመሪያው ማረፊያቸው ከነ አክረም ቤት አድርገዋል፡፡

የተጋድሏቸው "ሀሁ…"ም ከዚህ ይጀምራል፡፡ የእስካሁኑ ጉዟቸው የቱንም ያህል እሩቅ ቢሆን በብዙ ነገር ታግዘዋልና ብዙም አልተፈተኑም፡፡ ስለዚህ ወደመጀመሪያው ተጋድሎ ቅጽር መግቢያ በር የሚያመራውን መንገድ ከነአክረም ቤት መነሻ ጀምረዋል፡፡ በእርግጥ ከዚሁ ቁራኒ፣ ከነአክረም ቤት ከመድረሳቸውም አስቀድሞ የነበረው የተጋድሎ መንገድ ቀላል የሚባል እንዳልነበረ የሚከተለው ታሪክ ያስረዳናል፤

> […] "ይቅርታ እዚህ አካባቢ የአክረምን ቤት ማግኘት እንችልይሆን?"
> "ዏ! ልጆች የአክረም ቤት የኸው አይደል፤ እኔደግሞ ባለቤቱ ነኝ፤ ምነው በደህና ነው?" […]
> […] "እፉ በሉን እናንተን ስንፈልግ በጣም ደክሞን ተስፋ ልንቆርጥ ስንል ስላገኘናችሁ ነው በጣም ደስ ያለን፡፡" […] (ኤልያስ፣ 2010፤ 203)፡፡

እንደ Hunter (2007) እና Campbell (2004) ገለጻ፣ የተጋዳሊያንን ጉዞ ጨለማ በማድረግ መንገዱ እንደልብ እንዳይታያቸው፣ እንደፈለጉ እንዳይረግጡ፣ እንዳሻቸው እንዳይዘሉ የሚያደናቅፍ እንቅፋት ሁልጊዜም ከፊታቸው አይጠፉምና፤ ከልቦለዱ ታሪክ በግልጽ እንደምንረዳው፣ ከነአክረም ቤት ካደሩ በኋላ ወደሚቀጥለው እና ወደመጀመሪያው ቅጽር መግቢያ በር የሚያመራው መንገድ ግን ጉዟቸውን የበለጠ አስቸጋሪ እና ውስብስብ ያደረገ ነበረ፡፡ ይሁን እንጅ ተጋዳሊ ልዑካኑ ታላቅ ጽናትን ታጥቀዋል እና በቀላሉ የሚበገሩ

አልሆኑም፤ "ንጋት አልፎ ለብዙ ሰዓታት ከተጓዙ በኋላ የማለዳው ብርድ በሐሩር ተተካ፡፡ ሙቀቱን ለመከላከል ግንባሮቻቸው ላይ ሽሚዝ እና ቲሸርቶቻቸውን ሸብ ያደረጉት… ጫካ ከዚያም ቁጥቋጦ፣ ከዚያም የገበሬ ማሳ፣ ከዚያም እልም ያለ ድንጋያማ ምድር… ሁሉም ይተካካል"፤ (ኤልያስ፣ 2010፤ 207)፡፡

እንዲያውም ከዚህ በከፋ ደረጃ ለአንዳንዶቹ እልህ አስጨራሽ ድካም የበዛበት ብቻም አልነበረም፤ ከባድ ህመም የታከለበት ታላቅ ፈተናም ጭምር ነበር እንጂ፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ ከድካማቸው ብርታት የተነሳ ማረፊያ ቦታ በእጅጉ ናፍቀዋል፤ ውሃ ጥሙም ቢሆን በድካማቸው ላይ "በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ" ሆኖባቸዋል፤ "[…] መሸትሸት እያለ ነበር፡፡ በዚያ ላይ ሁሉም ደክሟቸዋል፣ ርቧቸዋል፣ ውሃ ጠምቷቸዋል፡፡ […]" (ኤልያስ፣ 2010፤ 207)፡፡

ከልቦለዱ ታሪክ እንደምንረዳው፤ ፀሐዩ ምንም ያህል ቢጠጥር፣ ውሃ ጥሙ ምንም ያህል ቢባባስ፣ የራስ ምታቱ ምንም ያህል ቢበረታ፣ እንቅፋቱ ሁሉ ምንም ያህል ከመንገዳቸው ላይ ቢገተር ይህ ሁሉ ፈተና ግን እነዚህን ተጋዳሊያን ከታላቁ ጉዟቸው ፈጽሞ የመግግታት አቅም አልነበረውምና፤ በዚህ ሁሉ መካከል ጉዟቸውን ቀጥለው፣ የመጀመሪያውን ቅጽር መግቢያ በር አልፈው፣ የመጀመሪያውን በረከት ሼህ ከድር ከሚባሉ ልዕለሰብዕ ለመቀበል በቅተዋል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ በዚህ ሁሉ ጉዟቸው ወቅት ቢያንስ እንኳን መንገዱን የሚመሩ፣ "አይዞህ ባይ ውሃ ያሻግራል" እንዲሉ፤ በአንደበታቸውም ቢሆን በአንዳች እረቂቅ ትዕምርታቸው አይዟችሁ፣ በርቱ የሚሉ የልዕለተፈጥሮ መልዕክተኛ ኃይላት አብረዋቸው አሉ፡፡

አዎ! በእነርሱ አልሸነፍ ባይነት እና በልዕለተፈጥሮ መንገድ መሪነት እነዚህ ተጋዳሊያን የመጀመሪያውን ቅጽር መግቢያ በር አልፈው ሌላ ረድኤት፣ በረከት እና አንዳንድ ፈተናዎች ካሉበት ሌላ ግዛት ውስጥ ገብተዋል፡፡ ገና ከጥሪያቸው ከተበሰራቸው ከመጀመሪያው እውነት ጋር ለመገናኘት ታድለዋል፡፡ ወደዚህ ግዛት ሲገቡም በልዕለሰብዕ አካላት ጥሩ አቀባበል ተችሯቸዋል፡፡ "[…] ከቀርከሃ [ስህተት ከምንጩ] በተሰሩ ኩባያዎች ትኩስ ወተት ተሰጣቸው፤ ሙልሙልም ተቆራርሶ በሰፌድ ቀረበላቸው፡፡ […]" (ኤልያስ፣ 2010፤ 210)፡፡

### 3.2.5. የዓሳ ነባሪ ሆድ

ይህ ክፍል ደግሞ በርካታ አስቸጋሪ እና ጥሩ ነገሮችን በአንድ አስተቃቅፎ የያዘ ግዛት ስለመሆኑ በቀደመው ምዕራፍ ላይ ጠቁሜያለሁ፡፡ ስለሆነም በኤቶሮጵ ልቦለድ ውስጥ የምናገኛቸው ስድስት ልዑካን ተጋዳያን ገፀባህርያት ከብዙ ልፋት እና ድካም በኋላ የመጀመሪያውን ቅጽር መግቢያ በር አልፈው ከዚህ ታላላቅ አበርክቶዎችን ከፈታኝ ሁነቶች ጋር አዋህዶ ከያዘ ክፍል (የዓሳ ነባሪ ሆድ) ውስጥ ገብተዋል፡፡ በዚህ ግዛት ውስጥ ደግሞ እነዚሁ ተጋዳሊያን ከአንድም-ሁለትጊዜ፤ ከሁለትም -ለሦስተኛ ጊዜ በርካታ ጸጋዎችን ከበርካታ ድካም፣ ፈተና እና ስቃይ ጋር ተቀብለዋል፡፡

ይህ እንግዳ እና አዲስ ስፍራ በርካታ ጸጋዎችን (treasures) እና አደገኛ ተፋላሚዎችን በአንድ ላይ አካቶ የያዘ እንደሆነ ይታመናል፡፡ በዚህ መልኩ ሁለት ተቃራኒ ጉዳዮችን በአንድ ላይ አዋህዶ የያዘ ቦታ ደግሞ፣ በሩቅ አገር፣ በጥቅጥቅ ደን (ጫካ)፣ ከምድር በውስጥ ወይም ከሰማይ በላይ ባለ ግዛት፣ ሁልጊዜም የተለየ እና አዲስ መልክ ያለው እንዲሁም የተለያዩ ፍጡራን መገኛ (መኖሪያ) በሆነ ቦታ፣ ባልተለመዱ እና ባልተጠበቁ ስቃዮች፣ በልዕለሰብ ተግባራት እና እንግዳ በሆነ ብርሃን ይገለጻል ወይም ይወከላል (Campbell፣ 2004)፡፡

አዎ! መልካም እና የተቀደሰ ነገርን ከአሰልቺ ድካም፣ ደስታን ከምቾት እና እረፍት እጦት ጋር አዋህደው እየተቀበሉ ይገኛሉ፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ፣ ምንም እንኳን ህብስቱ በቂ፣ የሚሰጣቸው ታሪካዊ እና መንፈሳዊ እውቀት አመርቂ፣ ቢሆንም ሙሉ በሙሉ በምቾት ለመሞላቀቅ አሊያም ልክ በነባሩ ዓለም ላይ በለመዱት መልኩ የድሎት ኑባሬን ለመግፋት አልታደሉም፡፡ ይልቁንም አሁን ባሉበት ዓለም ውስጥ ከነባሩ ዓለም በተለየ መልኩ የማያውቋቸው፣ ያልለመዷቸው ፈታኝ ሁነቶች መከሰታቸውን ቀጥለዋል፡፡ ማስረጃ እንመልከት፤ "… ከዋሻው ውስጥ በተነጠፉ ሰሌኖች ላይ ተደርበው የተነጠፉት ሰፋፊ የፋርስ ምንጣፎች ላይ ነበር አስመራ [ስህተት ከምንጩ] ድርድር ሰርተው በተርታ የተኙት፡፡ […] ያ ልስላሴ እና ሙቀት ለለመደው ገላቸው የሚመች መኝታ አልነበረም (ኤልያስ፣ 2010፤ 229)፡፡

ይህ የዓሳ ነባሪ ሆድ የተሰኘ ግዛት የትኛውም ተጋዳሊ በነጻነት ብቻ ተንፈላስሶ የሚኖርበት የነጻነት ብቻ ዓለም አለመሆኑን ከላይ የተቀመጠው የCampbell ሃሳብ ያስረዳናል፡፡ ከዚህ በላይ እንዳየነው፣ ተጋዳሊን በዚህ ግዛት ውስጥ ከብዙ መልካም ነገሮች በስተጀርባ ለሌሎች አስቸጋሪ ፈተናዎችም ይጋለጣሉ፡፡ የብስራት ታሪኮችም እንዲሁ በሚመች ሁኔታ ብቻ አልቀረቡላቸውም፡፡ በማይመች መኘታ እየተኙ፣ ለአድካሚ ሰዓታት እየተቀመጡ፣ በብርድ እየተንቀጠቀጡ ወዘተ የመጡለትን ቅዱስ ታሪክ ማዳመጥ የተጋድሏቸው አንዱ ትግልም፣ ውጤትም ነው፤ “… ለሶላት የተነሱት መርየም እና ዘይኔ፣ ናያድ፣ ኢትኤል እና አብርሃምን ቀሰቀሷቸው፡፡ ሁሉም ብርዱ እያንቀጠቀጣቸው ተነስተው ሼህ ከድርን ከበቧቸው” (ኤልያስ፣ 2010፤ 231)፡፡

ተደጋግሞ እንደተነሳው ይህ ክፍል ሁለት ተቃራኒ ነገሮች (ጥሩ እና መጥፎ) ተቀላቅለው የሚገኙበት በመሆኑ፤ በአጠቃላይ ሁሉም ተጋዳሊ ገፀባህርያት በየቅጽሮቹ ሲገቡ ፈተናዎችም እንዲሁ እየተባባሱ እና የበለጠ ሀአስቸጋሪ እየሆኑ ይመጣሉ፡፡ ስለሆነም አሁንም ለመጨረሻ ጊዜ ሌላ በረከትን ከብዙ ከድካም ጋር የሚያገኙበት ቀጽር ውስጥ ናቸው፡፡ አሁንም እንደወትሮው ሁሉ ታላቅ በረከት ከእነዚህ አሰልቺ ትግሎች ጋር ቀርበውላቸዋልና፤ በሁለት ስሜቶች ውስጥ ትግላቸውን ቀጥለዋል፡፡ “እነኢትኤል ፊታቸው ላይ የደስታ እና የድካም ስሜት እየተደባለቀ እርስ በእርስ ተያዩ” (ኤልያስ፣ 2010፤ 231)፡፡ ነገር ግን ምንም ያህል ፈተናው ቢበዛባቸውም ወደኋላ አልተመለሱም፤ ይልቁኑ በብቃት እያለፉ የበረከቱ ተቋዳሾች ለመሆን በቅተዋል፡፡

በአጠቃለይ በእንዲህ መልኩ በሁለት ስሜቶች መካከል በማለፍ ገና በጥሪው ላይ የተበሰሩላቸውን ቦታዎች ሁሉ አዳርሰው ሁሉንም በረከቶች አግኝተዋል፡፡ በእርግጥ እነዚህ ሰባት ተጋዳሊያን ሁሉም ተመሳሳይ የሆነ በረከትን ለማግኘት እኩል ጽናት አልነበራቸውም እና ያገኟቸው ትሩፋቶችም እነዲሁ ተለያዩ ሆነዋል፡፡ ለምሳሌ ዘይኔ ገና ከመጀመሪያው የበረከት ቦታ ከሼህ ከድር ጋር ቀርቷል፤ ዮሴፍ የመጀመሪያውን እንደምንም ጨርሶ ወደ ሁለተኛው ቦታ ለመሄድ በመንገድ ላይ ሳለ ተጠልፎ ቀርቷል፤ ቶላ ወደመጀመሪያው ቅጽር ሳይገባ በአቋራጭ ከሁለተኛው ቅጽር ውስጥ ገብቶ ቀርቷል፤ ናያድም ቢሆን ምንም እናኳን እስከ ሦስተኛው እና ታላቅ መገለጥ ያለበት ስፍራ ቢደርስም፣ ለሙሉ ጸጋ መብቃት አልታደለምና የአባ ኤልካኖን ማረጋገጫ ወደኋላ ትቶ ወጥቷል፡፡ ስለዚህ የመጨረሻውን ጨምሮ ሦስቱንም ጣፋጭ እና አሰልቺ ድሎች

የተጎናጸፉት ሦስቱ ተጋዳሊ ልዑካን ኢትኤል፣ አብርሃም እና መርየም እንደሆኑ የልቦለዱ ታሪክ ይነግረናል፡፡ ይህ ደግሞ የዚህን ግዛት መልከ ብዙነት ያጎላዋል፡፡

በመጨረሻም እነዚህ ሦስት ተጋዳሊያን ለአዳኝነት እና ለፍቅር ተምሳሌትነት ጸጋዎች በቅተዋል "[…] በራማ ተራራ እንዳሉ የብርሃን ጸዳል ፊታቸው ሲያንጸባርቅ፡፡ [ስህተት ከምንጩ] ኢትኤል፣ አብርሃም እና መርየም ወደ ሰማዩ ቀና አሉ፡፡ ከዚህ በፊት ታይቶ የማይታወቅ ደማቅ ቀስተደመና ሰማዩ ላይ ተዘርግቶ ነበር" (ኤልያስ፣ 2010፤ 344)፡፡ እንደ (Campbell፣ 2004)፣ ይህ የዓሳ ነባሪ ሆድ እንግዳ በሆነ ብርሃን ይገለጻል ወይም ይወከላል፡፡ በተጨማሪም "ኢትኤል ከዚህ ሰዓት ጀምሮ አንተ የ‹‹ኤቶዮጵ››ን መንፈስ አንግበሃል"፤ (ኤልያስ፣ 2010፤ 359) ተብሎ ታላቅ ተክህኖ ተሰጥቶታል፡፡

ከእነዚህ ተጋዳሊያን በተጨማሪ ደግሞ በዚህ ክፍል ውስጥ ታላቅ ድል እና ፈተናን የሚጋፈጡት ፐ/ር እሴ ናቸው፡፡ በልቦለዱ ውስጥ እንደሰፈረው፣ ከብዙ ትግል እና ፈተና በኋላ ፐ/ር እሴ ወደመጨረሻው የተጋድሎ ስፍራ አክሱም ሐውልት ስር መዳረሻቸውን አድርገዋል፡፡ አሁን የመጨረሻውን የተጋድሎ ድል የሚቀዳጁበት ቦታ ደርሰዋልና በቀጥታ "ድብቅ ታሪክ አለ" ወደተባለበት ቦታ ገብተዋል፤ ታላቋ ተፋላሚያቸው ፍሬድሪካም አብራ እግር እግራቸውን እየተከታተለቻቸው ነው፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ፍሬድሪካ አሁን የመጨረሻውን እርምጃ ለመውሰድ የተቃረበችበት ጊዜ ላይ ነች፡፡ እንዳሰበችው በወርቅ የተሞላ በርሜል፣ አሊያም እንቁ አልቻለችም፤ ስለላዋ ሁሉ የታሰበውን ያህል ፍሬ ባለማፍራቱ ተበሳጭታለችና ለበቀል ቆርጣ ተነስታለች፡፡

በዚህ መካከል ከዚያ ሚስጥራዊ ስፍራ፣ ታላቅ መንፈሳዊ እና ታሪካዊ ሁነቶች ካረፉበት ቦታ፣ ከዚያ ታላቅ የኢትዮጵያ መድህን ከሆነ ጨለማ ቦታ ከግዙፉ የአክሱም ሐውልት ስር ታላቅ ጦርነት ተፈጥሯል፤ በፍሬድሪካ እና በመድኃኔ ሕይወቱ ፐ/ር እሴ መካከል፡፡ ይሁን እንጅ ፐ/ር እሴ በአንዳች ኃይል ታግዘውም ቢሆን ድል አድርገው፣ "አክሱም ስር ያለውን በር መክፈት ማለት የእያንዳንዳችንን እምነት መክፈት ማለት ነው" (ኤልያስ፣ 2010፤ 338) ብለው የተዘጋውን ሚስጥራዊ ስፍራ ከፍተው፣ ለኢትዮጵያውያን ዘለአለማዊ ህልውና እነሆ መሠረት ሆነዋል፡፡ የሚከተለውን ከልቦለዱ ላይ የተቀነጨበ ታሪክ እንመልከት፤ "(ምንም አይነት የሚስጥር ቁልፍም ሆነ ድብቅ ሃብት የለም፤ እቅድሽን ከመጀመሪያውም አውቄው

ነበር፡፡ ለማነኛውም እውነታውን ተቀበይ፤ በወርቅ የተሞላ ሳጥን ለመክፈት ሳይሆን የተዘጋ መንገድ ልከፍት ነው የመጣነው!)" አሉና… (ኤልያስ፣ 2010፤ 332)፡፡

## 3.3. መነሳሳት

### 3.3.1. የምርመራ ወይም የሙከራ መንገድ

ከእነዚያ ሰባት ተጋዳሊያን መካከል ወደመጨረሻው ቅጽር ለመዝለቅ የሚታገሉት አራት ተጋዳሊያን (ኢትኤል፣ ናያድ፣ አብርሃም እና መርየም) ብቻ ቀርተዋል፡፡ እነዚህ ተጋዳሊያን በየጉዟቸው መካከል ጉዟቸውን የሚያጠናክሩ ትሩፋቶችን እንደሚያገኙ ሁሉ ሌሎች እንቅፋቶችም እንዲሁ አብረው ይጋረጡባቸው ቀጥለዋል፡፡ በእርግጥም የተጋድሎ ጉዞ አንዱ መገለጫው ደስታ እና ሃዘን፣ ጥሩ እና መጥፎ፣ ስቃይ እና ተድላ ወዘተ በአንድ ላይ ተቀላቅለው የሚገኙበት ስለመሆኑ እየታወቀ የመጣ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም እነዚሁ አራት ተጋዳሊያን በበለጠ የሚፈተኑበት እና የሚመረመሩበት ወቅት ደግሞ ከሁለተኛው እና ብዙም ድካም ካስተናገዱበት አስደሳች ጸጋ በኋላ ሆኗል፡፡ ስለዚህ አሁን እጅግ ፈታኝ ከሆነው የተጋድሎ መንገድ ላይ ደርሰዋልና ይህንን ፈተና በብቃት እና በታላቅ ጽናት መወጣት ደግም በእጅጉ ይጠበቅባቸዋል፡፡

እነዚህ አራቱ ተጋዳሊያን መነሻቸውን ጅማ ዩኒቨርሲቲ አድርገው፣ ወደ ወሎ አቅንተው፣ ቁራኒ አካባቢ ከሼህ ከድር የመጀመሪያውን ጸጋ ተጎናፅፈው፣ ወደ ወሎ ኦሮሞ አካባቢ አሳልጠው የኦቦ አራርሳን መግለጫ ተጎንጭተው፣ አሁን ደግሞ በወልድያ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ አንዳች ዱብ ዕዳ ከፊታቸው ላይ ተደንቅሯል፤ የደህንነት የፖሊስ አባላት በአሸባሪ ሃይል ጠርጥረዋቸው ለታላቅ ምርመራ ፈልገዋቸዋል፡፡ ምርመራው ደግሞ ግፍተራ፣ ዱላ የተቀላቀለበት ነው፡፡ አዎ! አሁን ገና ከመነሻው በልዕለተፈጥሮ አካላት የተነገራቸውን ታላቅ ማስተዋል መታጠቅ ግድ ሆኗል፡፡ ቀጥሎ ከልቦለዱ በቀጥታ የተወሰደውን ማስረጃ እንመልከት፤

> "እስኪ መታወቂያ ይዛችኋል?" አለ ከአክሎግ ጋ አብሮ የመጣው ፖሊስ፤ …
> "የጅማ ካምፓስ ተማሪዎች ወልድያ ድረስ ምን ሊሰሩ ነው የመጡት?" አለ አክሎግ…
> "አይ ላስረዳህ እችላለሁኝ" ብሎ ኢትኤል ሊናገር ሲል… ገፍተር ሲያደርገው ከኋላው የነበረ ጣውላ አደናቀፈውና በጀርባው ወደቀ፡፡…
> "… አሁን በስርዓቱ ተከተሉኝና ወደጣቢያ እንሂድ"

> “… እስኪጣራ ዛሬ ወልድያ ማረሚያ ቤት ያድራሉ፡፡” አላቸው፡፡… (ኤልያስ፣ 2010፤ 308)፡፡

እንደ Campbell (2004)፣ *ሚታዊ ተጋዳሊያን የመጀመሪያውን ቅጽር መግቢያ በር ከተሻገሩ በኋላ ወደ አዲስ እና ወደተመኙት መልክዓምድር እንዲሁም አወዛጋቢ የሆነ ቅጽር ወዳለው ስፍራ የሚንቀሳቀሱበት ምዕራፍ ነው፡፡ በዚህ ግዛት ውስጥም እንደዚሁ ተጋዳሊያኑ የሚደረግባቸውን ምርመራ ወይም የሚቀበሉትን የሙከራ ፈተና በብቃት መወጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህን ፈተናቸውን ተከትሎ የሚመጣውን ነገርም ለመቋቋም እራሳቸውን የበለጠ የሚያዘጋጁበት ክፍልም ነውና፤ እነዚህ አራት ተጋዳሊያን ከታላቅ ተስፋ መቁረጥ ጋር ተፋጠዋል፡፡ ሁሉም ነገር መንገዱን ስቶ እንዳሰቡት፣ እንዳቀዱት፣ እንደ ህልማቸው ባለመሆኑ ፈርተዋል፤ በእጅጉም ተጨንቀዋል፡፡*

*ይህ ክፍል ሁልጊዜም ቢሆን እንደወርቅ በእሳት መፈተንን፣ የሚጠይቅ እጅግ አስጨናቂ እና ተስፋ አስቆራጭ፣ ግን ደግሞ ለመውደቅም ሆነ ለማለፍ እጅግ ወሳኝ የሆነ ግዛት ስለመሆኑ ከፍ ሲል የተቀመጠው የ* Campbell (2004) *ሃሳብ ታላቅ ምስክር ነው፡፡ እነዚህ ተጋዳሊያንም ድንገት ባጋጠማቸው ወህኒ የመወርወር አደጋ ከምንም በላይ አስጨንቋቸዋል፤ አስፈርቷቸዋል፡፡ ማስረጃ እንመልከት፤*

> *…ህልማቸውን ማመናቸው፤ ሃገር አቋርጠው መምጣታቸው እና እውነትን መፈለጋቸው ልክ አይደለም ብለው እስኪጠራጠሩ ድረስ ፈርተዋል፤ ትምህርታቸው፣ ተስፋቸው፣ ቤተሰቦቻቸው ልፋት… ሁሉም ጥያቄ ውስጥ ገብቷል፡፡ የእስር ቤቱ ሁኔታ በእርግጥም ተስፋ አስቆራጭ ነበር፡፡* … (ኤልያስ፣ 2010፤ 309)፡፡

እንደ Campbell *ሃሳብ ይህ ክፍል በዚህ መንገድ የተወሳሰበ ሊሆን ስለሚችል ሁልጊዜም ቢሆን የአንዳች ልዕለተፈጥሮ እርዳታ ከተጋዳሊያኑ ጋር አብሮ ሊሆን ይገባል፡፡ በስተመጨረሻ እነዚህን አራት ተጋዳሊያን ነጻ ያወጣቸውም ይኸው ነው፡፡*

## 3.3.2. ሴትነት እንደ ማሳሳቻ ፈተና

በእርግጥ Campbell (2004)፤ *በሚታዊ ሥርዓት ውስጥ ከሴትነት ጋር በተያያዘ የሚሰጠው መመዘኛ፣ እጅግ አስቸጋሪ የሆኑ እና የወደፊት አጋር እንስትን የሚቃሙ አካላትን ከማሸነፍ ጋር ያያይዙታል፡፡ ታዲያ እንደ* Campbell *ሃሳብ፣ በዚህ ክፍል ውስጥ የአንድ ተጋዳሊ ጀብዱ የሚሆነው በጉዞው ውስጥ የሚያገኛትን እንስት ጣኦት ከክፉ ነገር*

ሲያስጥላት እና በአንዳች ረቂቅ መንፈስ ከዚች ጣኦት ጋር ሲጋባ ነው፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ ግን ከዚህ ለየት ባለ መልኩ ተጋዳሊው በአካል ሲያገባት እና በመንፈስ ሲፋቱ እንዲሁም እንስቷ እራሷ የተጋድሎ ጉዞውን በማደናቀፍ ስትታገለው በሚያሳይ መልኩ ቀርቧል፡፡

የልቦለዱ ታሪክ እንደሚያወሳው፣ ፕ/ር እሴ ፍሬድሪካን የተዋወቋት በተመሳሳይ የሥራ መስክ ሁለቱም ለታሪክ ጥናት በሚመስል መንገድ በአንድ አጋጣሚ በመገናኘታቸው ነበር፡፡ በእውንም ፕ/ር እሴ እና ፍሬድሪካ ግንኙነታቸው ከዚህም በላይ ሆኗል፡፡ በአንድ አጋጣሚ ይገናኙ እንጅ ፍቅረኛሞች ሆነው ትንፋሽህ ትንፋሼ፣ ገላህ ገላዬ፣ ሚስጥርህ ሚስጥሬ የሚባባሉ ፍቅረኛሞች ሆነዋል፤ "ፍድሪካ እስራኤላዊት የታሪክ አጥኚ መሆኗን ነግራቸው፤ በግብፅ የዛሬ አምስት አመት አገናኝቶ ያጣመራቸውም የዚሁ እየዞሩ ታሪክ የማጥናት አባዜያቸው ነበር" (ኤልያስ፣ 2010፤ 73)፡፡

ከዚህ ግንኙነታቸው በኋላ ሁለት ግለሰቦች ፕ/ር እሴ እና ፍሬድሪካ፣ ከፍቅር ባሻገር በጋራ በመሆን የታሪክ ምርምራቸውንም አጠናክረው ለመቀጠል ተስማምተዋል፡፡ ይሁን እንጅ ፍሬድሪካ ይህን ሁሉ ስምምነት የምታደርገው በእውንም በፕ/ር ፍቅር ከንፋ አልነበረም፤ ለዓላማዋ ስትል እያስመሰለች እንጂ፡፡ ይኸውም ሴትነቷን ተጠቅማ የፕ/ር እሴን ቅዱስ የሆነ ሃይማኖታዊ እና ታሪካዊ ተጋድሎ ከመሰለል እና ከንቱ ከማድረግ ባለፈም በኢትዮጵያ ይገኛል ተብሎ ስለተነገራት ሚስጥራዊ ቁልፍ ማወቅ እና በኢጇ ማስገባት ነው፡፡ ስለዚህ በአካል ከጎኑ እንዲያውም ከእቅፉ ስር በመሆን እና ሴትነቷን በመጠቀም "ጅብ እስኪይዝ" እንዲሉ፤ ይህን የቋመጠችለትን ሚስጥራዊ ቁልፍ ለማግኘት አብራው ትኳትናለች፡፡ ይሁን እንጅ እነዚህ ሁለት ግለሰቦች በመንፈስ እና በዓላማ ምንም የማይገናኙ እና ፍጹም ተቃራኒ በሆነ አቅጣጫ ተወጥረው በአካል ግን አብረው የሚጓዙ ባተሌ ነፍሶች ነበሩ፡፡

አዎ! ፍሬድሪካ በፍቅር ስም ሴትነቷን ተጠቅማ የምትፈልገውን ሚስጥር ለማግኘት ብቻ ስትል የቅዱሱን ተጋድሎ እንቅፋትነቷን ሥራዬ ብላ ተያይዛዋለች፡፡ ይህንን ሃሳብ ደግሞ የሚከተለው ታሪክ ያጸናዋል፤ " … በመሃከላቸው የሆነ መጠን የሌለው የመግባባት መንፈስ ሲፈጠር … ሁለት መሰረታቸው እጅጉን የተለያዩ ሰዎች እንዲህ ሲግባቡ ከጀርባ አንድ ነገር አለ ማለት ነው፡፡ አንድ ነገር…" (ኤልያስ፣ 2010፤ 75)፡፡

## 3.4. መመለስ

### 3.4.1. መመለስ አለመፈለግ

ተጋዳሊያን ወደ ምንጩ ዘልቀው በመግባት ወደ አንዳች አባታዊም ይሁን እናታዊ ጸጋ፣ ሰው ወይም እንስሳ፣ ሕይወት አልባ (ግዑዛን) አማልክት የሚያደርጉትን ፍለጋ ከጨርሱ በኋላ የቀድሞ ሕይወታቸውን (ማንነታቸውን) ከለወጠው ሽልማታቸው ጋር መመለስ ይጠበቅባቸዋል (Campbell፣ 2004)፡፡ ይሁን እንጅ በሚታዊ ሥርዓት ውስጥ ሁሉም ተጋዳሊያን አንዳች ቅድስናን በተመሳሳይ ሁኔታ  ይዘው ላይመለሱ ይችላሉ፡፡ ከዚያው ከተጋድሎ ስፍራው ወይም ከተጋድሎው ዓለም ውስጥ የሚያገኙት በረከት ስቧቸው፣ አሊያም ለሌላ ታላቅ ቅድስና ለመብቃት አስበው ወይም ደግሞ እንዲሁ በልዕለተፈጥሮ ኃይል ተመርጠው ለተጋድሎ በገቡበት ዓለም ውስጥ እዚያው ሊቆዩ ወይም ደግሞ ሊቀሩ ይችላሉ፡፡

ዘይኔ፣ በኢቶዮጵ ልቦለድ ውስጥ ካሉት ተጋዳሊ ገፀባህርያት መካከል አንዱ ሲሆን፤ ልክ እንደሌሎቹ ተጋዳሊያን ጓዶቹ ሁሉ ከሚማርበት ጅማ ዩኒቨርሲቲ ተነስቶ ወሎ-ቁራኒ ድረስ የመጀመሪያውን የተጋድሎ ጉዞ አድርጓል፡፡ እስካሁን እንዳየነው፣ ዘይኔ ለተጋድሎ ሲጠራም ይሁን ወደተጋድሎው ሲገባ ብቻውን አልነበረም፤ ከሌሎቹ አምስት ጓዶቹ ጋር እንጂ፡፡ ይሁን እንጅ ዘይኔ ከዚሁ የመጀመሪያው በረከት መገኛ ከሆነው ከሼህ ከድር ዘንድ መቆየትን ወይም ከተቀሩት ተጋድሎዎች መቅረትን መርጧል፡፡ ይህ ስፍራ የበረከት፣ የቅድስና፣ የሚስጥራት መገለጥ እንደሆነ በጥቂቱም ቢሆን ተረድቷልና መመለስ አሊያም ይህንን የበረከት ዓለም ጥሎ መውጣት ተስኖታል፤ ከዚሁ መቆየትን ሽቷል፡፡

> […] ሁሉም ተራ በተራ ተነሱ እና ወደዋሻው ገብተው ቦርሳዎቻቸውን ይዘው ወጡ፤ ዘይኔ ግን ከቦታው አልተነሳም ነበር፡፡
> “ምነው ዘይኔ ተነስ እንሂድ እንጅ? አለ ኢትኤል ወደ’ሱ መጥቶ፤
> “ስለህይወት ትርጉም እና ስለማንነቴ፣ ሃይማኖቴ እና ሃገሬ ያላዎቅሁት ገና ብዙ ሚስጥር እንዳለ እየተሰማኝ ስለሆነ እዚህ ቆይቼ … ዕውቀትን መማር እንዳለብኝ ወስኛለሁኝ” አለ […]፡፡ አብሯቻቸው እንዲሄድ ለማስማማት ቢሉት ቢሰሩት እሱ ግን ወይ ፍንክች አለ፡፡ ውሳኔው ቀድሞ ጸንቶ ነበር እና እንቢ አላቸው፡፡ […] (ኤልያስ፣ 2010፤ 259)፡፡

ዘይኔ ከዚህ ስፍራ ያገኘው አስተምህሮ ማርኮታል፤ በሕይወቱ ላይ አንዳች መሠረታዊ እና አዲስ ነገርን አግኚቶበታልና፤ አሁን በሕይወት ዘመኑ ብዙ የማያውቃቸው ነገሮች የነበሩ

መሆኑን ተረድቷል፡፡ ስለሆነም እራሱን የበለጠ ለማብቃት ወስኗልና፤ ገና በቅድሚያ ከገባበት የተጋድሎ ስፍራ ከሼህ ከድር ጋር መቅረትን ብሎም በርካታ ዕውቀት እና ጥበብ፣ ሌላ ተጨማሪ እውነት መቅሰምን ውሳኔው አድርጓል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ዮሴፍ ከሼህ ከድር ሦስት ታሪኮች መካከል የሁለተኛውን አቋርጦ ቢሄድም፤ በአንዳች ልዕለ ተፈጥሮ ሃይል ግፊት ዳግም ወደ ተጋድሎው እንደመጣ የልቦለዱ ታሪክ እራሱ ይነግረናል፡፡ ይሁን እንጅ ዮሴፍ አሁንም ቢሆን አንዳች ጸጋን ተክኖ ወደመጣበት ቤት፣ አካባቢ፣ ማኅበረሰብ መመለስን አልፈቀደም፡፡ ምክንያቱም ወደሚቀጥለው ተጋድሎ በሚደረገው ጉዞ ላይ ከአንድ በድንገት መኪና ላይ ከተዋወቀው ሰው ጋር ከጓደኞቹ ተቋርጦ መቅረትን መርጧል፡፡ አምስቱን የቀድሞ ጓደኞቹን ትቶ ሌላ እውቀት እና እውነትን ፍለጋ ቀሪ መንገዱን በድንገት ካገኘው ራስታ ጋር ለማድረግ ወስኗል፤ መወሰን ብቻም አይደለም፤ አድርጎታል፡፡

> "ጓደኞቼ እኔ ለእናንተ ጥሩ ምባል ጓደኛ እንዳልሆንኩኝ አውቃለሁኝ፤ ያን ሁሌ ጊዜ የሚያናዱ [ስህተት ከምንሬጩ] ጥያቄዎችን እየጠየቅሁኝ አዛ የማደርጋችሁ ለራሴ በውስጤ የሚፈጠሩብኝን ጥያቄዎች መመለስ ስላቃተኝ ነበር ብሶቴን እናንተ ላይ የምወጣው፤ ዛሬ ግን ማንም ሳይመልስልኝ በውስጤ ተፈጥረው የቆዩ ጥያቄዎችን ይህ ራስታ ሰው መልሶልኛል፡፡ [...]"
> "እና ከዚህ ራስታ ጋር ለመሄድ ወስኛለሁኝ ነው የምትለን?" አለ ናዖድ [...]
> "አዎ ወስኚያለሁኝ፤ [...]" (ኤልያስ፣ 2010፤ 283)፡፡

ከዮሴፍ እና ከዘይኔ በተጨማሪ ደግሞ ቶላ፣ በመጨረሻው የማንቂያ ደወል በይፋ ተጠርቶ ከሄደበት እና ወሎ አካባቢ ከሚገኝ ኦሮሞ ከሚባል ስፍራ ለታላቅ በረከት ታጭቶ ቢገባም ዳግም ግን ወደነባሩ ስፍራ ለመመለስ ሳይችል እንደቀረ የልቦለዱ ታሪክ ይነግረናል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ እዚሁ ስፍራ የተጋድሎውን በረከት ያገኘ ቢሆንም፤ ይህ በረከት ገና አላጠገበውም፤ አላረካውምና ነው፡፡ ስለዚህ እስከመቸ ድረስ እንደሆነ በውል ባይታወቅም ለጊዜው ግን እዚሁ መቆየትን እንጅ ይህን አካባቢ ለቆ ወደቀድሞው እና ወደነባሩ ቀየው ለመመለስ ከቶውንም አልፈለገም፡፡ ማስረጃ እንመልከት፤

> ኢትኤል ጥቅሉን መልዕክት ተቀብሎ ሁሉሙ ተነስተው ጉዞ ሊጀምሩ ሲሉ ቶላ ከተቀመጠበት ሳይነሳ ቀረ፡፡
> "ቶላ እንሂድ እንጅ ተነሳ፤" አለ ኢትኤል [...]
> "[...] አልሄድም ኢትኤል፤... እዚሁ ከእርሳቸው ጋር ቁጭ ብየ ስለራሴ ብዙ ማወቅ ያለብኝ ነገር እንዳለ ተረድቻለሁ፡፡" [...] (ኤልያስ፣ 2010፤ 300)፡፡

በእርግጥ በስተመጨረሻ፣ ዘይኔም ሆነ ዮሴፍ እንደዚሁም ቶላ ከሁለት ዓመታት ቆይታ በኋላ ከሌሎች ጓደኞቻቸው ጋር በአንድነት ወደ ጅማ ዩኒቨርሲቲ ሲሄዱ የልቦለዱ ታሪክ

ያስነብበናል፡፡ ይሁን እንጅ እነዚህ ሦስት ተጋዳሊ ገፀባህርያት በምን እና እንዴት ወደ ነባሩ ዓለም እንደተመለሱ፣ ያመጧቸው ተክሕኖዎችም ምን ምን እንደሆኑ በግልጽ ባለመታየታቸው እና ለሌሎች ነባር ማኅበረሰቦቻቸው ያጋሯቸው በረከቶች ባለመኖራቸው በዚህ ክፍል ውስጥ እነዲታዩ አድርጓቸዋል፡፡

ፕ/ር እሴም እንደዚሁ፣ ምንም እንኳን የተጋድሏቸው ዓብይ ጉዳይ የሆነውን እና በአክሱም ሐውልት ስር የሚገኘውን ድብቅ እውነት ቢያገኙም፤ በስተመጨረሻ ከሌሎች ተጋዳሊያን በተለየ መልኩ ቀድሞ ወደመጡበት እና ወደ መነሻቸው ሲመለሱ አናስተውልም፡፡ ይልቁንም በዚያው ወደ ኢትዮጵያ ሰሜናዊ ክፍል በማምራት ከራማ ከተማ ላይ ከትመዋል (ኤልያስ፣ 374-378)፡፡

## 3.4.2. ተዓምራዊ በረራ

ሚታዊ ተጋዳሊያን ወደ ተጋድሎ የሚገቡት ከተጋድሎ በኋላ በሚያገኙት ጸጋ ማኅበረሰባቻን እና ዓለምን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ለማዳን ነው፡፡ ታዲያ የተጋዳሊያኑ በተጋድሏቸው ያገኙትን ሽልማት ይዘው ወደተነሱበት ዓለም መመለስ ደግሞ የተልዕኮው አንዱ አካል ነው፡፡ ይሁን እንጅ የመመለሻው መንገድ አሁንም በድጋሚ በተቃዋሚዎች ሊያዝ ወይም የተጋድሎው ተቃዋሚዎችን ሊያገኙ ይችላሉ፡፡ የተጋዳሊኑን ወደ ዓለም የመመለስ ፍላጎት ደግሞ ፈጣሪን ወይም ሌሎች ሰይጣናዊ መናፍስትን ቅር የሚያሰኝ ከሆነ፣ በመጨረሻ ደረጃ ሚታዊ ዙሪቱ በአስቸጋሪ ኃይል የተሞላ እየሆነ እና አብዛኛውን ጊዜ ደግሞ አስቂኝ መልክ ይዞ አሊያም ተከታታይ እየሆነ ይመጣል፡፡ ታዲያ አሁን ተጋዳሊያኑ የብዙ ጸጋዎች ባለቤት ሆነዋልና፤ እነዚህን ሁሉ አስቸጋሪ እና ውስብስብ መሰናክሎች በአንዳች ተጨባጭ ባልሆነ፣ ተዓምራዊ እና ድንቅ በሆነ በረራ ያልፏቸዋል (Campbell፣ 2004)፡፡

በኢቶ<sub></sub>ጵ ልቦለድ ውስጥ ከምናገኛቸው ተጋዳሊ ገፀባህርያት መካከል ኢትኤል የዚህ ተዓምራዊ በረራ ተቋዳሽ ነው፡፡ ኢትኤል ሁሉንም የተሰጡትን ተጋድሎዎች ያምንም ማመንታት እና ማቅማማት በብቃት፣ በትዕግስት፣ በጽናት ፈጽሟል፡፡ በበርካታ አሰልቺ እና አድካሚ ተጋድሎዎች ውስጥ አልፎ ሁሉንም በረከቶች ለመቀበል በቅቷል፤ እነዚህ በረከቶች የተጋድሎው ሽልማቶች ናቸውና፡፡

ከልቦለዱ ታሪክ እንደምንገነዘበው፣ ምንም እንኳን ኢትኤል በእልህ አስጨራሽ ተጋድሎ ውስጥ አልፎ ታላቅ ዓለምን የማዳን ጸጋ ቢቸረውም፤ ወደዓለም በቀላሉ ተመልሶ ለመድኃኔ ሕይወት ለመብቃት ግን አሁንም ብዙ ውስብስብ መንገዶች ይጠብቁታል፡፡ ቢያነስ የሄደባቸውን መንገዶች መልሶ መርገጥ አለበት፡፡ በዚያ መንገድ ለመመለስ ደግሞ ቢያንስ እንኳን ዘልቆ ሲገባ ያጋጠመውን ድካም እና ጣጣ እንዲሁም ሌሎች ያልታወቁ አዳዲስ ሁነቶችን እንደገና መጋፈጥን ይጠይቃል፡፡ ይሁን እንጅ አንድ ጊዜ ለታላቅ ልዕልና ተመርጧል፣ ተልዕኮውንም በብቃት ፈጽሟልና ምንም ነገር የማይሳነው የማይታመን አይነት ጸጋን ጨምሮ አጎናጽፎታል፡፡

ኢትኤል አሁን ቀድሞ ወደተነሳበት (የቀድሞ ግዛቱ) በመመለስ በጭንቅ ውስጥ ለወደቀችው የልጅነት አብሮአደጉ ፅዮን በፍጥነት ደርሶ፣ ዓለምን የማዳን ተክኖውን "ሀ" ብሎ ጀምሯል፡፡ ታዲያ ሲመለስ እንደቀድሞው ሁሉ በእግሩ አሊያም በመኪና አልነበረም፤ ከተጋድሎው በተበረከተለት የማይታመን እና ረቂቅ በሆነ ምትሃታዊ ጸጋ እንጂ፡፡ ከልቦለዱ በቀጥታ የትሰደ ማስረጃ እንመልከት፤

> …መቋሚያቸውን ሰጡት፤… "በእምነት ተሞልተህ ያዘው" አሉት፡፡ ኢትኤል እጆቹን ዘርግቶ ዘንጉን ያዘ፡፡ … ያሉትን በሙሉ ከሰማ በኋላ አይኑን ጨፍኖ ፅዮንን እያሰበ ዱላውን ጭምቅ አድርጎ ያዘው … አንጎሉን እንደማዞር እና እግሩም ውትርትር አለበት፡፡ የእርሳቸው ድምጽም እራቀው፤ ሰውነቱን ይበርደው ጀመር፡፡ አይኑን ሲገልጥ እራሱን ‹‹ባህር ሃጠራ›› አጠገብ ነበር ያገኘው፤ (ኤልያስ፣ 2010፤ 358)፡፡

አዎ! አሁን ኢትኤል በአንዳች ተዓምር ከምንም ነገር ፈጥኖ፣ በዓይን አርግብግቢት ቅፅበት ውስጥ፣ በአጋንንት አዞ የተዋጠችውን የፅዮንን ነፍስ ሊታደጋት በጭንቅ ከምትሰቃይበት እንግዳ ቦታ "ባህር ሃጠራ" ድንገታ ዱብ ብሏል፡፡ ይህ የኢትኤል በዚህ አይነት ተዓምር መመለስ እንዲሁ መመለስ ብቻ ሳይሆን የማዳን ተልዕኮንም ጨምሮ ያነገበ ነው፡፡

የፅዮንን ነፍስ ማዳን ደግሞ የተጋድሎው ሌላኛው አካል ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ምክንያቱም ከዚያ ከገባችበት ውስብስብ እና ምትሃታዊ የሆነ ሰይጣናዊ ዓለም ውስጥ ይቺን ምስኪን ነፍስ መንጥቆ ማውጣት ቀላል አይደለም፡፡ ስለዚህ ይህ የማዳን ተግባር ከተጋድሎ መልስ ሌላ ፈተና ነው፡፡ አንድም ማዳኑ በተግባር የሚፈተንበት፣ አንድም ደግሞ የተጋድሎውን ማረጋገጫ የሚያገኙበት እና ተመልሶ ከተጋድሎው ዓለም ወደነባሩ ማኅበረባህላዊ ዓለም በድል የሚቀላቀልበት፡፡ በመጨረሻም፣ የተጋድሎው ጉዞ እየተገባደደ

እና መሰል በረከቶች እየተገለጡለት በመሆኑ፤ በልዕለተፈጥሮ እና በልዕለሰብዕ ጓዶቹ እገዛም ቢሆን ፅዮንን ከዚህ መዓት ውስጥ አውጥቶ የማዳን ጸጋውን ለዓለም ይፋ አድርጓል፡፡

### 3.4.3. የመመለሻውን በር ማለፍ

ተጋዳሊያን ያጋጠሟቸውን ፈተናዎች እና መሰናክሎች ጨርሰው ወደ ቀድሞ ቤተሰቦቻቸው፣ አካባቢያቸው፣ ማኅበረሰባቸው እና ግዛታቸው ሲመለሱ ምዘናዎቻቸውን የተወጡባቸው እና የተመለሱባቸው መንገዶች በእያንዳንዱ ሚት እና ታሪክ ልዩነት ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም አንዳንድ ጊዜ ከሚከተሏቸው ኃይላት በመሸሽ፣ በልዕለተፈጥሮ አካላት ዕርዳታ፣ እንዳንድ ጊዜም በሁኔታዎች መመቻቸት (ሁኔታዎች በራሳቸው ሲፈቅዱ)፣ ወደ ቀድሞ መኖሪያቸው ይመለሳሉ፡፡ ይሁን እና ሲመለሱ በአካል፣ በዕድሜ፣ በስነልቦና እና በመሳሰሉት ማንነቶቻቸው ላይ ለውጥ ሊኖር ይችል፡፡ በተጋድሏቸው ወቅት ባጋጠሟቸው ሳንካዎች ምክንያት በዕድሜ ገፍተው (አርጅተው)፣ ከቀድሞ የተሻለ አስተዋይ እና አዋቂዎች ሆነው፣ በአካላቸው ጠንክረው፣ ከበፊቱ የበለጠ ጠቢብነትን ተክነው ወዘተ ይመለሳሉ (Hunter፣ 2007)፡፡

በኢቶፖጵ ልቦለድ ውስጥ ለተጋድሎ የሄዱት ሰባት ተጋዳሊ ልዑክንም እንዲሁ ወደነባሩ ዓለማቸው የተመለሱት ሁኔታዎች በተለያየ መንገድ ነው፡፡ ግን ሁሉም ቢሆን በእድሜያቸው (ጥቂት የሚባሉ ጊዜያትንም ቢሆን) ጨምረው፣ በእውቀት ከበፊቱ በተሻለ በስለው ወደነባሩ ዓለም፣ ዳግም ወደጅማ ዩኒቨርሲቲ ለፅዮን ምርቃት በጋራ ተሰባስበዋል፡፡ ከዚህ ሁሉ በፊት ግን፣ በልቦለዱ በግልፅ እንደሰፈረው፣ ኢትኤል በታላቅ የልዕለ ተፈጥሮ እርዳታ እና በአንዳች ተዓምራዊ በረራ ወደነባሩ ዓለም ጉዞውን ጀምሯል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ ደግሞ የቤተሰቦቹን ድብቅ ሴራ እና የፅዮንን ጉዳት ለማስታረቅ የሚያደርገው ትግል የመመለሻውን በር ለማለፍ ሌላው ፈተና ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

ኢትኤል ከዚያ ሁሉ ተጋድሎ በኋላ ፅዮንን ወደቀድሞ መኖሪያ ሰፈራቸው ብሎም ወደቤተሰቦቹ ቤት ይዞ ለመመለስ ብዙ ፈታኝ ነገሮች እንዳጋጠሙት ታሪኩ እራሱ ይነግረናል፡፡ በዚህ መሠረት የመመለሻ ቅጽሩን የዘጉባቸው ደግሞ ቤተሰቦቹ ብቻም አልነበሩም፤ ቤተሰቦቹ ተንከባክበው ያሳደጉት ሰይጣናዊ ዘንዶም ቀላል አልነበረም፡፡ ይህ ጉዳይ የተጋዳሊውን ፈተና ሁለት መልክ እንዲኖረው ያደርገዋል፡፡

የመጀመሪያው፣ ቤተሰቦቹ ከፅዮን ቤተሰብ ጋር እጅግ የቆየ እና የተወሳሰበ ጸብ ውስጥ መግባት ብቻም ሳይሆን ለጽዮን ቤተሰቦች ድህነት እና ለአባቷ መሞት እንዲሁም ለራሷ ለፅዮን "ባህር ሃጠራ" ውስጥ መወርወር ቤተሰቦቹ ተጠያቂዎች ናቸው፡፡ ስለዚህ ይህን ሁሉ ትብትብ ለመፍታት እና የፅዮንን እና የእርሱን አብሮ መሆን ቤተሰቦቹ አምነው ይቀበሉ ዘንድ ማሳመን፣ በራሱ ታላቅ የፍቅር ሐዋርያዊነትን መካንን ይጠይቃል፡፡ ስለሆነም ለኤትኤል የተሰጠው ክህነት የቱንም ነገር ቢሆን የማሸነፍ ኃይል አለውና፤ ፈታኝ ቢሆንም ወደ ቤተሰቦቹ ቤት አስገብቷታል፡፡

ሌላው እና ሁለተኛው ፈተና ደግሞ፣ ለዘመናት ከቤት ውስጥ ተኙቶ ሲቀለብ የኖረውን እና የማምለኪያ ዘንዱቻውን ከቤት ውስጥ አውጥቶ መጣል አሊያም መግደል፡፡ ይሁን እንጅ ይኸኛው ተጋድሎ ከመጀመሪያው ተጋድሎ ከበድ ያለነው፡፡ ምክንያቱም በአንድ በኩል፣ ቤተሰቦቹ ይህንን ጣያታቸውን ማጣት ስለማይፈልጉ የእነሱን ይሁንታ በእጅጉ ይጠይቃል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ፣ እራሱን ዘንዶዉን ለማስወጣት ወይም ለመግደል ታላቅ ጥበብን፣ ማስተዋልን፣ ጉልበትን፣ ዘዴን፣ ዕውቀትን መካን ይጠይቃል፡፡ ኢትኤል ግን ይህንንም ቢሆን በታላቅ ኃይል እና ትግል ተወጥቶታል፤ ዘንዶውን ቀጥቅጦ ገድሎት ከገባበት ተጋድሎ ውስጥ ወደ ነባሩ ዓለም ተቀላቅሏል፤ (ኤልያስ፣ 2010፤ 372-373)፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ጥናት ከዚህ በላይ በትንተናው ክፍል ውስጥ እንዳየነው፤ በኤቶ፦ጵ ልቦለድ ውስጥ ካሉ ገፀባህርያት መካከል ስምንቱ ተመርጠው በእያንዳንዱ ዓበይት የተጋድሎ ጉዞ ደረጃዎች ውስጥ ያለፉባቸውን የተጋድሎ ዝርዝር የጉዞ ሂደቶች ተንትኖ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ በዚህ መሠረት ከእነዚህ ለትንተና ከተመረጡት ገፀሰዎች መካከል፣ ኢትኤል፣ አብርሃም እና መርየም ከመነሻቸው ጀምሮ የገጠሟቸውን መሰናክሎች ሁሉ ተቋቁመው አልፈው፣ የተሰጣቸውን ተልዕኮ ሁሉ በብቃት በመወጣት ከሦስቱም ዋና ዋና የተጋድሎ ዓለማት ውስጥ ይገኛሉ የተባሉትን ጸጋዎች ተቋዳሽ ሆነዋል፤ ለመጨረሻው ተክህኖም በቅተዋል፡፡ ይኸውም በዋናነት ኢትኤል ለነባሩ ዓለም ማኅበረሰቦች መድኃኔ ሕይወትነት፣ አብርሃም እና መርየም ደግሞ ለወሰን የለሽ ፍቅር አንጸባራቂ ተምሳሌት ይሆኑ ዘንድ ተመርጠው ታላላቅ የክብር አክሊልን ተቀዳጅተዋል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ፣ ፕ/ር እሴ ከብዙ አድካሚ እና ፈታኛ የተጋድሎ ጉዞ በኋላ ውስጣቸውን ሲኮረኩራቸው የነበረውን የመንፈሳዊ እና ታሪካዊ ቅይጥ እውቀትን አውቀው

ለሌሎችም አሳውቀዋል፡፡ ኢትዮጵያንን ሊያጠፋ የተዘጋጀውን ወጥመድ አክሽፈው የዜጎችን ሕይወት ነፍስ ዘርተውበታል፤ በእያንዳንዷ እስትንፋሳቸው የሚተነፈሷትን አየር ሚስጥር ገልጠዋል፡፡ በተለይም በሴረኞች የተዘጋውን የእያንዳንዱን የሃገሪቷን ዜጎች የመንፈሳዊነት እና የእምነት በር ከፍተዋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ዮሴፍ ከዋናው የተጋድሎ ጉዞ መንገድ ላይ በአጋጣሚ ካገኘው የታሪክ እና የሳይንስ ተመራማሪ እራስታ ጋር ተጠልፎ በመሄድ አንዳች ጥበብን ተምሮ መሰሎቹን ከአልባሌ ተግባር ለመታደግ በሚያስችል መድኃኒት ቅመማ ተሰማርቷል፡፡ ምንም እንኳን የጥበቡ ባለቤት ሆኖ ሌሎችን ሲፈውስ ባናስተውልም፣ ከሌሎቹ ተጋዳሊ ጓዶቹ ተነጥሎ እና ዋናውን የተጋድሎ ጉዞ አቋርጦ በአንድ ቅጽበት ወደ ሕይወቱ የመጣችውን አጋጣሚ ተጠቅሞ ድንገተኛ የሆነውን የልቡን መሻት ለማርካት እና ለሌሎቹ ፈውስ ለመሆን አልሞ ጉዞውን ቀይሯል፡፡

ዘይኔ፣ ቶላ እና ናያድ ደግሞ በየተጋድሎ ሂደቶች ውስጥ ሲገቡ በአስተምህሯቸው ከተማረኩባቸው አባቶች ጋር ቀርተዋል፡፡ ስለሆነም የእያንዳንዱ በዚያው መቅረት ምክንያት ነበረው፤ ይኸውም የበለጠ ጥበብ እና ዕውቀት ፍለጋ፤ ወይም ለተጋሎ በገቡባቸው የተጋድሎ ግዛቶች ውስጥ ባሉት በረከቶች መማረክ ነው፡፡ በስተመጨረሻ ግን ሁሉም የተሻለ እውቀት እና ጥበብን ሰንቀው፣ ያላወቁትን አውቀው፣ አንዳች ቁምነገርን ሸምተው ወደነባሩ ዓለም በመመለስ ከዚያው ከመነሻቸው ጅማ ዩኒቨርሲቲ ዕዮንን ለማስመረቅ በጋራ ከትመዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## ማጠቃለያ

ይህ ጥናት "ሚታዊ ንባብ በኢቶዮጵ ረጅም ልቦለድ ውስጥ" የሚል ርዕስ የተሰጠው ሲሆን የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ደግሞ፣ ለጥናት የተመረጠውን ኤቶዮጵ ረጅም ልቦለድ ከሚታዊ ሒስ አንጻር በመመርመር በልቦለዱ ውስጥ የቀረቡትን የሚታዊ ተጋድሎ (ጉዞ) ደረጃዎችን ለይቶ ማውጣት እና ተንትኖ ማሳየት ነው፡፡ ይህን ዋነኛ ዓላማ ከግብ ለማድረስ ደግሞ፤ በልቦለዱ ውስጥ የቀረቡትን ሚታዊ ተጋዳሊያን መለየት፣ ለተጋዳሊ ገፀባህሪያት ተጋድሎ መነሻ የሆኑ ጉዳዮችን መተንተን፣ ያለፉባቸውን ሚታዊ ተጋድሎዎች መፈከር እና በተጋድሏቸው ያገኟቸውን በረከቶች መመርመር የሚሉ ንዑሳን ዓላማዎችን አንግቧል፡፡ በትንተናው ውስጥ ደግሞ መለየት፣ መነሳሳት እና መመለስ የሚሉትን ዓበይት የተጋዳሊያን የተጋድሎ ጉዞ ደረጃዎች መነሻ በማድረግ፤ በተመረጠው ልቦለድ ውስጥ ያሉ እና ዋነኛ በሆኑት ገፀባህሪያት (ኢትኤል፣ አብርሃም፣ መሪየም፣ ናያድ፣ ዘይኔ፣ ቶላ፣ ዮሴፍ እና ፕ/ር እሴ) በእያንዳንዱ ዓበይት የጉዞ ደረጃዎች ውስጥ ያለፉባቸውን የተጋድሎ ጉዞ ሂደቶች ተንትኖ አቅርቧል፡፡ በዚህ ሂደትም እነዚህ ገፀባሕሪያት በልቦለዱ ውስጥ ከነባሩ ዓለማቸው ሲነጠሉ፣ ወደ አንዳች አዲስ እና እንግዳ የሆነ ቦታ ውስጥ ገብተው የሞት ሽረት ትግል ሲከውኑ እና በስተመጨረሻም አንዳች ጸጋን፣ ዕውቀትን፣ ጥበብን ወዘተ ተክነው ወደቀደመው መነሻቸው ሲመለሱ አሳይቷል፡፡

በተመረጠው ልቦለድ ውስጥ የሚገኙት ተጋዳሊ ገፀባርያት በአንዳች ተዓምር፣ በአጋጣሚዎች፣ በገዛ ፈቃዳቸው ወይም ደግሞ በውል ልብ ባላሏቸው ረቂቅ ጉዳዮች ተጠርተው ተጋድሏቸውን ሲገቡ በትንተናው ውስጥ አስተውለናል፡፡ የተጋድሎ ጥሪዎቹ እንደሚለያዩ ሁሉ ጥሪዎቹ የቀረቡባቸው ድግግሞሾችም እንዲሁ ይለያያሉ፡፡ በዚህ መሰረት ሁሉም ከአንድ ጊዜ እስከ አራት ጊዜ ድረስ ጥሪየተቀበሉ ተገጋዳሊያንን አይተናል፡፡ ጥሪውን ያልተቀበሉት ተጋዳሊ ገፀባህርያት ደግሞ የደረሰባቸውን መርገም እንዲሁ ታዝበናል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ተጋዳሊያኑ በእያንዳንዱ የተጋድሎ ቅጽሮች ውስጥ ሲገቡ የሚያጋጥሟቸውን መከራዎች እና እልህ አስጨራሽ ፈተናዎች በምን መንገድ እንደተቋቋሟቸውም እንዲሁ ለማየት ሞክረናል፡፡ በዚህ መሠረት አንዳንዶቹ በዘዴ እና

በብልሃት፤ ሌሎቹ ደግሞ በኃይል ሲገዳደሯቸው አይተናል፡፡ ነገር ግን በእያንዳንዱ የተጋድሎ ጉዟቸው እና በሚያጋጥሟቸው ታላላቅ ፈተናዎች ወቅት አንዳች አጋዥ ኃይል ከኋላቸው፣ ከጎናቸው አሊያም ከፊት ለፊታቸው እንደሚኖርም አስተውለናል፡፡

አንዳንዶቹ ተጋዳሊያን የማይታሰቡ፣ የማይሞከሩ ከሚመስሉ ሁነቶች ጋር በመጋፈጥ ወደ ፊት ሲራመዱ እና ብዙ መከራዎችን በመቀበል ሲገሰግሱ ተመልክተናል፡፡ በዚህ ሂደትም ብዙ መልካም ነገሮች ከአስቸጋሪ ጉዳዮች ጋር በአንድነት ሲቀርቡላቸው አይተናል፡፡ ተጋድሊያኑም አስቸጋሪ የሚባሉትን መሰናክሎች ሁሉ አልፈው እነዚያን ቅዱስ ጸጋዎች ለመጎናጸፍ ሲታትሩ ተስተውለዋል፡፡

በአጠቃላይ በትንተናው ውስጥ የተካተቱት ሁሉም ገፀሰዎች በአንዳች ግልጽ ወይም ህቡዕ መንፈሳዊ ጥሪ ምክንያት የመኖሪያ አካባቢያቸውን፣ የለመዱትን ቀያቸውን ጥለው ወደሌላ እንግዳ ቦታ ይሄዳሉ፡፡ ከበዙ ውጣውረድ፣ ከአድካሚ ጉዞ፣ በርካታ አይነት ካላቸው ፈተናዎች በኋላም የሆነ አስደሳች፣ አስገራሚ፣ አዲስ የሆነ በረከትን ያገኛሉ፡፡ እያንዳንዱ ተጋዳሊ ገፀባህርያት ያገኙት በረከት ግን ይለያያል፡፡ ምክንያቱ ደግም ከመካከላቸው አንዳንዶቹ ሁሉንም ተልዕኮዎች አልፈጸሙምና፤ የተሰጣቸው በረከትም እንዲሁ ውስን ነው፡፡ ሌሎቹ ደግሞ ሁሉንም ችግሮች ተቋቁመው አልፈዋል እና ለታላቅ ክህነት በቅተዋል፤ በታላቅ ገድል ወደ ነባሩ ዓለማቸው ተመልሰውም በተሰጣቸው ተልዕኮ እና ተክህኖ ሌሎችን ለማዳን ታድለዋል፡፡

# ዋቢ ጽሑፎች

ቀና ለሚ፡፡ (2010)፡፡ "የኦሮሞ ሚቶልጂ ይዘታዊ ትንተና" (ቴሲስ)፡፡ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ታደሰ ሺበሺ፡፡ (2005)፡፡ *"ሚቶሎጂያዊ ጥናት እቴሜቴ ሎሚ ሽታና ይወስዳል መንገድ ያመጣል መንገድ"* (ቴሲስ)፡፡ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ቴዎድሮስ ገብሬ፡፡ (2001)፡፡ *በይነ ድሲፕሊናዊ የሥነ ጽሑፍ ንባብ፡፡* አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፡፡

አማቀፍ ተናገር፡፡ (2010)፡፡ "*ሚታዊ* ንባብ በይስማዕከ ወርቁ *ዴርቶጋዳ* እና *ራማቶሓራ* ረጅም ልቦለዶች"፡፡ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ፡፡ ባሕር ዳር፡፡

ኤልያስ ገብሩ አዕምሮ፡፡ (2010)፡፡ *ኤቶዮጵ*፡፡ Nebadan Publishers. Addis Ababa, Ethiopia.

Al-Haidari, A. (2012). "The Reflection of Aniciant Mythical Caracters in Europian Literature: A review of Antiquity and Contemporaneity". International Journal of Social Science Tomorrow. Vol. 1 No. 4.

Ann, S. (1982). "The Feature Story as Mythological Artifacts". College of Journalism. University of Maryland. Presented to The Qualitative Studies Division, Association for Education in Journalism Annual Convention, Athens, Ohio.

Binford, P. (2011). "Common Mythological Motifs in literature". Graduate School of Humanities And Social Science. Nagoya City University. Nagoya Japan.

Campbell, J. (2004). *A Hero with A Thuosand Faces.* Princeton Univesity Press. Princeton and Oxdord.

Cirlot, J.E. (1971). *A Dictionary of Symbols* (Second ed.). Routledge & Kegan Paul Ltd.

Culler, J. (1997). *Literary Theory: A Very Short Introduction*. Oxford University Press. New York.

Cupe, L. (2009). *Myth* (Second ed.). Routledge Taylor & Francis Group London and New York.

Eliade, M. (1963). *Myth and Reality*. Harper & Know, Publishers. New York & Evanston.

Fernandez, A. & Lipscomb, A. (2017). “A Special Issue in The Eternal Return of Myth: Myth Updating in Contemporary Literature”. Journal of Comparative Literature and Aesthetics.

Finnegan, R. (1992). *Oral Tradition and The Verbal Arts.* Routledge. London and New York.

Frey, J. N. (2000). *The Key: How to Write Damn Good Fiction Using The Power of Myth*. ST. Martin’s Press. New York.

Halpe, A. (2010). “Between Ayth and Meaning: The Function of myth in Four Postcolonial Novels” (PHD Thesis). Department of English and The Collaborative Program in South Asian Studies. University of Torono.

Harris, J. (2003). “Myth and Literary History: Two Germanic Examples”. The Albert Lord and Milman Parry Lecture.

Hartman, D. (2009). “The Hero’s Journey of Selftransformation: Models of Higher Development from Mythology”. Journal of Heart- Centered Therapies, 2009, Vol. 12, No.2, PP. 3-93.

Hartman, K. L. (2000). “The Rhetorical Myth of the Athlate As A Moral Hero: The Implications of Steroids in Sport And The Threatened Myth”. Lausiana State University and Agriculture and Mechanical College (PHD Thesis). Departemants of Communication Studies.

Hunter, Cheryl, A. (2007). “Mythological Heroes and The Presence of The Hero and Journey archetypes in “The Lord of the Rings” and “Harry Potter”” (M.A Thesis and Capstones). University of new Hampshire, Durhan.

Jaja, J.M. (2012). “Myth in African Concept of reality”. International Journal of Adminstration and Policy Studies. Vol.6(2), PP. 9-14, Feb. 2014.

Klaus, S. (2010). “Heroes in Vertual Space”. University of Ljublijana, Faculity of Arts Department of Ethnology and Cultural Anthropology. Cerkova 7, 1000 Ljumbljana, Slovenea.

Leeming, D. (2002). *Myth：A Biography of Bilief*. Oxford University Press.New York.

Levi-Strauss, C. (1978). *Myth and Meaning*. Routledge. London and New York.

L-Jay, f. (1997). “A Hero’s Jouyney: A Freshman Orientation Challenge Cource Program”. California State University Fresno, Freshman Orientation, Rites of Passage, Rope Cources.

Losada, J. (2015). “Myth and origion: Men Wantto Know”. Universite Complutenese, Madrid Spain. Journal of Literature and Art Studies, Oct. 2015, Vol. 5, No. 10, 93o-945.

Lugli, U. (2014). “The Concept of Myth”. Journal of Studies in Social Scinces. ISSN 2201-4624. Vol. 6, Number 1, 2014, 38-57.

Lynch, P. (2010). *African Mythology Atoz* (Second ed.). Chelsea Hous Publishers. New York.

Matey, N. (2016). “The Most Common Mythological Themes Across Different Cultures”. International Journal of Science Thechinology and Management. Vol. 5, Issue No. 05, May 2016.

Moghaddam, S.S. (2016). “Analytical Study of The Status oof Myth in The Creation of literary and Artistic Works”. Advances in Language and

literary Studies. ISSN: 2203-4714, Vol. 7, No. 1, Feb. 2016. Australian International Accademic Center, Australia.

Morales, H. (2007). *Classical Mythology: A Very Short Introduction*. Oxford University Press. New York.

Sagal, R. A. (2004). *Myth*: *Very Short Introduction*. Oxford University press. New York.

# መግለጫ

“ሚታዊ ንባብ በኤቶᎋጵ ረጅም ልቦለድ ውስጥ” የተሰኘ ርዕስ የተሰጠው ይህ ጥናት፣ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ ሂዩማኒቲስ ፋኩሊቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል ለአማርኛ ሥነጽሑፍ ሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ መመረቂያ ቴሲስ ሲሆን፤ ከዚህ በፊት በማንኛውም ዩኒቨርሲቲ የዲግሪ ማሟያ ሆኖ አልቀረበም፡፡ ለጥናቱ በምንጭነት የተጠቀምኩባቸው መረጃዎችን በሙሉ በተገቢው መንገድ መጥቀሴን በፊርማየ አረጋግጣለሁ፡፡

<u>ብርቱካ ሙላው</u>　　<u>ነሐሴ 2012 ዓ.ም</u>　　<u>ባሕር ዳር</u>